Translated by Zemen@MERF ET Team

ጸንታችሁ ቁሙ

ስለእግዚአብሔር ጦር እቃ የአንድ ወጣት ክርስቲያን መመሪያ

ፒተር ጄፈሪ

የዊልስ ኢቫንጀሊካል ፕሬስ

ማውጫ

መግቢያ 7

1. ጠላት 9
2. የጠላት ስልት 12
3. የእኛ ብርታት 19
4. የእውነት ቀበቶ 26
5. የጽድቅ ጥሩር 31
6. የሰላም ወንጌል 39
7. የእምነት ጋሻ..... 45
8. የደህንነት ቁር 51
9. የመንፈስ ሰይፍ 56
10. “ሁሉንም የጦር እቃ በጸሎት መልበስ” 63
11. ድል 67

'በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ። የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፉት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወምና ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ። እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፤ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው። በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ።'

ኤፌ 6፡10-18

መግቢያ

‘ወደ ኢየሱስ ና ከዚያ ሁሉም ችግርህ ያበቃል’ ከአንዳንዶች የምንሰማው መልእክት ነው። ልክ “አሁን ቀኑን ሁሉ ደስተኛ ነኝ” በማለት እንደሚጨርሰው አዝማች ጥቂት መዝሙሮችም ይህን ትምህርት የሚያረጋግጡ ይመስላል - ይሁን እንጂ እንዳለመታደል ሆኖ፣ ይህ ዳግም ከተወለደ በኋላ የክርስቲያን ተሞክሮ አይደለም በዋናነትም ይህን አይደለም ቅዱሳት መጻህፍት የሚያስተምሩት።

አንድ ሰው በንስሀና በእምነት ወደ ክርስቶስ ሲመጣ - ሀጢአት - ትልቁ ችግሩ - ምላሽ አግኝቷል። የደኅንነት ደስታ እና ከእግዚአብሄር ያገኘው ሰላም አይምሮን የሚያልፍ ነው ይህ ደግሞ ለአንዳንዶች ለቀናት፣ ለሳምንት ወይም ለወራትም እንኳን ይቆያል። ሄዶ ሄዶ ግን ዳግም ከመወለድ በፊት በፍጹም የማይታወቁ ሌሎች ችግሮች ግን ራሳቸውን መግለጥ ይጀምራሉ። ከዚህ የተነሳ ‘ቀኑን ሙሉ መደሰት’ ይቅርና ወጣቱ ክርስቲያን የመጠራጠርን፣ የጥፋተኛነትን እና ስለ ሀጢአት የመወቀስን ሀዘን ከዚህ በፊት በማያውቀው ሁኔታ ያውቃል። በዚህ ሁሉ ላይ፣ አዲስ ስለተቀበለው እምነት ከወጆቹና ከዘመዶቹ አለመግባባትና ተቃውሞ ይገጥመዋል።

ይህ ሁሉ ለአዲሱ አማኝ እጅግ አስፈሪ ይመስላል ቅዱሳት መጻህፍት ግን ይመጣል ብሎ መጠበቅ እንዳለበት ይናገራል። ጌታ ኢየሱስ ራሱ ደቀ መዛሙርቱን በአለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ” ብሎአቸዋል (ዮሐ 16፡33)። ሐዋርያው ጳውሎስም በመጀመሪያ የሚሽነሪ ጉዞው የመሰረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት ሊያጠነክራቸውና ሊያጽናናቸው በመመለስ “ወደ እግዚአብሄር መንግስት በብዙ መከራ ልንገባ ይገባናል” ብሏቸዋል (ሐዋ ስራ 14፡22)።

እንዲህ መሆን ያለበት ለምንድን ነው? እውነታው ክርስቲያኖች ስንሆን፣ ሁሉም ነገር ወደሚያምርና ምቹ ወደሆነ ወደ አመት በአል ቤቶች አይደለም የምንገባው፣ ብርቱ ጦርነት ወዳለበት ወደ ጦር ሜዳ ነው እንጂ። አሁን በእግዚአብሄር ሰራዊት ውስጥ ወታደሮች ነን ጠላትም በእኛ ላይ ከፍተኛ መከራን ያመጣል። በዚህ መንፈሳዊ ጦርነት የምንሆነው ነገር ምን ያህል የታቅን በመሆናች ላይ እጅጉን የተመሠረተ ነው።

በኤፌ 6፡10-17፣ እግዚአብሄር ለህዝቡ ስለሰጠው የጦር ዕቃ ጳውሎስ ያስተምረናል። የእርሱ የጦር እቃ ነው፣ ለእኛ የሰጠው እኛም ልንለብሰው ይገባል። ይህ መጽሐፍ ያንን ክፍል

በእምነታቸው ጸንተው እንዲቆሙ ለወጣት ክርስቲያኖች ሊተረጉም ይፈልጋል ። ከዚህ በኋላ ያለውን ከማንበብህ በፊት እባክህ የኤፌሶንን የመጀመሪያ 3 ምዕራፎ በጥንቃቄ አንብብ።

የሚከተሉት ምዕራፎች ከዶክተር ማርቲን ሎይድ ጆንስ ጽሁፎች በርካታ ጥቅሶችን ያጠቃልላሉ። ከዚህ በመቀጠል ለምለው ነገር ባለእዳ የሆንኩባቸውን የእርሱን ሁለት መጽሐፎች፣ *የክርስቲያን ውጊያና ክርስቲያን ወታደርን* እንድታነቡ አጥብቄ ልመክራችሁ እወዳለሁ።

1. ጠላት

“ውጊያችን ከስጋና ከደም ጋር አይደለምና . . .” (ኤፌ 6፡12)

የክርስቲያን ህይወት እንዲህ ውጊያ የሆነው ለምንድን ነው? በኤፌሶን የመጀመሪያ 3 ምዕራፎች የተገለጸውን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ካደረገልን፣ በመንፈሳዊ ህይወት ይህን ያህል የምንታገለው ለምንድን ነው ብዙ ጊዜስ የምንወድቀው ለምንድን ነው? መልሱ በኤፌሶን ቁ 11፣ 12 እና 16 ተሰጥቶናል። ተስፋ አስቆርጦ ሊጥለን በሙሉ ህይሉ በስራ ላይ ያለ ጠላት አለን። ያ ጠላት ዲያብሎስ ነው።

ዲያብሎስ ተራ ጠላት አይደለም። ህይሉና ተጽኖው አስፈሪ ነው፡ ሠራዊቶቹም አለምን ሞልተዋል። ኢየሱስም እንኳን “የዚህ አለም ገዢ” (ዮሐ 14፡30) ብሎ ይጠራዋል። ዛሬ ብዙ ሰዎች ዲያብሎስ የሚለውን አጠቃላይ ጉዳይ እንደመካከለኛው ዘመን ተራ ነገር አስወግደውታል፤ ኢየሱስ ግን እርሱ የእውነት ማንነት እንደሆነ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ካመንን የዲያብሎንም እውነተኛነት በትክክል ማመን አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ክፉ ተጽዕኖ ብቻ እንዳይደለ ይናገራል። እውነተኛ ማንነት እንደሆነ እንጂ። እግዚአብሔር እንዳለ ሁሉ እርሱም አለ። እርሱ ማን ነው ከየትስ ነው የመጣው?

ምንጭ እና ሃይል

ለሰው ዘር ጠላት መጽሐፍ ቅዱስ በርካታ ስሞችን ይጠቀማል። አንዳንድ ጊዜ ዲያብሎስ ሌላ ጊዜ ሰይጣን ወይም ብኤልዜቡል ወይም ቤልየል ተብሎ ይጠራል። በመጀመሪያ ስሙ (የቀን ኮከብ ማለት የሆነው) ሉሲፈር ነበር። በሰማይም ደግሞ መልአክ ነበር። ስለእርሱ በኢሳይያስ 14 እናነባለን። (የኪንግጀምስ ትርጉም “ሉሲፈር” ብሎ ሲጠራው አ.መ.ት “የንጋት ኮከብ” ብሎ ይጠራዋል። በኋላ ያለልክ የሚመኝ መልአክ ነበር፣ ከእግዚአብሔር በላይ ለመሆን ተመኘ (ኢሳ 14፡13-14)። በእግዚአብሄር ተቀጣ (ቁ 15-17) ከሰማይም ተባረረ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ስራው የእግዚአብሄርን ስራ በሙሉ ማተራመስና ማበላሸት ሆነ።

በመጀመሪያ በኤደን ገነት ውስጥ ሲሰራ እናየዋለን (ዘፍ 3)። በማታለልና በመፈተን አዳምና ሄዋንን ራሱ እንዳደረገው በእግዚአብሔር ስልጣን ላይ እንዲያምጹ ሲያደርጋቸው እናያለን። የሆነው ነገር አዳምና ሄዋንን ብቻ አልነበረም የጎዳው፣ ሁሉን ወንድ፣ሴትና ገና የሚወለዱትንም ልጆች ነው። ይህ የሆነው በአዳም ምክንያት ሀጢአት የሰው ተፈጥሮ ስለሆነ

ነው (ሮሜ 5፡12-14)፣ ከዚህ የተነሳ (አለም በሙሉ በክፉ ስር ሆኗል" (1ዮሐ 5፡19)። ዲያብሎስ የሰውን ዘር በሙሉ ይቆጣጠራል። እርሱ ጌታ ነው እኛም ስንወለድ የእርሱ ልጆች ሆነን ነው የተወለድነው (ዮሐ 8፡44፤ 1 ዮሐ 3፡10)።

የሰዎች ሀጢአተኝነት ነው ዲያብሎስ በነርሱ ላይ የበላይነት እንዲኖረው ያደረገው። እርሱን እንዲታዘዙት በባሪያዎቹ ላይ አለንጋ ይዞ መቆም የለበትም። በእነርሱ ላይ ያለው ሀጠኢት ስራውን እንዲሰራ ያደርጋል ያ ደግሞ በቂ ነው። ባሪያዎቹን በማታለል መኖሩን እንዲክዱ ያደርጋቸዋል፤ ዘወትር ግን ክፉ ተጽኖው ህይወታቸውን ይቆጣጠራል። አንዳንድ ጊዜ ግልጽ በሆነ መንገድ ይሰራል፤ ክፋትም ሁሉን ይሞላል ። በየትኛውም መንገድ የሴቶችን እና የወንዶችን ህይወት ይገዛል።

የእግዚአብሔር መልስ

ለዚህ የእግዚአብሄር መልስ ምንድን ነው? በሉቃስ 11፡21-22 በተጻፈው ምሳሌ ውስጥ ጌታ ኢየሱስ መልሱን ይሰጣል። "ሙሉበሙሉ የታጠቀው ሀይለኛው ሰው" ዲያብሎስ ነው፤ ወንዶችና ሴቶች "የእርሱ ይዞታ" ናቸው ኢየሱስ ራሱ "ከእርሱ ይልቅ የበረታው" ነው። በቀራንዮ ላይ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በሰው ዘር ላይ ያለውን የዲያብሎስን ይዞታ ሰበረው። ቆላ 2፡13-15ን እና 2፡14-15ን አንብብ። ክርስቲያኖች ስንሆን ሀጢአታችን ብቻ አይደለም ይቅር የተባለው የሰይጣን ጌትነትና ግዛትም ተሰብረዋል። አሁን ኢየሱስ ነው ጌታችን ከዚህም በኋላ የሀጢአት ባሮች አይደለንም (ሮሜ 6፡6-7)።

ይህ ማለት ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ በክርስቲያኖች ላይ ምንም አይነት ስልጣን ወይም ገዢነት የለውም። ምንም ነገር እንድናደርግ ሊያስገድደን አይችልም። ሊፈትነን ይችላል ፈተና ግን ግፊት አይደለም። አንድን ጌታ ከባሪያው ጋር አስበው። ባሪያው የእርሱ ነው እያንዳንዱን ትዕዛዙን እንዲታዘዝ ማስገደድ ይችላል።

"ባሪያ ጉርጓድ ቆፍር፣ ባሪያ ከብቶቹን መግብ! ባሪያ ይህንን አድርግ እዚያ ሂድ ብሎ ሲያዘው ባሪያው ይታዘዛል ባሪያ ስለሆነና ነጻነት ስለሌለው። አንድ ቀን ግን ያ ባሪያ ይሞታል። ጌታው ምናልባት አሁንም ትዕዛዝ ይሰጣል አሁን ግን መታዘዝ የለም። ለምን? ባሪያው ሞቷል የጌታውም ስልጣን አብቅቷል። በሮሜ 6 ውስጥ ጳውሎስ የሚናገረው ይህንን ነው። ክርስቲያን ለሀጢአት ሞቷል (ቁ 11)። አሮጌው ጌታችን፣ ዲያብሎስ፣ ከዚህ በኋላ እንድንታዘዘው ሊያደርገን አይችልም። ከአዲሱ ጌታችን ጋር አዲስ ፍጥረቶች ነን።

ጦርነት

ዲያብሎስ ውሸቱን አላቆመም። ተሸንፎአል፣ ደግሞም ኢየሱስ ባዳናቸው ላይ ሙሉ የሆነ ሀይል በፍጹም ሊኖረው አይችልም። የክርስትና ህይወታቸው በተቻለ መጠን አስቸጋሪ እንዲሆን በእነርሱ ላይ ግን ጦርነት ያደርጋል። ከዳግም ልደት በፊት ስለዲያብሎስ ምንም ተሞክሮ አልነበረንም ወይም በጣም ትንሽ ተሞክሮ ነው የነበረን። የእርሱ ነበርን ስለዚህም እኛን መዋጋት አያስፈልገውም ነበር። አንዴ ግን ደህንነት ወደ ሰው ከመጣ፣ ሲኦል ባጠቃላይ በቁጣ ይገነፍላል ደግሞም ዳግም በተወለደው ነፍስ ላይ ጦርነትን ያውጃል።

ክርስቲያን ከሆንክ ዲያብሎስ በአንተ ላይ ይነሳል፣ የሲኦል ሀይላትም ባንተ ላይ ይነሳሉ። አስፈሪ ትእይንት ነው። ስለዚህ ምን ማድረግ ይሻለናል? በፍረሀት አፈግፍገን እንመለስን? ለሁሉም ውጊያና ፈተና እንማረክን? በፍጹም፣ በርግጥ እንደዛ አናደርግም!

1ዮሐ 5፡18ን አንብብ ክፉው አንተን መንካት እንደማይችልም ተመልከት። ያዕ 4፡7 “ዲያብሎስን ተቃወሙት ከናንተም ይሸሻል” ብሎ ይነግረናል። የማርቲን ሉተር ታላቅ ቅኔ በዚህ መተማመን ላይ ያቃጭላል፡

ይህ አለም በሞላ ዲያብሎስ ነግሶበት ነበር

ሲቦጫጭቀን በመመልከት፣

በልባችን እጅግ ስፍራ አልሰጠነውም

ሊበረቱብን አይችሉም

የመከራ ንጉስ

ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አስፈሪ ይምስል

ቅንጣትም ያክል አይጎዳንም

በምን ምክንያት? ጥፋቱ ስለወሰነ

አንድ ቃል ፈጥኖ ያጠፋዋል

የራሳችን ሀይል ባይኖረንም፣ “በጌታና በሀይሉ ችሎት” መበርታት እንደምንችል በመገንዘብ (ኤፌ 6፡10) **ማድረግ ያለብን ነገር መዋጋትና ወጦርሜዳው መግባት ነው ። የጌታ ብርታት ለጨለማው ሀይል እጅግ ታላቅ እንደሆነ ተረጋግጧል። የታመነ ብርታት፣ የተረጋገጠ ብርታት ነው፤ ደግሞም በክርስቶስ የእኛ ነው።**

2. የጠላት ስልት

“የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ . . . “ (ኤፌ 6፡11)

ታሪክ በጦርነት የተሞላ ነው አንዳንዶቹ በጣም አጭር ሌሎቹ ደግሞ ረጃጅም። ክርስቲያኖች የሚዋጉት ጦርነት ግን የታሪክን ክፍል ብቻ ሳይሆን ሙሉውን ታሪክ ነው። በሰው ዘር ታሪክ የሆነው ሁሉም ነገር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የዚህ ጦርነት ክፍል ነው።

ይህ ጦርነት በእግዚአብሔርና በሰይጣን መካከል ነው። ጦርነቱ ለመግባትና ለማሸነፍ ክርስቶስ ወደ አለም መጣ ወደ ። ሐዋርያው ዮሐንስ “አለሙ ሁሉ በክፉ እንደተያዘ” “የዲያብሎስን ስራ ሁሉ ሊያፈርስ” ኢየሱስም ወደ ወደ አለም እንደመጣ ይነግረናል (1 ዮሐ 5፡19፤ 3፡8)።

ከቤተልሄም እስከ ቀራንዮ ድረስ ጦርነቱ ታውጇል። ኢየሱስ ሲወለድ ሰይጣን ነብዩን ንጉስ ሄሮድስን ተጠቀመ አዳኙን የመግደል መከራ ለማድረግ። ሰይጣን ተሸነፈ ክርስቶስ ድል አገረገ። ኢየሱስ የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር ሰይጣን በተከታታይ ፈተናዎች አዳኙን በሀጢአት ለመጣል ሞከረ። አንዴ እንደገና ክፉው ወደቀ። ብርቱ የሆነው ውጊያ በቀራንዮው መስቀል ላይ የተደረገ ነበር። በቆላ 2፡15 ላይ በመስበክ ቻርለስ ስፐርጅን ይህን ተጨባጭ ስዕል ፈጥሮልናል።

> አሁን የእግዚአብሄር ልጅ መነሳት እና ሰይፉን በጭኑ መሻጥ አለበት። አስፈሪ ፍርሀት ወይም የክብር ድል የቤተ ክርስቲያንን ሻምፒዮን ይጠብቃል። የትኛው ይሆን የሚሆነው? ወጀቡ እያንዣራ ነበር እኛም ጉጉት ባለው አጠባበቅም ትንፋሻችንን ይዘናል . . . . ሰይጣን በክርስቶስ ላይ ተነሳ፤ በእጁ በሀጢአት መርዝ የተነከረ ህግ የተባለ የተሳለ ሰይፍ ይዟል። ህጉ የመታው ቁስል ሁሉ ገዳይ እንዲሆን። ክርስቶስ ይህን ሰይፍ ከሰይጣን እጅ ሰበረው። ከዚያም የጨለማው ንጉስ ያለትጥቅ ባዶውን ቀረ። የራስ ቁሩ ለሁለት ተከፈለ ጭንቅላቱም በብረት በትር እንደተቀጠቀጠ ሆነ። ሞት በክርስቶስ ላይ ተነሳ። አዳኙ መውጊያውን ከእርሱ ነጠቀው፣ መወንጨፊያዎቹንም ከውስጡ አወጣቸ፣ ለሁለትም ቆረጣቸው፤ የተመረዘውን መውጊያ ከእርሱ አስቀርቶ ለሞት መልሶ የላባውን የመጨረሻ ጅራት ሰጠው የተዋጁትን በፍጹም እንዳያጠፋ። ሀጢአት ወደ ክርስቶስ መጣ፤

> ሀጢአት ግን ክፉኛ ተቆራርጦ ነበር፤ የሰይጣን ትጥቅ ተሸካሚ ሆኖ ነበር። ጋሻውም ተጥሎ ነበር በሜዳ ላይ ወድቆ ሞተ። የክርስቶስን ጠላቶች ለመረዳት አይነተኛ ስዕል አይደለምን? - በፍጹም፣ ወንድሞቼ፣ የናንተና የኔ ጠላቶች በፍጹም ትጥቃቸው ተፈቶአልን? ሰይጣን አሁን እኛን የሚዋጋበት ምንም ነገር አልቀረውም። ሊጎዳን ሊሞክር ይችላል ነገር ግን እኛን ማቁሰል በፍጹም አይችልም ። ሰይፉና ቀስቶቹ ሙሉ በሙሉ ተወስደዋልና።

የመጨረሻውና የተሟላው የክርስቶስ ድል የተደረገው፣ ትላልቆቹ የሰይጣን መሳሪያዎች፣ ሞትና መቃብር በክርስቶስ ድል በተዋጡበት፣ በትንሳኤው ነው። ይሁን እንጂ ይህ ማለት ጦርነቱ አብቅቷል ማለት አይደለም። የመጨረሻው ድል ተረጋግጦአል ውጊያው ግን እየተካሄደ ነው። አሁን ክርስቶስ በአካል በአለም ውስጥ አይደለም፤ ቤተ ክርስቲያን ግን አለች። ቤተ ክርስቲያን አካሉ ነች ህዝቡን የያዘች። ስለዚህ አሁን ሰይጣን ጦርነቱን በክርስተያኖች ላይ ነው የሚያካሂደው። ለዚያ ነው አሁን በጦርሜዳ ውስጥ ያለነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ዳግም በተወለደበት ጊዜ የእርሱ አገልግሎት ሀጢአተኞችን “ከሰይጣን ሀይል ወደ እግዚአብሄር” መመለስ እንደሆነ እግዚአብሄር ተናግሯል (ሐዋ ስራ 26፡ 18)። በከፊል ይህ የእያንዳንዱ አማኝ ስራ ነው። ሰይጣንም ይህ ሲደረግበት ዝም አይልም በሙሉ ሀይሉ ይዋጋል። ስለዚህ በመንፈሳዊ ስራዎች ውስጥ ይበልጥ ስንሳተፍ፣ ይበልጥ የዲያብሎስን ተቃውሞ እንረዳለን። የአትክልት ስፍራን ስትቆፍር ወይም ቲቪ ስታይ ወይም ጌም ስትጫወት ሰለጦርነቱ ምንም ወይም ትንሽ ይሆናል የምታውቀው ነገር ግን ለጸሎት ጉልበትህ ሲንበረከክ ወይም መጽሐፍ ቅዱስህን ስትከፍት ወይም ለማያምኑ መመስከር ስትጀምር ጦርነቱ እንደተጀመረ ታውቃህ።

በዚህ ተስፋ መቁረጥ ይገባናልን? በፍጹም፣ ምክንያቱም ኤፌ 6፡10 ለብቻችን እንዳልሆንን ይነግረናል። ሰልፉ የጌታ ነው ስለዚህም የመለኮት ሀይሉን ይሰጠናል። ይህን ፍጹም መርሳት የለብንም። የጦር ዕቃው የእግዚአብሄር ነው ደግሞም አይረቱ ነው። ሰልፉ የጌታ ነው እርሱም ሁሉን ቻይ ነው። አሁንም ግን በጦር ሜዳ ውስጥ ነን ለውጊያውም ራሳችን ማዘጋጀት አለብን።

ጠላትን እንወቅ

የመጀመሪያ ማወቅ ያለብን ነገር ጠላትን መገንዘብ ነው። ይህ ጦርነት መጥፎዎቹ ጥቁር ባርኔጣ ጥሩዎቹ ደግሞ ነጭ ባርኔጣ እንደለበሱበት እንደ ጥንቱ የካውቦይ ፊልሞች አይነት አይደለም። እዚያ ሁሉም ነገር ግልጽና የታወቀ ነው። የእኛ ውጊያ እንደዛ አይደለም ዲያብሎስ በዚያ መንገድ ስለማዋጋ። በኤፌ 6፡11 የዲያብሎን "ሽንገላ" ወይም "ማታለሎች" ያመለክታል በቅዱሳት መጻህፍት በሙሉ ስለዚህ ተስጠንቅቀናል። ጥበበኛ ነው (ዘፍ 3፡1) አታላይም ነው (2 ቆሮ 11፡3)፤ ሊያስተን ይፈልጋል (2 ቆሮ 2፡11) ወጥመድንም ይዘረጋል (1 ጢሞ 3፡7)፤ የውሸት ሁሉ አባት ነው (ሐ 8፡44) ተአምራትንም ሳይቀር ማድረግ የችላል (ማቴ 24፡24)።

ስለዚህ ክርስቲያን ምን ያህ ጠንቃቃ መሆን እንዳለበት ታያለህ። ጦርነቱ ሁልጊዜ ግልጽ አይደለም። አንዳንድ ጊዜም በርሱ ውስጥ እንዳለን ገና ሳንረዳ በውጊያው ልንሸነፍ እንችላለን። ስለዚህ ያለማቋረጥ ነቅተን መኖር አለብን። ንጹህና ጉዳት የሌለው በሚመስል ነገር ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ነው የእግዚአብሔር ህዝብ የሚገባው! ይህ በዲያብሎስ ማታለሎችና ጥበብ ምንያት ነው።

የጠላታችንን ድርጊት ለመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምት ቋንቋ በጣም ግልጽ ነው። አንዳንዴ "እንደሚያገሳ አንባሳ ይዞራል" በሌላ ጊዜ ደግሞ "እንደ ብርሃን መልአክ ይመስላል" (1 ጴጥ 5፡8፤ 2 ቆሮ 11፡14)። "የብርሀን መልአክ" ከሚያገሳ አንባሳ" ይልቅ የከፋ ነው ምክንያቱም የኋለኛው እንድትጠነቀቅ ሲያደርግህ ሌላኛው እንዳታውቅ ያደርግሃል። በሐዋርያት ስራ በክርስቲያኖች ላይ ሀይለኛ እና መራራ ስደትን እዲያስነሱ መጠቀሚያዎቹን እንደሚያገሳ አንበሳ ሆኖ ሲያነሳሳቸው እናያለን። አሁንም እንደዚህ ይሰራል። በተለያዩ መንገዶችም በእኛ ላይ ቀጥተኛ ጥቃትን ያስነሳል። እንደብርሃን መልአክ ሆኖ የምምጣቱ አይነተኛ ምሳሌ በዘፍ 3 የምናገኘው ሲሆን፣ ወደ ሄዋን በወዳጅነትና ግድ በተሰኘ ማንነት አሰምስሎ ይመጣል ቢሆንም ግን በእግዚአብሔር እውነት እና ባህሪ ላይ ጥርጥር ይወርውራል (ቁ 5)።

እውነታው

ጠላት እንደብርሃን መልአክ ሲመጣ፣ የእግዚአብሔር እውነት ነው ማንነቱን የሚገልጠው። ምንም ያህል በጥበብ ያስመስል ወይም አመጣጡ ምንም ያህል በዘዴ ቢሆንም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲገለጥ ሁልጊዜም ከእግዚአብሄር እውነት ጋር ይጋጫል። የእግዚአብሔር ቃል የሰይጣንን ሽንገላ የሚገልጥ መርማሪ ብርሃን ነው።

በኤፌ 6 ሁለት ጊዜ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን እውነታ እንደጠቀሰ ልብ በል። በቁ 14 “ስለእውነት ቀበቶ” እና በቁ 17 “ስለመንፈስ ሰይፍ” ስለ እግዚአብሄር ቃል ይናገራል። የእግዚአብሄር ጦር ይሄኛው ክፍል በጣም አስፈላጊ ነው ጠላት በፍጹም ከእግዚአብሄር ቃል እውነት ጋር ስለማይስማማ። በእርሱ ዘንድ ያለ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ስልጣን ላይ ያምጻል። አንዳንዴም እንኳን ሊያታልለን ሲፈልግ፣ አንድ ጊዜ የእግዚአብሄር መርማሪ ብርሃን የተገለጠ እውነት በእርሱ ላይ ከተነጣጠረ፣ ትክክለኛ ማንነቱ፣ የእግዚአብሄር ጠላት መሆኑ ይጋለጣል።

የዲያብሎስ ሽንገላዎች ብዙ ናቸው ይሁን እንጂ በጣም ዋና ዋናዎቹ በ3 ርዕሶች ሊከፈሉ ይችላሉ - ቅዱስ ያልሆነ ህብረት፣ የሐሠት ልምምዶችና የሐሰት ትምህርት። ከእነዚህ የትኞቹም አዲስ አይደሉም ዛሬ ዛሬ ግን በተለየ ሁኔታ መርዛማ ናቸው።

ቅዱስ ያልሆነ ህብረት

ለብዙ ሰዎች የኢኪዩሚኒካል እንቅስቃሴ ስራ እና የአንድ ቤተ ክርስቲያን እሳቤ በጣም መልካም ይመስላል። ይህንን ለመደገፍ አንዳንዴ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ቢጠቀሱም፣ እንዳለመታደል ሆኖ የኢኪዩሚኒካል እንቅስቃሴ አጠቃላይ ዝንባሌ ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ ትንሽ ወይም ምንም ክብር ነው ያለው። ጥቅም ላይ የዋለው ክርክር፣ ዶክትሪን እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ህዝብን እየከፋፈሉ ነው ስለዚህ ልንረሳቸው ይገባል የሚል ነው። ያቆሙት መሰረታዊው አመለካከት ከእውነት ይልቅ አንድነት ነው የሚያስፈልገው የሚል ነው።

ጥያቄው ይህ ከእግዚአብሄር ወይስ ከዲያብሎ ነው የሚል ነው? መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ አንድ የሚያደርገን ነገር እውነተ ብቻ እንደሆነ ይናገራል። በቃሉ በየስፍራው እግዚአብሔር የእውነት አስፈላጊነት ላይ ያጠነክራል። ኢየሱስ አምልኮ “በእውነትና በመንፈስ” መሆን እንዳለበት ይናገራል (ዮሐ 4፡24)። በመጨመርም እውነት እርሱ እንደሆነ (ዮሐ 14፡6) ከሀጢአት አስራትም ነጻ የሚያወጣን እውነት እንደሆነም ይናገራል (ሐ 8፡32)።

የክርስቲያኖች አንድነት በእግዚአብሄር እውነት ላይ ብቻ ነው መመስረት የሚለው። “አንድነት” እንዲሁ በተለመደው የቤተ ክርስቲያን ድርጅት ነው የተገኘው የሚል አስተሳሰብ መስጠት ስህተት ነው። እነዚህ ያልተቀደሱ ጥምረቶች በእነርሱ ላይ የእግዚአብሄር ቃል እንዲያበራ ሲደረግ የሚጋለጡ ከሰይጣን ሽንገላ ውስጥ አንዱ ናቸው (ሮሜ 16፡17-18፤ ቲቶ 3፡10፤ 2 ቆሮ 6፡14-18፤ ገላ 1፡6-9፤ 2 ዮሐ 7፡11)።

የሐሰት ተሞክሮዎች

ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ የእግዚአብሄር መንፈስ ታላቅ ልምምድ እንዳላቸው የሚናገሩ በሀይል በመደሰትም ስለምልክቶችና ድንቆች የሚናገሩ። እነዚህ ነገሮች ከእግዚአብሔር የሆኑ ትክክለኛ ነገሮች ከሆኑ ከእነርሱ ጋር ሀሴት ማድረግ አለብን። ነገር ግን መጠንቀቅ አለብን ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ዲያብሰሎም ምልክትና ድንቅ ማድረግ እንደሚችል ስለሚያስጠነቅቀን (ማቴ 24፡24)። ሙሴ ብቻ እንዳልነበር በትሮችን ወደ እባቦች ሲለውጥ የነበረው በፍጹም መርሳት የለብንም፤ የፈርኦን መተተኞችም እንዲሁ አድርገው ነበር (ዘጸ 7፡6-13)።

የዚህ የተለየ አደገኛ ውጤት እነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ቀጥታ መገለጥ ተቀበልኩኝ የሚሉት አበባል ነው። "እንዳደርገው እግዚአብሔር ተናገረኝ" ይላሉ። እንደዛ ሊሆን ይችላል ነገር ግን እግዚአብሔር ከራሱ ጋር እንደማይቃረን ግን አትርሳ። በቅሳት መጻህፍት የከለከለንን ነገር እንድናደርግ አይነግረንም። ለምሳሌ፣ አንድ ወጣት ከሴት ጓደኛው ጋር እንዲተኛ እግዚአብሔር እንደተናገረው ይናገራል። እግዚአብሄር እንደዚህ ያደርጋል ወይስ የዲያብሎስ ሽንገላ ነው? ከዚህ ጀርባ ማን እንዳለ የእግዚአብሄር ቃል በጥርጥር ውስጥ አልተወንም። ይህ ከመስመር የወጣ ምሳሌ ነው ብላችሁ መከራከር ትችላላችሁ። ተዛምዶው ጥግ የያዘ ሊሆን ይችላል መርሁ ግን እንደዛ አይደለም። በማይለወጥ በእግዚአብሔር ቃል አስቀድሞ ሳይመረመር ከእግዚአብሄር ቀጥተኛ መገለጥ ነው ማለት በጣም አደገኛ ነው።

ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ ከዚህ የተነሳ ለማስተማር አስቸጋሪ የሆኑ። ራሳቸውን ከእግዚአብሄር ቃል ስልጣን በላይ አድርገዋል። "በመጽሐፉ እስረኞች" ከመሆን እንድናቆም ተነግሮናል ደግሞም የዋናውን መጽሐፍ ቅዱስ ሽርጥ ማሰሪያዎች እንደንበጥስና በቀስታ ግን በመተማመን ወደ ሰማዩ አባታችን እቅፍ እንድንሄድ ተመክረናል። ይሄ ገዳይ ምክር ነው። መረዳቶቻችን በሀጢአት ጨልመዋል እንዲመሩን በነርሱ ላይ ከተደገፍንም፣ ወደ ስህተት እናመራለን ራሳችንንም ለዲያብሎስ ሽንገላ እናጋልጣለን።

የሐሰት ትምህርት

የዲያብሎስ ሽንገላዎች ቅዱስ ባልሆኑ ጥምረቶችም ሆነ በሐሰት ልምምዶች መልክ ይምጡ፣ በመጨረሻ ተመልሰው በሀሰት ትምህርት ተጽኖ ስር ይመጣሉ። የሀሰት አስተማሪ የታመነና እውነተኛ ሊሆን ይችላል የሚያስተምረው ነገር ከእግዚአብር ቃል ተቃራኒ ከሆነ ግን ኑፋቄ

ነው። የተማርነውና የምናምነው ነገር በጣም አስፈላጊ ነው። ዶክተር ማርቲን ሎይድ ጆንስ እንዲህ ይላል፣ “በዚህ የክርስትና ህይወት እና ውጊያ ለምትማራቸው የመጀመሪያ ነገሮች፣ በትምህርትህ ከሳትክ፣ በሁሉም የህይወትህ አቅጣጫ ትስታለህ”። ምናልባትም በተግባርህና በባህሪህ ልትስት ከቻልክ፤ በርግጥም በልምምድህ ትስታለህ። “

ስለዚህ እኛን ለማጥቃት ሰይጣን የተወሰነ መላ ሊጠቀም እንደሚችል መጠበቅ አለብን። የሐሠት አስተማሪን መለየት ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። አንድ ሰው የኢየሱስን አምላክነት፣ ደህንነት በጸጋ ብቻ መሆኑን፣ ትንሳኤንም የሐሰት አስተማሪ እንደሆነ ግልጽ ነው። ኢየሱስ ግን የበጎች ለምድ ከለበሱ ተኩላዎች አስጠንቅናል (ማቴ 7፡15)። የእነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ችግር የሚናገሩት ነገር ሳይሆን የማይናገሩት ነገር ነው። በሌላ አነጋገር፣ ብዙውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወንጌል ይተውታል።

> ከሐሰት ትምህርት በጣም የሚጠብቀን ነገር ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን በመጸለይ ከጥርጥር ሁሉ በላይ የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር ማጥናት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሃን እንዲሆን ነው (መዝ 119፡105)። በትክክል የሚያነበው ሰው ለስህተት ታልፎ አይሰጥም። መጽሐፍ ቅዱስን ችል ማለት ነው የሀሰት አስተማሪዎችን የሚሰሙትን ብዙዎችን አደን የሚያደርጋቸው የመጀመሪያ ነገር . . . በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የሚጸልይ ደስተኛ ነው ደግሞም በሀይማኖት ውስጥ ባለው እውነትና ውሸት መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል! ልዩነት አለ እርሱን ማወቅ እና እውቀታችንን መጠቀም አለብን።
>
> ጄ.ሲ. ራይል

ጉዳይ አስፈጻሚ

“መጋደላችን ከስጋና ከደም ጋር” እንዳልሆነ ጳውሎስ ይነግረናል (ኤፌ 6፡12)። ይህ ማለት ክርስቲያን እንደመሆናችን ሰዎች ሲቃወሙን አናይም ማለት አይደለም። ሁላችንም በብርቱ ሁኔታ ሀይማኖታችንን እና እምነታችንን የሚቃወሙ ጓደኞች፣ የስራ ባልደረቦች እና ቤተሰብ ተሞክሮ አለን ። እኛን በሚያጠቃ ጊዜ ሰዎችን እንደስራ አስፈጻሚ ይጠቀማል፤ የሚጠቀመውም አማኞችን ብቻ አይደለም። በእኛ በኩል ትልቅ ትጋትን ይጠይቃል የክርስቲያን

ወገኖቻችን እምነት ላይ ተጽኖ ለማድረግ ወይም ለሚያምኑት እንቅፋት እኛን ጠላት እንዳይጠቀም። ውጊያችን ከስጋና ከደም ጋር አይደለም ዲያብሎስ ግን ስጋና ደምን ይጠቀማል።

ከሀጢአትና ከስህተት ጋር ዲል ስናደርግ፣ ከጀርባው ያለውን ሀይል ፍጹም መርሳት የለብንም። ምንም የሀሰትን ትምህርት ብንጠላም እርሱን የሚያስተምሩትን ሰዎች እንዳንጠላ በጣም ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። ሀጢአትን መጥላት እና ሀጠኢተኛን መውደድ ከሚደረግ ይልቅ ሲነገር ይቀላል ነገር ግን በጣም አስፈላጊ ነው። ከጉዳዩ እንድንወሰድ እና ይልቁንም ስብዕናን ለማጥቃት ለራሳችን ስንፈቅድ በዲያብሎስ እጅ መጠቀሚያ በመሆን ትልቅ አደጋ ውስጥ ነን።

3. የእኛ ብርታት

“በጌታና በሀይሉ ኀይሎት የበረታችሁ ሁኑ” (ኤፌ 6፡10) ውጊያው በጣም እውነተኛ ነው። ጽኑ አንዳንዱም አሳችና በጣም ግራ አጋቢ ነው። ይበልጥ ስለርሱ ስናስብ ድል መንሳቱ ቀርቶብን እንዴት እንደምንተርፍ እንኳን ይጨንቀናል። ትልቅ ሠራዊት ወደ እርሱ ሲቀርብ ሲያይ ወደ እግዚአብሄር በመቅረብ ይህንን ትልቅ ሠራዊት ለመግጠም ሀይል የለንም . . . ምን እንደምናደርግ አናውቅም” (2 ዜና 20፡12) ካለው ከይሁዳ ንጉስ ከኢዮሳፍጥ ጋር ማዘን ይቀላል። ኢዮሳፍጥ ግን እዛ ላይ አላቆምም፣ አይኖቻችን በአንተ ላይ ናቸው” ማለትን ቀጠለ። በእግዚአብሄር ላይ ነበር መታመኑ “ውጊያው የእግዚአብሄር ነው እንጂ የናንተ አይደለም” በማለት ጌታም ያንን መታመን አበረታ (ቁ 15)። ጸንቶ ለመቆም ተበረታታ ተስፋም አልቆረጠም ምክንያቱም “ጌታ ከእናንተ ጋር ይሆናል” ተብሎ ማረጋገጫ ተሰቶታልና (ቁ 17)።

ሰልፉ የጌታ ነው ደግሞም የእርሱ ህዝብ ስለሆንን ነው ወደ ሰልፉ የገባነው። ይህ ማለት ቀላል ነው ወይም እኛ እንቆማለን እግዚአብሄር ይገባበታል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ አይዋጋም፤ እኛ መዋጋት አለብን ግን በእግዚአብሔር ብርታት። መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ “አንተም እግዚአብሄርም ተዋጉ” አይደለም ይልቁን “በጣም ጸልይ ደግሞም ተዋጋ” ማለት ነው። ለእያንዳንዱ ሽንገላ፣ ለእያንዳንዱ ፈተና ፣ ከእግዚአብሄር የሚሰጥ ብርታትና ሀይል አለ እኛ ግን እርሱን መጠቀም አለብን። አንዳንድ ጊዜም እግዚአብሔር በቀጥታ ጣልቃ ይገባል፤ እነዚያ በጣም አስደሳች ልምምዶች ናቸው ነገር ግን እርሱ ራሱ ያስቀመጠውን መርህ ግን አያፈርሱም። በኤፌ 6 ያለውን የዚህን ክፍል ሙሉ አጽኖት እግዚአብሄር ነው የሚሰጠን። ነገር ግን ይህንን በህይወታችን እንዴት ነው የምንተገብረው?

ውጊያ

በጦር ሜዳው ለመግባት አትፍራ። ውጊያው ብርቱ መሆኑ እና አንተም እንደምትመታና እንደምትቆስል ጥርጥር የለውም። ጠባሳዎች ሊቀሩ ይችላሉ ግን በዚህ መፍራት የለብንም። አንዳንድ ክርስቲያኖች የጦርነት ድምጽ ይሰማሉ፤ የሞት አደጋን ያያሉ ይሮጣሉም። ያ በራሱ ግን ሽንፈት ነው። ሰይጣንን ሳናቃወመው ገሰገሰ ማለት በክርስቶስ ላይ ያለንን መታመን መካድ ነው። ያቆ 4፡7 ዲያብሎን ተቃወሙት ነው የሚለው። ሩጥ ሳይሆን ተቃወመው ነው። ጠላት ዘልቆ ሲገባ ተጋፈጠው።

በኤፌ 6፡12 ጳውሎስ ስለ “መጋደላችን” ወይም እንደ ንጉስ ጀምስ ትርጉም ስለ “ትግላችን” ጳውሎስ መናገሩን ልብ በል፡፡ ትግል አካላዊ ንክኪን ያካትታል - እጆች፣ እግሮችና አካላት በመጋጠም ውስጥ ይያዛሉ፡፡ ጦርነት እንደዛ ነው፡፡ ሌላ ማንም የማይገባበት የግል ጉዳይ ነው፡፡ ሰይጣን ያጠቃሃል አንተ ትቃወማለህ፡፡ ይህ መንፈሳዊ ትግል ነው፡፡

መሮጥ ሳይሆን መቋቋም አለብን ካልን፣ አንዳንድ ጊዜ የመቃወም የላቀው መንገድ መሮጥ እንደሆነም መነገር አለበት፡፡ ይህ እርስ በርስ የሚቃረን ይመስላል እውነታው ግን ያ አይደለም፡፡ እንዳየነው ዲያብሎስን መቃወም ማለት መዋጋት እንጂ መተውና እንዲያሸንፍ ማድረግ አይደለም፡፡ አሁን የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አስተውል፡፡

1 ቆሮ 6፡18 “ከወሲባዊ ርኩሰት ሽሽ”

1 ቆሮ 10፡4 “ከጣኦት አምልኮ ሽሽ”

1 ጢሞ 6፡11 “ከዚህ ሁሉ ሽሽ

1 ጢሞ 2፡22 “ከጎልማሳነት ምኞት ሽሽ

በእነዚህ ሁሉ ክፍሎች፣ “መሸሽ” ማለት መቃወም፣ በነዚህ በተወሰኑ ሀጢአቶች አለመያዝ ማለት ነው፡፡ በ1 ጢሞ 6፡11 “ከዚህ መሸሽ” የሚለው ትእዛዝ ወዲያውኑ “መልከሙን ገድል በእምነት ተጋደል “ በሚል ተተክቷል (ቁ 12)፡፡ እነዚህ ሁለት ትዛዛት ተመሳሳይ ናቸው፡፡

አስታውስ

ማንና ምን እንደሆንክ አስታውስ፡፡ ለሀጢአት ባሪያ ነበርክ አሁን ግን አይደለህም (ሮሜ 6፡6)፡፡ በሀጢአትና በተፈጥሮ ምሽት ተጠርቀህ ታስረህ ነበር አሁን “በክርስቶስ” ነህ፡፡ ያም ማለት “ሻሸናፊዎች በላይ ነህ” ማለት ነው (ሮሜ 8፡37)፡፡ ብርታት የሚመጣው ክክርስስ ነው፡፡ በእርሱ ብቻ ነው አሸናፊ የሆንከው፤ በራስህ የሰይጣን እኩያ አይደለህም፡፡ ራስህን በቦክስ ቀለበት ውስጥ የአለምን ከባድ ክብደት ካለው ሻምፒዮንጋር ስትጋጠም ማሰብ ትችላለህን? ሁኔታው ተስፋ የለሽ ነውን? ይህንን ሻምፒዮን በ100 አለቃው ታንክ ሆነህስ ቢሆን የተጋጠምከው ? ከባላጋራህ ጋር ስትወዳደር ያው ደካማ ነህ፣ አሁን ግን ሁኔታው ተስፋ የለሽ አይደለም፡፡ በክርስቶስ ከመሆን ሚመጣ ጥንካሬ አለህ፡፡

“በክርስቶስ” ከመሆን ጋር ይህ የሚወዳደር ነገር አይደለም፡፡ በእርሱ ከአሸናፊዎች በላይ ነህ፡፡

እግዚአብሔርን እወቅ

“አምላካቸውን የሚያውቁ ህዝብ በጽናት (ጠላታቸውን) ይቃወማሉ (ዳን 11፡32)። ትልቁ ብርታትህ እዚህጋ ነው። ይበልጥ እንበረታለን። ያዕቆብ “ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል” ብሎ ይነግረናል (ያቆ 4፡7)። ይህንን ጥቅስ ልብ በል ደግሞም ከነዚህ አጽናኝ ቃላት በፊት “ለእግዚአብሄር ተገዙ” በመቀጠልም “ወደ እግዚአብሄር ቅረቡ” ተብለናል።

ራሳችንን ለእግዚአብሄር ስናስገዛ፣ ወደርሱ ስንቀርብ እና በውበቱ እና በግርማው እርሱን ስናወቀው ብቻ ነው በውጊያ ድል የምናገኘው። ጎልያድን ሲጋጠም የዳዊት ብርታት ይህ ነበር (1 ሳሙ 17፡37፣ 45-47)። እምነታቸውን ለማጥፋት ሐዋርያት መራራ የሚቃወም አለም ገጠማቸው፤ የምርና ቀጣይነት ያለው የእግዚአብሄርን ህልውና ማወቅ ነበር ያበረታቸው (ሐዋ ስራ 4፡19፣31)። በእኛም ዘንድ ያለ ይኸው እግዚአብሄርን ማወቅ ነው ብቸኛው ተስፋችን ከዲያብሎስ ጋር ስንዋጋ።

> ይህንን መልእክት ለማብራራት (ሀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ) በሚለው ቃል የሰበክ የሚማርክ የኩዌንት ሽማግሌ ሰባኪን ታሪክ ልንገራቸሁ ። መልእክቱን ወደ ጉባኤው ዘልቆ ለማስገባት በዚህ መልክ አስቀመጠው። “ሁሉን ማድረግ እችላለሁ” የሚሉትን ቃላት አነበበ - ለአጭር ጊዜ አቆመና ለሐዋርያው በነዚህ ቃላት ይህንን ጥያቄ አስቀመጠ ፡ “ጳውሎስ በጣም ያበዛኸው አልመሰለህም?” ሁሉን ማድረግ እንደምትችል በርግጥ ትናገራለህን? ማድረግ የማትችለው ነገር የለምን ? በውኑ እንዚህን ሀየልትና ስልጣናት መዋጋት ትችላልለህን? ከዲያብሎስ ጋር እኩል ነህን ? እንደ እግዚብሔር ወዳጅ እንደ አብርሀም ባሉ ሰዎች ላይ እንኳን ሳይቀር በአባቶች ላይ ያደረገውን ተመለክት። ዲያብሎስ አብርሃምን አሸንፎታል “ሁሉን እችላለሁ” ስትል ከእነርሱ እበልጣለሁ እያልክ ነውን? ሽማግሌው ሰባኪ ለጥቂት ጊዜ በዚህ መልክ ቀጠለ ችገሮቹን እያነሳየና ሐዋርያውን ጥያቄዎች እየጠየቀ። ከዚያ ግን ሙሉውን ክፍል ማንበቡን ቀጠለ፣ “በሚያስችለኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።” “ አ ጳውሎስ ይቅርታህን እጠይቃለሁ፣ ጳውሎስ” ይላል ሽማግሌው ሰባኪ፣ “ሁለታችሁ እንደሆናችሁ አላወኩም ነበር!” ይላል። አንድ ብቻ እርሱም ሐዋርያው ጳውሎስ እንደነበር ስእል እየሰጠ ነበር። በርግጥ ያ አጽኖት መስጠጥ ያስፈልገው ነበር፤ “እኔ” ይላል ጳውሎስ፣ “ሁሉን ነገር ማድረግ እችላለሁ” ይላል። ሁሉን ነገር “በሚያስችለው በክርስቶስ” ብቻ ነበር የቻለው። ክርስቶስ እያበረታው ነው፣ ወደርሱ ሀይል እየጨመረ ነው፣ ግን ጳውስ ነው ሁሉንም ነገሮች የሚያደርገው። እርሱ ነው ሁሉንም ነገር አሳልፎ አልሰጠም ደግሞም ቁጭ ብሎ ተመልካች አልነበረም ዝም ብሎ “እየታዘዘ”። ተሳትፎአል እነዚህን ነገሮች ሁሉ የሚያደርገው እርሱ ነው። ነገር ግን የዚህ ክብር እነዚህን ሁሉ “ሁሉን

በሚያደርግልኝ" ሳይሆን ነገር ግን በሚያበረታኝ በክርስቶስ ማድረግ ችያለሁ። ደምን እንደማስተላለፍ አይነት ነው፣ ሀይል ወደእርሱ ተቸምሮአል እርሱ ብርቱ ተደርጓል። ስራዎቹ ከእጆቹ አልተወሰዱም ነገር ግን ሊያደርጋቸው ችሎአል ምክንያቱም በዚህ መንገድ ብርቱ ተደርጓል።

ዲ.ኤም. ሎይድ - ጆንስ

እግዚአብሔር ሁለቱንም የጦር እቃውንም ብርታቱንም ይሰጣል፣ ይህንም የሚያደርገው ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ነው። ሁላችንም አንድ አይነት ምንጭ ካለን ታዲያ ለምድን ነው አንዳንድ ክርስቲያኖች የእምነትን ውጊያ ተዋግተው ድል ሲያገኙ ሌሎቹ ምንም የማይዋጉት? ሲዋጉም በጦርነቱ መቀት እንደቸኬት ወታደሮች የሚቀልጡት? መልሱ ከምንም ነገር በላይ ወታደሮቹ ሁለት አሰፈላጊ ብቃቶች ያስፈልጉአቸዋል የሚል ነው፡ ራስን መግዛትና ጽናት።

ራስን መግዛት

የጦር እቃው አለ ግን መለበስ አለበት። በራሱ አይለበስም እግዚአብሔርም አያለብሰንም። ጳውሎስ በኤፌ 6፡11 እንደገናም በቁጠር 13 በጣም ግልጽ ነው። ትዛዙም ግልጽና ጠንካራ ነው፡ "የእግዚአብሄርን እቃ ጦር ሁሉ ልበሱ"። ይህ የዲሲፕሊንና በርግጥም የመታዘዝ ጉዳይ ነው።

የትኛውም ሠራዊት ያለ ዲሲፕሊን ተግባር አይፈጽምም። ጦርነቶች ድል የሚነሱትና የሚሸነፉት በአንድ ወይም በሁለት ሰዎች በኩል የጀግንነት ታላቅ ስራ አይደለም ነገር ግን እሱን በማከናወን ጊዜ በጄኔራሎች እቅድና ስልት እንዲሁም በወታደሮች ዲሲፕሊን ነው። ስለዚህም፣ ሠራዊቱን ሲቀላቀል አንድ እጩ ወታደር የሚማረው የመጀመሪያው ነገር ዲሲፕሊን ነው። በመሠረታዊው ሥልጠና መታዘዝን ለመማር ብዙ ጊዜ ያጠፋል። "የአደባባይ ሰልፍ" ተብሎ በሚጠራው በሰልፉ አዳባባይ ላይ ሰኣታት ይጠፋሉ። ፈጣን ጉዞ፣ ወደቀኝ ታጠፍ፣ ወደግራ ታጠፍ፣ ቀኝ ኃላ ዙር ፣ መሳሪያን አጋድለህ ያዝ፣ በመሬት ላይ ተኝተህ መሳሪያን አነጣጥረህ ያዝየሚለውን ያለማመንታት እስሚታዘዝ ድረስ ትዛዞች በፍጥነትና በችኮላ ይመጣሉ። በየትኛውም የጦርነት አይነት ውስጥ ዲሲፕሊን የህይወትና የሞት ጉዳይ ሊሆን ይችላል። በ2ኛው የአለም ጦርነት ጊዜ የጠላት አየሮች ሲቀርቡ፣ የማስጠንቂያ ደወሉ ጮኸ፣ ወደ አየር ላይ የቦምብ ጥቃት ጊዜ መጠለያዎች የመሮጥ ፈጣን የዲሲፕሊን ምላሽ ብዙ ህይወቶችን አድኖአል። ተመሳሳይ ዲሲፕሊን እያንዳንዱን ሰው የጋስ ማስክ እንዲይዝ

አድርጎአል። የጋስ ቦምብ ጥቃቶች ቢኖሩ ኖሮ ክልያዝከው የዚህ መከላከያ ጥቅም ምን ድን ነው?

ከስgaና ከደም ጋር ለመዋጋት ይህ አስፈላጊ ከሆነ፣ በቁ 12 ላይ የተገለጠውን ጠላት ስንዋጋ እንዴት ይበልጥ አያስፈልገንም! ጳውሎስ ለጢሞቴዎ ያለ ዲሲፕሊን የድል ተስፋ እንደሌለ ይነግረዋል (1 ጢሞ 4፡7-8)። "እግዚአብሄርን ለመምሰል ራስህን አስለምድ" ብሎ ይመክረዋል።

ያንን እያደረግህ ነውን? አንድ አትሌት በአካላዊ ስልጠናው ጊዜ ትልቅ ዲሲፕሊን ያስፈልገዋል፣ ክርስቲያንም እንደዛው ለሁለቱም፣ ለጦርነቱ ለመዘጋጀት እንዲሁም በጦርነቱ ጊዜ ሁሉ። በሚከተሉት አቅጣጫ ክርስቲያን ዲሲፕሊንድ መሆን አለበት፡

ሀ) ጊዜን የመጠቀም ዲሲፕሊን። ምንያህል ጊዜአችን ነው የባከነው፣ ደግሞስ መንፈሳዊ ነገሮችን ከመለማመድ ይልቅ ተራ ለሆኑ ነገሮች ምን ያህል ጊዜ እንሰጣለን!

ለ) የጸሎት ዲሲፕሊን። ጸሎት ቀላል ነገር አይደለም ስለዚህም ብዙ ክርስቲያኖች ትንሽ ይጸልያሉ። እግዚአብሄር ከሰጠን የከበሩ ነገሮች መካከል ይህ አንዱ ነው። በጦርነት ውስጥ በጣም የጎላው ስፍራ ነው፤ ስትጸልይም ዲያብሎስ ሊረብሽህ በሀይል ይመጣል። ስለዚህ እጅ ላላመስጠት ዲሲፕሊንና ጽናት ይጠይቃል። አንዳንድ አማኞች ይህን አይረዱም፤ ጸሎት ሁልጊዜ ቀላል መሆን እንዳለበት ያስባሉ፣ አስቸጋሪ ከሆነ ይተውታል። ይህ የዲያብሎስ ምክር ነው። የእግዚአብሄር ቃል በጸሎት እንድንጋደል፣ እንድናምጥና እንድንታገል ይናገራል - የጦርነቱ በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው።

የፀሎት ህይወትህ ዲሲፕሊንድ ነውን? ጊዜና ጥረት ለእርሱ ትሰጣህን? የቤተ ክርስቲያንህ የጸሎት ጊዜስ? ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ስለሆነ መካፈልን አቆመህልን? በድጋሚ ይሄ የሰይጣን ምክር ነው። እግዚአብሔር እንድንጸለይ ይነግረናል። ለብቻህ ጸልይ፣ ከሌሎች ክርስቲያኖችም ጋር ጸልይ።

ሐ) የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዲሲፕሊን። የጦር እቃው የመጀመሪያው ክፍል እውነት ነው። እውነትን እንዴት እናውቃለን? የእግዚአብሄርን ቃል በማንበብና በማጥናት ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ብቻ በቂ አይደለም፣ እሱን ለማጥናት ጊዜ መስጠት አለብን። "የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" (2 ጢሞ 2፡15)

ትጥቁ መለበስ አለበት፣ በዲሲፕሊንና በመታዘዝ ነው የምናደርገውም። በጠዋት ከአልጋህ ስትነሳ፣ ልብስህን የምትለብሰው እንዴት ነው? ልክ እንደ መንፈሳዊቷ ሜሪ ፖፒንስ እያንዳንዱ ነገር በስፍራው ላይ እንዲሆን በመጠበቅ ዝም ብለህ ትቆማለህን? በርግጥ አትጠብቅም። የተለያዩ ልብሶችን መልበስ አለበህ። የእግዚአብሄር የጦር ዕቃም እንዲሁ ነው - ልበሰው።

መጽናት

ሙሉውን ትጥቅ ስንለብስ ጸንተን እንቆማለን እንበረታለንም ጠላት ወደ እኛ የሚወረውረውንም ነገር መቋቋም እንችላለን። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ያበረታታዋል "እንደ በጎ ወታደር . . ." (2 ጢሞ 2፡3)። መጽናት ማለት ብርቱ ሆኖ መቆየት ማለት ነው። ብዙ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ጉዞአቸውን እንደ ፈንድሻ ጠርሙስ ወደላይ በመፈናጠር ይጀምራሉ፣ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ወዲያውኑ እንደጠርሙስ ውሃ ዝም ይላሉ። ብርታትና ጸንቶ መቆም ያቃታቸው ለምንድ ነው? ሊሆን የሚችለው መልስ የእግዚአብሄርን የጦር ዕቃ ሁሉ አለመልበሳቸው ነው።

ዊንድሰር ካስልን ጎብኝተህ የምታውቅ ከሆነ፣ የሄንሪ 3 ኛን ትጥቅ ማየት ችለሀል። ግዙፍ ሰው ነበር በተለየ ሁኔታ ለእርሱ የተሰራ ሙሉ የትጥቅ ልብስም ነበረው። ይህንን ለብሶ መጠቃት አይችልም ነበር ይባላል። ሄንሪ 3ኛን የራስ ቁሩን ለብሶ ጋሻና ሰይፉን በእጁ ይዞ ነገር ግን የሌሊት ጋውን ለብሶ ወደጦርነት ሲሄድ ማሰብ ትችላለህን? በርግጥ አታስብም፤ ያ የማይታሰብ ነው የሚሆነው። ብዙ ክርስቲያኖች ግን ያንን ነው የሚያደርጉት። ስለዳንክ ብቻ እንዲሁ አትቆምም፤ ወይም ለእውነት፣ ለእምነት ወይም ለጸሎት ትልቅ ፍላጎት ስላለህም ብቻ አትቆምም። እውነት ወይም እምነት ወይም ጸሎት ሳይሆን እውነት እና እምነት እና ጸሎት ሁሉም ያስፈልጉሃል። በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የማይናወጡ ክርስቲያኖች አሉ፣ እንደ ጌታ ወታደር ግን አያገለግሉም ምክንያቱም የጸሎትን ትክክለኛ ቦታና ዋጋ አያውቁም። ተቃራኒውም እውነት መሆን ይችላል። በጸሎት ላይ ብርቱ አጽኖት መስጠትና ለእርሱ ጊዜ መስጠት ነገር ግን በጦርነት ትንሽ ብቻ ወይም ምንም አለማከናወን ይቻላል። ምክንያቱም እንዲህ ያሉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ችል ስለሚሉ ነው፣ በሰይጣን ሽንገላ በቀላሉ ይታለላሉ። ብቸኛው የመቆም መንገድ ሙሉ ትጥቅ መልበስ ነው።

ብርታታችን ከእግዚአብሄር ነው ደግሞም እርሱ የሚሰጠው የጦር ዕቃ ያስፈልገናል።

4. የእውነት ቀበቶ

“እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ ቀሙ” (ኤፌ 6፡14)

የጳውሎስ ጊዜ ግሩም ወታደሮች ያለጥርጥር የሮማን ሠራዊቶች ነበሩ። የሚታወቀውን አለም ድል ነስተው ነበር። ሐዋርያው በጉዞዎቹ በብዙ ስፍራዎች እነዚህን ወታደሮች በቅርብ አደባባዮች ተመልክቷቸዋል (ሐዋ ስራ 21፡30-37፤ 23፡23-24)። ትጥቃቸውን ስለዚህ በጣም ያውቅ ነበር። በኤፌ 6ም ይህንን ይጠቅሳል ለመንፈሳዊ ጦርነት ለክርስቲያን ወታደር ያለውን መሳሪያ ለማስረዳት።

እዚህ የተገለጹ 6 መሳሪያዎች አሉ። በጳውሎስ ትምህርት ውስጥ ድንገተኛ ነገር ኖሮ አያውቅም፤ ሲዘረዝር የነገሮቹ ቅደም ተከተል አስፈላጊ ነው፣ የእግዚአብሄርን የእቃ የጦር ዕቃ በተመለከተም ይህ እውነት ነው።

በእውነት ቀበቶ እንጀምራለን በወገብ ዙሪያ በሚታሰረው። የዚህ ቀበቶ ተግባር ምንድን ነው? በአንደኛው ክፍለ ዘመን አንድ ወንድ ወደታች የሚወርድ ረጅም ልብስ ይለብሳል - የድሮ ፋሽን የማታ ፒጃማ የመሰለ። በእንደዛ አይነት ሁኔታ ለመሮጥ ወይም ለመዋጋት መሞከር የማይቻል ይሆናል። ሰውየው በእርሱ ይጠለፋል፤ በእግሩ ላይ ምቾት አይሰማውም፤ ይሄ ደግሞ ግልጽ የሆነ አደጋ አለው። ስለዚህ በቀበቶ መታጠቅ አላማው ረጅምና የሚወርደውን ልብስ ለመሰብሰብና አንድ ላይ ለማሰር ነው፣ ሰውየውንም ለእንቅስቃሴ ነጻ ያደርገዋል። ስለዚህ መሳሪያ መጀመሪያ ላይ ማብራራቱ ግልጽ ይሆናል፤ ለስራ ዝግጁ ካልሆንክ፣ ካልተሰናዳህ፣ ተዝረክርከህ ትያዛለህ።

ይህን ከዲያብሎስ ጋር ካለን መንፈሳዊ ጦርነት ጋር ምን ያገናኘዋል? ጳውሎስ እውነት የመጀመሪያው አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ያስረዳል በዚህም ላይ ነው የሌላው ነገር ሁሉ ጠቃሚነትና ውጤታማነት የሚመሰረተው። አንዳንድ ሰዎች “እውነት” የሚለው ቃል እዚህ ላይ እውነተኛነት ወይም ታማኝነት ይመስላቸዋል። ትርጉሙ ይሄ ሊሆን አይችልም። የዚህ ትጥቅ እያንዳንዱ አይነት በእግዚአብሄር የተሰጠን ሆኖ ሳለ ታማኝነት ወይም እውነተኛነት ራሳችን የማናመጣው ነገር ነው። በጦርነት ጊዜ በዋናነት በራሳችን እውነተኛነት የምንደገፍ ከሆነ፣ በርግጥ ለውድቀት ተዘጋጅተናል። እንደዛ አይደለም፣ እዚህጋ “እውነት” ማለት የእውነት እውቀትና እምነት ማለት ነው። ይሄ ለጌታ ወታደር የመጀመሪያና የግድ ነው። ጠላትን ግራ

በተጋባና ጥርጥር በሞላው አእምሮ መጋጠም በብርቱ ጠላት ፊት በመንፈስ መሸመድመድ ነው።

> መታጠቂያ (ቀበቶ) ጥንካሬንና ለመንቀሳቀስ ነጻነትን፣ ብሎም መተማመንን እንደሚሰጥ ሁሉ፣ በመንፈስ ሲረዱትና ሲታመኑት እውነትም እንደዛ ያደርጋል። አእምሮው በራሱ ጽንሰ ሀሳቦችና ወይም በሌሎች ሰዎች ግምቶች ከተሞላ፣ የጨለማን ሀይላት ጥቃቶች ለመቋቋም እንደተዘጋጀ ማንም ሰው ማሰብ የለበትም። የእግዚአብሄርን እውነት በግልጽ ሲረዳና በዛው መሰረት ሲኖርበት ብቻ እንጂ በእነዚህ በሰማይ ሀይላት ፊት ለቅጽበት እግሩን ማቆም የሚያስችለው ሌላ ምንም ነገር የለም። አመክንዮ፣ ወግ፣ ግምታዊ መረዳት የሸረሪት ድር መታጠቂያ ናቸው። በመጀመሪያው ግጥሚያ ላይ ያበቃሉ። በመለኮታዊ እውቀት መልክ ስንታዘዘው እውነት ብቻ በክርስቲያን የየእለት ህይወት ውጊያዎችም ጭምር፣ በየትኛውም "በክፋ ቀን" ደግሞ የበለጠ ጥንካሬን ወይም መተማመንን ሊሰጥ ይችላል።
>
> *ቻርለስ ሆጅ*

ቀበቶው የሚወክለው በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያልበቃ መተማመንን ነው። ይህ የሁሉም ነገር መሠረት ነው። በክፍሉ ዝቅ ብሎ (ቁ 17) ጳውሎስ ይህ እውነት እንዴት ጥቅም ላይ መዋል ባለበት ጉዳይ ላይ ዲል ያደርጋል፤ እዚህ ላይ ግን እውነት ራሱን ነው ፊታችን የሚያቀርበው።

መጽሐፍ ቅዱስና ሳይንስ

ኢየሱስ የእግዚአብሄር ቃል እውነት እንደሆነ ይነግረናል (ዮሐ 17፡17)። ይህንን ማመን አስፈላጊ ነው ለዚህም ነው ዲያብሎስ ቅዱሳት መጻህፍትን ማጣጣል ለመሞከር ብዙ ጊዜ የሚያጠፋው። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ከተወለደችበት ጊዜ አንስቶ ሰይጣን በዚህ መንገድ እያጠቃት ነው። በ2 ኛው ክፍለ ዘመን በጣም ታማኝና እውነተኛ የሆነ ማርሲየን የተባለ ሰው በክርስትና ዋና ወደመሆን መጥቶ ነበር፤ ነገር ግን ብሉይ ኪዳንንደ በሙሉ እና ከአዲስ ኪዳንም የሚበዛውን ውድቅ አደረገ። ከጳውሎስ 10 መልእክቶችና ከሉቃስ ወንጌል በቀር። እነዚህንም ከራሱ የተለዩ ዶክትሪኖች ጋር እንዲስማሙ አመሳሰላቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋር በሚል በተባባሰ ክርክር የእግዚአብሄርን ቃል ማጥቃት በዚህ በአሁኑ ክፍለ ዘመን ተባብሷል፤ ይህም ደግሞ ጥቂት ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት

ላይ እምነት እንዲያጡ አድርጓቸዋል። ይህ ግን አያስፈልግም። በፍጹም ሳይንስ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክል አይደለም ማለት አይችለም። ችግሩ ብዙ ጊዜ ሳይንስ አሁን በአዲስ ሳይንሳዊ "እውነታዎች" ውድቅ ተደረገ በሚል ዛሬ ያመነውን ነገር ነገ ይጥለዋል ። ለምሳሌ ክርስቲያኖች የመጀመሪያዎቹን 5 የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሙሴ እንደጻፋው ያምናሉ። አንዴ ያ የማይሆን ነው ጽሑፍ በሙሴ ጊዜ አልተጀመረም ነበር ይላል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ግን አርኪኦሎጂስቶች ከሙሴ በፊት ብዙ ጊዜ አስቀድም በሺ የሚቆጠሩ ጽሁፎችን አግኝተዋል። አሁን በእርሱ ጊዜ ቢያንስ 6 የተለያዩ የተጻፉ ቋንቋዎች እንደነበሩ ታውቆአል።

> የምሁራን ውጤቶች መጽሐፍ ቅዱስን ውድቅ ከማድረግ ይልቅ እውነተኛነቱን ነው የሚያረጋግጡት። በርግጥ ስህተት የማይገኝበት መሆኑን አይረጋግጡም። ያንን ለማድረግም ሁሉም የሚያስፈልጉት ዳታዎችም ምናልባት አይኖሩንም። ነገር ግን በተአማኒነት አቅጣጫ ያመለክታሉ ደግሞም ከመጽሐፍ ቅዱስ ከፍተኛ አመለካከት ጋር የሚጋጭ ነገር አይገልጡም። ታይም መጋዚን ሳይቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ይህንን በሽፋን ታሪክ ላይ እውቅና ሰቶአል (ዲሴምበር 30፣ 1974)፤ "ለመሸከም የሚቻሉ፣ ከባድ ሳይንሳዊ ሽጉጦችን ከተጋጠመ ከሁለት ክፍለ ዘመናት በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ መኖር ችሏል- ለከበባው ምናልባትም የተሻለ ነው። በተቺዎቹ የገዛ ስያሜ - ታሪካዊ እውነት- መጽሐፍ ቅዱስ ሀሳባውየን ጥቃት ከጀመሩበት ጊዜ ይልቅ አሁን የበለጠ ተቀባይነትን ያገኘ ይመስላል ።"
>
> በእግዚአብሄር ቃል ላይ ጸንቶ ለመቆም ማንም ክርስቲያን መፍራት የለበትም። አንዳንድ ጊዜ ጽንሰ ሃሳቦች ሊገዳደሩት ይችላሉ። ክርክሮቹ ሊመለሱ የማይችሉ ይመስላሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስም የሚመራ ሞኝ ተብሎ ሊጠራ ይችላል። የአለም ጠቢባን፣ "ከፈለግህ ያንን ተራ ነገር ማመን ትችላለህ" ሳይንስ ግን የተሻለ ያስተምራል ይላሉ።" ይህ በፊትም ሆኗል እንደገናም ይሆናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ጸንቶ የሚቆም ክርስቲያን ግን በህይወት ዘመኑ ሁሉ፡ በምሁራን "የተረጋገጡ ውጤቶች" ሲፈራረሱ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና በታሪካዊቷ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በታመነው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መረዳት ጸንቶ ይኖራል።
>
> *ጀምስ ሞንትጎሜሪ ቦይስ*

ስልጣን

"የእውነት ቀበቶ" ስልጣናችን ምን እንደሆነ ያረጋግጥልናል። በጦርነቱ ምንነትና በጠላት ባህሪያት ምክንያት ይህ በጣም አስፈላጊ ነው ። ዲያብሎስ "ውሸታም ደግሞም የሀሰት አባት ነው" (ዮሐ 8፡44)፣ ውሸትን የመዋጊያ ብቸኛ መንገድ በእውነት ጋር ዘንድ ነው ያለው። ግን

እውነት ምንድን ነው? ኢየሱስ “ቃልህ እውነት ነው” ይላል (ዮሐ 17፡17)። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው ባለስልጣናችን ነው። ስለ እግዚአብሄር የበለጠ እንድንረዳ ግሩም የሆኑ በርካታ መጻህፍት አሉ እኛን - የሚያበረታቱ፣ የሚመሩና የሚያስተምሩ መጻህፍት፤ ብቸኛው አላማቸው እግዚአብሄርን ለማክበርና ህዝቡን ለመርዳት በሆነ መንፈሳዊ ሰዎች የተጻፉ መጻህፍት አሉ። ከእነዚህ ግን የትኞቹም የማያልፍ የለም ስለዚህ የመጨረሻ ባለስልጣናችን ሊሆኑ አይችሉም። መጽሐፍ ቅስ ብቻ የዘላለሙ እግዚአብሔር የማያልፍ ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ቃል አይደለም።

“ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ። ” (2 ጴጥሮስ 1፡20-21)።

“ቅዱሳት መጽሐፍት የእግዚአብሄር እስትንፋስ ያለበት ነው፡” (2 ጢሞ 3፡16)

በዚህ ምክንያት ነው በመንፈሳዊው ጦርነት እንደማያልፍ ባለስልጣናችን በእርሱ ላይ መደገፍ የምንችለው። ምን ማመን እንዳለብን ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ትክክል ወይም ስህተት መሆኑን ርግጠኛ የምንሆነው እንዴት ነው? ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ብለን የእግዚአብሄር ቃል ምን ይላል ብለን እንጠይቃለን። መጽሐፍ ቅዱስ ለእግራችን መብራት ለመንገዳችን ብርሀን መሆን አለበት (መዝ 119፡105) - በሌላ አነጋገር እርሱ የመጨረሻ ባለስልጣናችን ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣንና ስህተት መሆን አለመቻል ጥያቄ በአይምሮአችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማመን በጦርነት ውስጥ ለመቆማችን በጣም አስፈላጊ ነው። ዶክተር ጃም ስፓከር እንዲህ ይለናል፡

የመጽሐፍ ቅዱስን ስህተት መሆን አለመቻል እደግፋለሁ ሁሉም ክርስቲያኖችም እንዲሁ እንዲያደርጉ አበረታታለሁ።

መጀመሪያ እውነት ስለሆነ ነው። ከሌሎች መካከል ክርስቶስና ጳውሎስ እንደሚያምኑት የእግዚአብሔር ቃል “ከእግዚአብሔር አፍ በሰዎች መሳሪያነት ከመጣ” (ካልቪን)፣ የሆነ ውሸትን የሚያስተምርና የሚያረጋግጥ የእርሱ ሃሳብ አስነዋሪና የማይጠቅም በመሆን መወገድ አለበት።

ሁለተኛ፣ ገላጭ ነው። ስህተት አለመሆኑን የሚያረጋግጥ ሰው መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ መነዳት የተጻፈ ነው፡ ባለስልጣንና የማያልፍ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ያሳያል። እርስበርስ እንዲህ ያለ መተማመን አለን።

ሶስተኛ፣ ጤና ሰጪ ነው ("ጤናማ ትምህርት" በአዲስ ኪዳን ትርጉሙ)፣ የትምክህተኛው አይምሮአችን ስልታዊ መገዛት፣ ያለርሱ የእግዚአብሔርን የከበረ እውነት ወደምናጣበት፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚወስድ።

ልበስ

በእግዚአብሄር ቃል እውነት ያልበቃ መተማመን ሲኖረን የእውነትን ቀበቶ እንለብሳለን። እምነቶቻችንና ትምህርቶቻችን ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲገዙ- በአመክንዮ ወይም በስሜት ወይም ሰዎች በሚሉት ነገር ሳይሆን፣ በእውነት ቀበቶ እየታጠቅን ነው። የባህሪአችን መለኪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሲቆም፣ በአሁን የማህበራዊ መለኪያዎች ወይም ምቹ ወይም ቀላል በሆነ ነገር ሳይሆን፣ የእውነት ቀበቶ በትክክል በስፍራው ላይ ነው።

የእውነትን ቀበቶ ካልታጠቅን፣ ድል አድራጊ ወታደሮች በፍጹም አንሆንም። ስለ እምነት ልንናገር እንችላለን ወይም የምንፈልገውን ያክል ልንጸልይ እንችላለን ዲያብሎስ ግን በየጊዜው ያሸንፈናል።

ለኢያሱ የጌታ ምክር ዛሬም ለእኛ ጠቃሚ ነው፡

"የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም። በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ አትፍራ፥ አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?"

(ኢያሱ 1፡8-9)።

5. የጽድቅ ጥሩር

“የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ . . .” **ኤፌ** 6፡14

የጽድቅ ጥሩር ሰውነትን ከአንገት እስከ ጭን የሚሸፍን አንዱ የዕቃ ጦር ነው። ሁለት ክፍሎች አሉት፤ ፊትና ጀርባ። የደረት ጥሩር ከሌለ በጦርሜዳ ወታደር ለረጅም ጊዜ አይቆይም። የትኛውም ድንገተኛ ጦር ወይም ያልታሰበ ቀስት በፍጥነት ሊገድለው ይችላል። ይህ የጦር ዕቃ አይነት ነው ልብንና ሌላ ዋና የሰውነት ክፍሎችን የሚከላከለው።

ዲያብሎስ ሁልጊዜ ይህንን የክርስቲያን ዋና ክፍል እያጠቃ ስለሆነ በመንፈሳዊ ጦርነታችን ጊዜ ልብን የሚጠብቅ የሆነ ነገር ያስፈልገናል። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አነጋገር፣ ልብ የምኞቶቻችንን ማዕከል ይቆጣጠራል። ስሜታችን፣ አስተሳሰባችን፣ መውደዳችን እና ፈቃዳችን ከጽድቅ ጥሩር ጥበቃ ስር ይካተታሉ። እያንዳንዱ አማኝ በእነዚህ አካባቢዎች ላይ መጠቃትን ያውቃል። እንደ ዮዮ በስሜት ላይ ታች በማለት በስሜቶቻችን የምንገዛው ምን ያህል ነው! ከምኞቶቻችን ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ቀን የእግዚአብሄርን ነገር እንራባለን በሚቀጥለው ቀን በአለማዊ ደስተና ምኞቶች እንገዛለን። ይህ ሁሉ ትክክለኛ ነገር ነው፤ ሁልጊዜ በቴፕራመንት ብቻ የሚገለጽ አይደለም፤ ዲያብሎስ ነው እያጠቃን ያለው። ስለዚህ የመከላከያ ትጥቅን መልበስ ደግሞም በዚህ ጊዜ መዋጋትና ድል ማድረግ እንድችል እግዚአብሄር የሰጠንን መንፈሳዊ መሳሪያዎች መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው።

ጽድቅ

እዚህጋ “ ጸድቅ” ማለት ምን ማለት ነው? እነዚህን ቃላት ስንተረጉም የእግዚአብሔር የዕቃ ጦር እንጂ የእኛ አለመሆኑን በፍጹም መርሳት የለብንም። ስለዚህ ይህ ጽድቅ የእኛ አይደለም። ጳውሎስ የእኛን ታማኝነት እና የሞራል ባህሪ እያመለከተ አይደለም የእግዚአብሄርን ጽድቅ እንጂ። የራሳችንን ጽድቅ ለብሶ ወደ ጦር ሜዳ መግባት ተስፋ ወደሌለው ሁኔታ ይከተናል፤ እንዲህ ያለው ትጥቅ በጣም ደካማ ይሆናል። የእርሱን ክፉ ስራ የበለጠ ቀላል ስለሚያደርግለት ዲያብሎስ ክርስቲያኖች ለብሰውት ማየት ይፈልጋል ። የሚያስፈልገን የእግዚአብሄር የጦር ዕቃ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው።

በራሳችን ጽድቅ ላይ ተመስርተን ወደ ጦር ሜዳ ከገባን፣ ይሸውም፣ ምን ያክል መልካም፣ መንፈሳዊ፣ ጸላይ፣ መጽሐፍ ቅዱስን የምናውቅ እንደሆንን ተመክተን፣ በጣም የማንመካበትን

የህይወታችንን አቅጣጫ በማሳየት ዲያብሎስ ይገዳደረናል። እኔነት የነገሰበትን እና ክርስቶስ የተገለለበትን ስፍራ ያሳየናል። ከእኛ ይልቅ በጣም የተቀደሱና ህይወታቸው ከማማሩ የተነሳ የእኛን የዛገ እንዲመስል የሚያደርጉ ክርስቲያኖችን ያሳየናል። በዚህ አይነት ጥቃት የእኛ ጽድቅ በቀላሉ ይጠፋል ደግሞም መከላከል የማንችል ደካሞች ሆነን እንቀራለን።

የሚያስፈልገን የማይጠቃ ጽድቅ ነው ይህም እግዚአብሄር የሚሰጠው ነው። በፊሊ. 3፡9 በክርስቶስ ስለመገኘት ይጽፋል፣ "ከህግ ስለመጣ ስለራሴ ጽድቅ ሳይሆን በእምነት በክርስቶስ ስለሚገኘው- ከእግዚአብሄር በእምነት ስለሚገኘው ጽድቅ "። ያለፉትን ቁጥሮች ካነበብክ (4-6) በሆነ ጊዜ ጳውሎስ በራሱ ጽድቅ በጣም ተማምኖ እንደነበር ታያለህ። ክርስቲያን ሲሆን ግን እግዚአብሄር ከሚሰጠው ጽድቅ ጋር ሲነጻፀር ይህ ሁሉ ቆሻሻ እንደሆነ ተረዳ (ቁ 8)።

የተቆጠረ

ክርስቲያኖች ስንሆን እግዚአብሄር በክርስቶስ ጽድቅ ሸፍኖናል (ሮሜ 3፡21፣22፤ 5፡17፤10፡3-11)። በንጉስ ጀምስ ትርጉም ይህ ጽድቅ "የተቆጠረ" በአመት ደግሞ "የተሰጠ" ተብሎ ተገልጾአል። ሮሜ 4፡18-25ን አንብብ።

> ይህ በተለመደው ሐረግ "የክርስቶስ ጽድቅ መቆጠር" ተብሎ የተገለጠ ሀሳብ ነው - ይህም አማኞች ጻድቃን ናቸው (ሮሜ 5፡19) ደግሞም በእግዚአብሄር ፊት (ሮሜ 4፡11) ጽድቅ አላቸው፣ በራሳቸው ጻድቃን ስለሆኑ ሳይሆን የነርሱ ራስ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ስለሆነና ከእርሱ ጋር አንድ ስለሆኑ፣ የእርሱን ማንነትና ተቀባይነት ስለሚካፈሉ። የእርሱ ጽድቅ ፣ ለአብ የእርሱ መታዘዝ መሆን እንደሚገባው ሁሉ የእርሱ ጽድቅ የነርሱ ሆኗል ተቀባይነትም አግኝተዋል። አንዳንድ ጊዜ እንደሚገመተው በዚህ ትርጉሙ ለእነርሱ የእርሱ ጽድቅ መተላለፍ ህገወጥ የሆነ ልብ ወለድ አይደለም። በእነርሱና በእርሱ መካከል ባለ እውነተኛ ጥምረት ላይ ስለተመሠረተ፣ "በክርስቶስ" ጻድቀዋል (ገላ 2፡17)፤ እግዚአብሄርም ጻድቅ አድርጎ ቆጥሮአቸዋል እንደዛም ጠርቶአቸዋል፣ በግል ህጉን እንደጠበቁ ስለቆጠራቸው አይደለም (ይህ የሐሰት ፍርድ ይሆናል)፣ በወኪልነት ከጠበቀው ጋር በእምነት አንድ እንደሆን ስለቆጠራቸው ነው እንጂ (ይህ እውነተኛ ፍርድ ነው)።
>
> *ጄ.አይ. ፓከር*

ኢሳይያስ ለዚህ ደስ የሚል ስዕል አለው፡ "እኅሊልን እንደ ለበሰ ሙሽራ፥ በጌጥ ሽልማትዋም እንዳጌጠች ሙሽራ፥ የማዳንን ልብስ አልብሶኛልና፥ የጽድቅንም መጐናጸፊያ ደርቦልኛልና

በእግዚአብሔር እጅግ ደስ ይለኛል፥ ነፍሴም በአምላኬ ሐሤት ታደርጋለች።" ኢሳ 61፡10)። ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት በራሳችን ጽድቅ እንዴት ደስተኞች ነበርን! "እንደ ማንኛውም ሰው ጥሩ ነኝ። ሀጢአተኛ እንደሆንኩ የሚናገር ማነው?" ብለን እናስብ ነበር። የኢየሱስን ፍጹም፣ ሀጢአት የለሽ ንጽህና እግዚአብሄር እስኪያሳየንና "የጽድቅ ስራችን ሁሉ የመርገም ጨርቅ" እንደሆነ እስኪነግረን ድረስ። (ኢሳ 64፡6) የራስ ጽድቅ መጎናጸፊያ ልካችን ሆኗል እኛም ወደነዋል።

ምንም ያህል ሳንቆይ እኛም የመርገም ጨርቅ መሆናቸውን አይተናል ስለሀጢአትም ጥፋተኛነት ተሰምቶናል ተወቅሰናልም። ከዚያም በኋላ የነበረው ችግራችን ዋጋ ያሌለውን የራስ ጽድቃችንን የምንተካበት ሌላ መጎናጸፊያ የት ነው የምናገኘው? የሚል ነበር። እግዚአብሄርም መለሰ "ወደኔ ኑና የደህንነተን ልብስ አለብሳችኋለሁ"። በንሰሀና በእምነት ወደ እግዚአብሄር ስንመጣ ያገኘነው ምንድን ነው? የሚፈርድብንን ንጉስ አይደለም፣ በጥረታችን የሚቀልድና በሀጢአታችን የሚያሳፍረንን አይደለም፣ ጸጋና፣ ርህራሄንና ምህረትን የተሞላ የሚወደንን የሰማይ አባት ነው እንጂ።

ወደ ሉአላዊ ጸጋው ማስቀመጫ ወሰደን ደግሞም የጽድቅን መጎናጸፊያ አወጣ። የዋጋውን ባጅ አየን- "በኢየሱስ ደም የተገዛ" - በእሱም ላይ ስማችን መጻፉን በመገረም ተመለከትን። በመንፈስ ቅዱስ ነበር በልካችን የተሰራው - ፍጹምም ነበር። ከዚያም ልክ እንደኢሳያስ "በጌታ እጅግ ተደሰትን" ሃሴትም አረግን።

ስንድን ያ ሁሉ ነገር ሆነ። ጽድቅ ለእኛ ተላለፈልን (ወይም ተቆጠረልን)። ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ አንድ ወታደር የደረት ጥሩር ለምን ይለብሳል? ምንም አንኳን እንደበፊ የበረታ ቢሆንና ከፍ ያለ ብቃት ሁሉ ቢኖረውም፣ የተፈጥሮ ሰውነት ጦር፣ ሰይፍ ወይ ቀስት እንደማይቋቋም ተረድቷል። ስለዚህ ራሱን (ይበልጥ ብርቱ በሆነ - በደረት ጥሩር) በሌላ ሰውነት ይሸፈናል። ስለዚህ መከላከያው ራሱ ሳይሆን በርሱ ነው። በተመሳሳይ መንገድ የደረት ጥሩራችን፣ መከላከያችን ፣ የእግዚአብሄር የተላለፈ ጽድቅ ነው።

የተካፈልነው

ለተላለፈው ጽድቅ እግዚአብሔር ይመስገን ግን በራሱ ግብ አይደለም። "የተካፈልነው" ጽድቅም አለ። በጸጋ በመዳን፣ ደግሞም በተላለፈ በእግዚአብሄር ጽድቅ በመሸፈን አሁን የእግዚአብሔር መንፈስ ሊለውጠን ወይም ሊቀድሰን በእኛ መስራት ይጀምራል። ቀስ በቀስ አስተሳሰባችን፣

መሻታችንና ስለህይወት ያለን አመለካከት መለወጥ ይጀምራል። በአለም እያለን በፍጹም ሀጢአት አልባ አንሆንም ነገር ግን ራሳችንን ሀጢአት መጥላት ሲጀምር እናገኛዋለን። ምንድን ነው እየሆነ ያለው? ይህ "የተካፈልነው ጽድቅ" ነው። በደህንነታችን ጊዜ የእኛ ያልነበረ ጽድቅ፣ እንደካባ ሸፍኖን የነበረ፣ አሁን የእኛ ክፍል ሆኗል። በጸጋ ማደግና እግዚአብሄርን ማወቅ እንጀምራን።

በተቆጠረ ጽድቅና በተካፈልነው ጽድቅ መካከል ያለው ልዩነት የተቆጠረ ጽድቅ የክርስቶስ ነው ሙሉና ፍጹም ነው። ይሸፍነናል ደግሞም በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት እንዲኖረን ያደርገናል። የተካፈልነው ጽድቅ መንፈስ ቅዱስ የበለጠ ኢየሱስን እንድንመስል ያደርገናል። እግዚአብሄር በእኛ ውስጥ ያለማቋረጥ የሚሰራው ነው፣ በዚህ ምድር በፍጹም ሙሉ አያደርገንም ነገር ግን የበለጠ ኢየሱስን እንድንመስል ያደርገናል። ይህ የተካፈልነው ጽድቅ ነው የዲያብሎስ የሆነውን ነገር ሁሉ እንድንጠላ የሚያደርገን። በአዲሱ ጌታና ገዢ አዲስ ፍጥረት ነን ክፉውንም እንዋጋለን።

ስለዚህ ይህ ልባችንን እና ከእርሱ የሚወጣውን ሁሉ - ስሜቶቻችንን፣ መሻታችንን፣ አስተሳሰባችንን የሚጠብቅ የጽድቅ ጥሩር ነው። በደህንነት ጊዜ የተቆጠረልን የእግዚአብሄር ጽድቅ ነው ቀስ በቀስም በውስጣችን ባለው መንፈስ ቅዱስ እየተካፈልን ነው።

ዋስትና

አንድ ወታደር የደረት ጥሩር ለብሶ ወደ ጦር ሜዳ ሲገባ ታላቅ የመተማመንና የርግጠኝነት ስሜት አለው፤ መከላከያ እንዳለው ያውቃል።

> በመጀመሪያ ደረጃ የጽድቅ የጦርዕቃ የመተማመንን አጠቃላይ ስሜት በመስጠት ይረዳናል ይህ ደግሞ ዘወትር ለጦርነታችን ጠቃሚ ነው። ርግጠኛ ሳትሆን ወይም እያመነታህ ከዲያብሎስ ጋር ወደዚህ ውጊያ ከገባህ፣ በቃ ተሸንፈሃል። መተማመን ያስፈልገናል። እዚህ እንደወታደር ቆሜአለሁ ደግሞም ስለጠላት የሆነ ነገር አውቃለሁ። ግምቶቹን መርምሬአለሁ፣ ስለሚያዛቸው ስልጣናት የሆነ ነገር አውቃለሁ፣ ሊጠቀመው ስለሚችለው መሳሪያዎች ደግሞም በመራቀቅ፣ በሀይልና በጥንካሬም እንደሚታወቁ አውቃለሁ። ለእርሱ ጥቃት የተጋለጡትን በእኔም ውስጥ ያሉትን እነዚህ የተጋለጡ የሰውነት ክፍኞም አውቃለሁ። እንደተሸፈኑ እርግጠኛነት እስከሚሰማኝ ድረስ እየመጣ ላለው የሆነ የተለየ ውጊያ ልቀምና ዝግጁ ልሆን አልችልም። ይህ

> የደረት ጥሩር እንዳለኝ ባወኩኝ ቅጽበት ግን ሁሉም መልካም እንደሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ ይህ ማለት የደህንነት ማረጋገጫ ማለት ነው፤ የአጠቃላይ አቋማችንና ስፍራችን ግንዛቤ።
>
> *ዲ. ኤም. ሎይድ - ጆንስ*

ከዲያብሎስ ጋር ላለው ውጊያ ለክርስቲያን ወታደር የደህንነት ማረጋገጫ እጅግ ዋጋ ካላቸው እሴቶች መካከል አንዱ ነው ደግሞም ለህዝቡ ሁሉ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው (ዕብ 10፡22፤ 1 ዮሐ 5፡13፤ ሮሜ 8፡16)። ስለዚህ ሰይጣን ዘወትር በአእምሮአችን ጥርጥር ለመዝራት መሞከሩ አስገራሚ አይደለም።

> እርግጠኛነት ምርኮ ለመበዝበዝ፣ ያልጸና መንግስቱን በጆረው ላይ ለማናወጥ ብርቱ ሰዎችን ብርቱ እንደሚያደርጋቸው ሰይጣን ያውቃል ስለዚህም አማኞችን እርግጠኛ ከመሆን ለመከልከል በጣም ትጉና በጣም የሚሰራ ነው።
>
> *ቶማስ ብሩክስ*

ስሜቶች

በዚህ በስሜታችን ዙሪያ ርግጠኛነት የተጋለጠ ይሆናል። ስሜት የእያንዳንዳችን በጣም አስፈላጊ ክፍል ነው በተለይም በመንፈሳዊ ህይወታችን። የሆነ ነገር ሳይሰማህ በርግጥ በወንጌል አታምንም። የእግዚአብሄርን የጸጋ ወንጌል እንደሚያምን የሚናገር ሰው ግን ደግሞ በርሱ የማይነካ ሰው አልዳነም ወይም ብርቱ በሆነ መንፈሳዊ ማፈግፈግ ውስጥ ነው። በእግዚአብሄር ህልውና ውስጥ መሆንና አለመነካት ማንም ሰው አይችልም፤ ስሜትና መነካት በጣም አስፈላጊ ናቸው። ወደ ኢሳይያስ 6 ሂድና በእግዚአብሔር ህልውና ፊት የነብዩን የስሜት ጥልቀት ተመልከት- “ወዮ ለእኔ” (ቁ 5)፤ በተመሳሳይ ሁኔታ በሐዋ ስራ 5 የጥንቶቹ ክርስቲያኖች “ በታላቅ ፍርሀት” (ቁ 5) እና “ሀሴት” (ቁ 41) ይመልሳሉ።

ይህ ሁሉ በፍጹም ተፈጥሮአዊ ነው ዲያብሎስ ግን ለስሜት በጣም የበዛ አስፈላጊነት ላይ እንድናተኩር ይፈልጋል። ስሜት ሊያስደስት፣ ሊያነቃቃና ሊያበረታታ ይችላል ችግሩ ግን በፍጹም እነዚህ ነገሮች አይቆዩም። ወዲያው ወይም ትንሽ ቆይተው ይጠፋሉ። በሰንበት አገልግሎት የተሰማህ የደስታና የሀሴት ስሜት ጠዋት ሰኞ ወደስራ ስትሄድ ብዙ ጊዜ ተለይቶህል። ለዚህ ነው ስሜት ያለልክ አደገኛ ሊሆን የሚችለው ደግሞም ፍጹም

የማያስተማምኑ ናቸው። ለምሳሌ፣ “በልቤ ስለሚሰማኝ እግዚአብሄር እንደሚወደኝ አውቃለሁ” ማለት በቂ አይደለም። በልብህ ያልተሰማህ ጊዜስ?

በስሜታችን ላይ በጣም ጥገኛ ከሆንን፣ ይህ ነው የሚሆነው። መሆን ነበረባቸው ብለን እንደምናስበው ስሜቶቻችን ጠንካራ ባልሆኑ ጊዜ፣ እውነተኛ አማኞች እንሁንም አንሁንም ዲያብሎስ ወደ አእምሮአችን የጥርጥር አይነቶችን ሁሉ ያመጣል በውጤቱም ጭንቀትና ሃሳቦች ነፍሳችንን ያጥለቀልቃሉ። የብዙ ክረስቲኖች ችግር፣ ብዙ ይሰማቸዋል በጣም ትንሽ ያስባሉ። እንዲህ ያሉት ክርስቲያኖች ናቸው ደግሞም እርግጠኝነት በማጣት የሚቸገሩት። ከፍተኛ የሆነ የስሜት መንፈሳዊ ደስታ የሚለማመዱ ሰዎች፣ ከፍተኛ ጥልቅ የሆነ ተስፋ መቁረጥንም እንደሚለማመዱ ተገንዝበህ ታውቃለህን? እነርሱን ከፍ ያደረጋቸውና መንፈሳዊ ህይወታቸውን ያበለጸገ ስሜት ካልተረጋገጠ፣ ባዶ ያደርጋቸዋል ነፍሳቸውንም እጅጉን ያደኸያል።

ስሜት በጣም ዋና ነገር ነው - ምንም ስሜት ከሌለህ - ተጠንቀቅ! እምነትህንና ህይወትህን ግን በእነርሱ ላይ አትመስርት። ያ አንድ የዲያብሎስ ሽንገላ ነው። እምነታችን በስሜታችን ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ በክርስቶስ ባለ በእግዚአብሄር ፍቅርና ጸጋ ነው እንጂ። መተማመናችን በተቆጠረልን በእግዚአብሄር ጽድቅ ላይ ነው። ያ ነው የፅድቅን ጥሩር መልበስ ማለት ።።ታሽጸንችን እግዚአብሄር ለአንዱና ለመጨረሻ በሰራልን ነገር ላይ ነው እንጂ በጊዜአዊ በጊዜው የተለየ ስሜት ላይ አይደለም።

በፋሲካ ምሽት ስለ ሁለት የዕብራውያን ወንድ ልጆች የተነገረ ታሪክ አለ (ዘጸ 12)። ሁለቱም በቤተሰባቸው ታላቅ ናቸው እና (ቁ 12) ላይ ያለው የእግዚአብሄር አዋጅ እነርሱን እንደሚያካትት ያውቁ ነበር። ብቸኛው ተስፋቸው የፋሲካው በግ ደም በቤታቸው በር ላይ ከተረጨ፣ ፍርዱ ያልፋቸዋል የሚለው የእግዚአብሄር ቃል ነበር።

ቤተሰቦቻቸው እግዚአብሄር እንደተናገረው አደረጉ ሁለቱም ወንዶች ልጆች በእንዲህ ያለ ምሽት ወዳልጋቸው ሄዱ። አንዱ ያለምንም ችግር ተኛ በደሙ የተጠበቀ መሆኑን በመተማን። ሌላው ሌሊቱ አለፈ፣ ስለሚሆነው ነገር በመጨነቅ። ከእነርሱ የትኛው የበለጠ የተጠበቀ እንደሆነ ጥያቄ ተጠየቀ። አንዱ ታመነ ሌላው በጭንቀትና እርግጠኛ ባለመሆን ስሜት ሲመታ። ነገር ግን ሁለቱም፣ አንዱ ልክ እንደሌላኛው የተጠበቀ ነበር። ደህንነታቸው በስሜታቸው ላይ

የተመሠረተ አልነበረም “ደሙን ባየሁ ጊዜ አልፋቸኋለሁ፡፡” በሚለው በእግዚአብሄር ቃል ላይ እንጂ፡፡

አስተሳሰብ

ዲያብሎስ ሃሳባችንንም ያጠቃል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ከሳሽ ተብሎአል (ራዕይ 12፡10)፡፡ ሀጢአታችንን ሁሌ እያስታወሰ በእርሱ ይከሰናል እንዲህ ያሉ ነገሮችን በመናገር፡፡ “እናንተ ወጣት ወንዶች ክርስቲያን ነን ትላላችሁ፤ እነዚያን ሴቶች የምታስቡትስ? እናንተ ወጣት ሴቶች ክርስቲያች ነን ትላላችሁ ግን ራሳችሁን ትወዳላችሁ ፣ ትቀናላችሁ፣ ታማላቸሁ? እናንተ ሽማግሌ ወንዶችና ሴቶች ራሳችሁን ክርስቲያን ብላችሁ ትጠራላችሁ፣ ስስታችሁና ቁሳዊነታችሁስ አለማዊነታችሁስ?

በእነዚህና በሌሎች መንገዶች እውነተኛ ክርስቲያኖች አይደላችሁም እያለ ይከሰናል፡፡ እንዲህ ያ ነገር ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ህሊናችንም እንደተመታና እንደተቀጠቀጠ ይሰማናል፡፡ ምንድን ነው የምናደርገው? እንደገና ይሄም የጽድቅ ጥሩር ዋጋ ነው- ወደ ክርስቶስ ጽድቅ እንሻሻለን፡፡

ስላጠፋኋቸው ጥፋቶች

ከሳሽ ምንም ቢያገሳ

በሚገባ አውቃቸዋለሁ፣ በሺህ የሚቆጠሩ ሌሎችንም

ያህዌ አንዱንም አያስበውም

ኤስ. ድበሊው. ጋንዲ

ይህ የተቆጠረ ጽድቅ እና በእምነት የመጽደቅ ውበት ነው፡፡ የጽድቅ ጥሩርን መልበስ ማት ይሄ ነው፡፡

ተስፋ እንደቆርጥ ሰይጣን ሲፈትነኝ

በውስቴ ስላለ ሀጢአት ሲነግረኝ

አይኖቼን አንስቼ እርሱን አየዋለሁ

ሀጢአቴን በሙሉ ይቅር ያለውን

ሀጢአት የለሽ አዳኝ ስለሞተ

ሀጢተኛ ነፍሴ ነጻ ሆና ተቆጠረች

እግዚአብሄር ጻድቁ ረክቷልና

እርሱን ተመልክቶ እኔን ይቅር አለ

ቻሪቲ ሊስ ዴ ቸኔዝ

የጽድቅ ጥሩር የማያጋልጥ ነው ምክንያቱም ዲያብሎስ ስለክርስቶስ የምትክነት ሞት መልስ የለውም። የእርሱ ጽድቅ የእኛ ብርታት እና መከላከያ ነው።

ልበስ

ሙሉ በሙሉ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እና በእርሱ ጽድቅ ላይ ስንቆም የጽድቅን ጥሩር እንለብሳለን። ስለዚህ ክርስቶስን ለማክበር፣ እርሱን ከፍ ለማድረግና በእረርሱ ለመደሰት መማር አለብን። ይህ ነው ሰይጣንን እንዲሸሽ የሚያደርገው። በራስህ ችሎታዎች መታመን ከቀጠልክና በመልካም ስሜቶች ላይ ከተመሰረትክ፣ ሁልጊዜ ሰይጣን ትከሻህ ላይ ተቀምጦ በስኬቱም እየተደሰተ ነው።

የተቆጠረልን ጽድቅ ሀጢአታችን ምላሽ እንደተሰጠው ያረጋግጥልናል። የተካፈልነው ጽድቅ ሀጢአትን ቸል ከማለት ይጠብቀናል ደግሞም ዲያብሎስንና ስራውን እንድንጠላ ያደርገናል። የተቆጠረና የተካፈልነው ጽድቅ በጽድቅ ጥሩር ተዋህደው ከጠላት ክስና ነቀፋ ሊጠብቁን ባንድ ላይ የእግዚአብሄርን አቅርቦት ይፈጥራሉ።

ምንም አንኳን ሀጢአት በሀዘን ቢሞላኝም

የጸጋን ዙፋን እመለከታለሁ

ኢየሱስ ጽድቄ ነውና።

ምድርና ሲኦል ባንድነት በኔ ላይ ተነሱ

ከኃኔ ግን የመለኮት ሀይል አለ

ኢየሱስ ሁሉንም ነው ለኔ እሱም የኔ ነው!

ጆን ኒውተን

6.የሰላም ወንጌል

“በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው . . .” (ኤፌ 6፡15)

የጥንት ጦርነት በዋናነት የእጅ ለእጅ ግጥሚያ ስለነበር፣ ለአንድ ወታደር የእግር በሚገባ መርገጥ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ መስፈርቶች መካከል አንዱ ነበር። ጳውሎስ “ጸንታችሁ ቁሙ . . .” ሲል እያመለከተ ያለው ይህንን ነው። የሮማን ወታደር ጫማ ሚስማር የተደረገበት ጫማ ተብሎ ይበልጥ መገለጥ ይችላል። ታሪክ ጸሐፊው ጆሲፈስ “በሹል ሚስማሮች በወፍራሙ የተሰኩበት ጫማዎች” ብሎ ይጠራቸዋል። በዚያ ጊዜ ያልተለመደ ነበር ደግሞም በጠላት ላይ ትልቅ ጥቀም ይሰጣቸው ነበር።

> እንደ አንድ ጄኔራል ለጁልየስ ቄሳር ስኬት አንዱ ዋናው ምክያት ሰዎቹ በእንዲህ ያለ አጭር ጊዜአት ረጅም ርቀቶችን እንዲሸፍኑ ያስቸላቸውን የወታደር ጫማ ያደረጉ መሆናቸው ነበር። በቂ የሆነ መከላከያ ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ እንዳላቸው በማሰብ ራሳቸውን በማታለል ጠላቶቻቸው ደግመው ደጋግመው ያለ ትጥቅ ተይዘው ነበር። በታላቁ እስክንድርም ለተገኙ ድሎች ዋና ሚና የተጫወተው ይኸው ሁኔታ ነው።
>
> *ዊልያም ሄንድሪክሰን*

እነዚህ ልዩ የሆኑ ጫማዎች ለሮማን ወታደሮች ጽኑ መርገጥ ሰጥተዋቸው ነበር፣ በአዳላጭ መሬት ላይ ቢዋጉ እንኳን፡ ባለመጽናት እንዳይንገዳገዱ። ትልቅ እንቅስቃሴም ለወታደሩ ይሰጠዋል። የእነዚህ ሁለት ነገሮች፣ የጽናትና የእቅስቃሴ ቅንጅት ለጦርነት የዝግጁነቱንና የመተማመኑን ስሜት ይጨምራል። ሐዋርያው ጳውሎስ ጦርሜዳ ስንገባ፣ የሰላም ወንጌል በእኛ ውስጥ እነዚህን ተመሳሳይ ነገሮች ማፍራት እንዳለበት ይናገራል።

ሰላም

ወንጌል የሚሰጠው ሰላም “በእግዚአብሄር ዘንድ ሰላምን መያዝ” ነው (ሮሜ 5፡1)። ይህ ከአይምሮ ሰላም ጋር መጋጨት የለበትም። ሁሉም ሰዎች የአእምሮ ሰላምን ይፈልጋሉ። አንዳንዶች በድራግ፣ አንዳንዶ በመጠጥ፣ ሌሎች ደግሞ በደስታ ፈጣሪ መንገዶች ይፈልጉታል። አለም አሰቃቂና ትልቅ ጭንቀት ውስጥ ነች ስለዚህ ሰዎች የአእምሮ ሰላም መፈለጋቸው አስገራሚ አይሆንም። የሐሰት ሀይማኖቶች እና “የክርስቲያን” አምልኮ ተብለው

የሚጠሩት ለዚህ መሻት ራሳቸውን ይሰጣሉ ቀላል “ደህንነትም” ይሰራሉ። “በእኛ መንገድ ና” ይላሉ ደግሞም አትጨነቅ” መከራህን እርሳና ሰላምን አግኝ” ይላሉ። ብዙ ሰዎች በዚህ ይታለላሉ የሆነ አይነትም ሰላም ያገኛሉ፤ በእግዚአብሄር ዘንድ ያለ ሰላም ግን አይደለም። የሰዎችን ሀጢአትና ጥፋተኛነት ጥያቄ ዝም ብሎ የሚየልፍ በእግዚአብሄር ዘንድ ያለ ሰላም መጽሐፍ ቅዱስ አያውቅም። ከዚያም በላይ መጽሐፍ ቅዱስ ቀላል ሀይማኖት በሚሰብኩ ሰባኪዎች የሐሰትን ሰላም ያገኙትን ሰዎች ያጋልጣል ደግሞም ያስጠነቅቃል። (ህዝ 13)።

ስለዚህ በእግዚአብሄር ዘንድ ያልሆነ ሰላም አለ ማለት ነው። የዚህ የሀሰት ሰላም ምልክቶች ምን ምን ናቸው? እነዚህ ናቸው፡ ንስሀ የለም፣ የሀጢአት ክፉነት ስሜት የለም፣ ከሀጢአት ጋር ትግል የለም፣ መጋደል የለም። ይህ አይነት ሰላም ስነ ልቦናዊ እንጂ መንፈሳዊ ስላልሆነ እነዚህ ነገሮች የሉም።

በእግዚአብሔር ዘንድ ያለ ሰላም የወንጌል ውጤት ነው፣ በቅዱስ እግዚአብሔር ፊት ወንጌል ብቻ ስለሆነ ከሀጢአታችንና ከጥፋታችን ጋር ዲል የሚያደርገው። አንድ ሰው ክርስቲያን ሲሆን ይህ አስደናቂ ሰላም የእርሱ እውነተኛ ልምምድ ይሆናል። እዚህጋ ግን አያዎ አለ ምክንያቱም ክርስቲያን በሆንንበት ቅጽበት ወደጦርነት ገብተናል ይህም ደግሞ በጣም እውነተኛ ተሞክሮ ነው። ሰላምና ጦርነት፣ ሁለቱም በተመሳሳይ ጊዜ- ይህ እንዴት ይሆናል?

ክርስቲያን በጦርሜዳ ውስጥ ሰላም ሊኖረው ይችላል ምክንያቱም በዚህ ጦርነት ሶስት አበይት ነገሮች አሉ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያጠቃልሉ ። እነርሱም፡ 1) የመንስኤው መልካምነት፡ 2) የድሉ ርግጠኛነት እና 3) ድል ነሺዎቹን የሚጠብቅ ክብር፡ ናቸው።

መንስኤው በምድር ላይ የእግዚአብሄር ክብር፣ የሀጢአትና የክፋት መጥፋት ነው ። የተረጋገጠው ድልና ድል አድራጊዎችን የሚጠብቅ ክብር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ የተረጋገጡ ናቸው። በዚህ እውቀት ወደ ጦርነቱ በእግዚአብሔር ሰላም መግባት መቻላችን ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሄር ሰላም ልባችንንና አይምሮአችንን ሞልቶታል።

መረጋጋት

በኤፌ 4፡14 ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች “እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገሙ ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፉ ሕፃናት መሆን . . .” እንደሌለባቸው ናፍቆቱን ይገልጻል። በዚህ ውስጥ የመንፈሳዊው

አለመረጋጋት ፍጹም ስእል አለን። የመረጋጋት ጉዳይ ሁሉን አዲስ አማኝ የሚገጥም የማይቀር ችግር ነው። ገና በቅርቡ ነው ዳግም የተወለደው፤ ዳግም ተወልዷል ደግሞም በክርስቶስ አሁን ህጻን ነው። ልክ እንደሁሉም ህጻናት ብዙ ጫጫታዎችን ሊያደርግ ይችላል፣ ግን በእግሩ በጣም አልጸናም፤ መረጋጋት የለውም። ስለዚህ በተቻለ ፍጥነት መንፈሳዊ መረጋጋትን ማግኘት ተቀዳሚ አስፈላጊነት ያለው ነው።

ምንም እንኳን ዳግም ከተወለዱ አመታት ቢያስቆጥሩም በርካታ አማኞች ገና መንፈሳዊ ህጻናት መሆናቸው አሳዛኝ እውነታ ነው። “በሁሉም የትምህርት ነፋሳት ወዲህና ወዲያ ይነፍሳሉ።” ሁሉንም ዘመናዊ መንፈሳዊ ዝንባሌ ወይም አጽኖት በጉጉት ይቀበላ፤ በውጤቱም በጦር ሜዳ ጥቅም የለሽ ናቸው። በወንጌል እውነተ ላይ መቆም አይችሉም ስለምንነቱ በፍጹም ርግጠኞች አይደሉም። በሁሉም ስፍራ ይዞራሉ፤ እንግዳ አመለካከቶችንም ይይዛሉ፣ አንግዳ ነገሮችን ያደርጋሉ ሙሉ በሙሉም ወጥነት የላቸውም። ለምን? እግሮቻቸው “ከሰላም ወንጌል በሚመጣው ዝግጁነት አልተጫሙም። በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮና ዶክተሪን ፍጹም ፍላጎት የላቸውም። እንደ ደንበኛ ህጻን የሚጫወቱበትን ነገር፣ የሚያዝናናቸውን ነገር፣ ለመቅመስ ጣፋጭ እና ለማየት ደስ የሚያሰኝ ነገር ነው የሚፈለጉት። ውጤቱ ከብዙ አመታት በኋላ መንፈሳዊ ህጻንነትና አለመረጋጋት ነው።

አዲስ አማኝ ከሆንክ፣ እነዚህን ስህተቶች አትስራ። እነዚህን የማስወገድ ብቸኛ መንገድ ይህን የጦር ዕቃ መልበስ ነው። ከእግዚአብሄር ጋር ሰላምን የሚሠጠን ወንጌል ነው ስለዚህም ወንጌል ብቻ ነው ጸንተን ለመቆም የሚያስችለን። ወንጌል ግልጽ ያልሆነ፣ ያልታወቀ ሃሳቦች የሉትም፤ ግልጽ ፣ የማይለወጥ የህያው የእግዚአብሄር ቃል ነው። የሚለውን ነገር ማለቱ ነው እኛም ልናምነው ይገባል።

መንፈሳዊ መረጋጋት የሚመጣው እግዚአብሄር የተናገረውን ነገር ባለማንገራገር በመታመን ነው። የምናምነውን ነገር ማወቅና በእርሱ ላይ ጸንተን መቆም አለብን።

ተሀድሶ አምጪው ማርቲን ሉተር እዚህ ላይ ለእኛ ታላቁ ምሳሌአችን ነው። በ1521 ስለ እምነቱ መልስ እንዲሰጥ በሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፊት ሲቀርብ፣ እንዲህ በማት መለሰ፡

> ክቡርነትዎና ጌትነትዎ ከእኔ ግልጽ፣ ቀላልና አጭር መልስ ይፈልጋል፣ እኔም አንድ እሰጥዎታለሁ፣ እርሱም ይሄ ነው፤ እምነቴን ለጳጳሱም ሆነ ለምክር ቤቶች ማስገዛት አልችልም

> ምክንያቱም ልክ እንደ ቀን ሁሉ እርስ በርስ በተደጋጋሚ እንደሚስቱ ግልጽ ነው። ስለዚህ በቅዱሳት መጻህፍት ምስክርነት ካልተረዳሁ በቀር ወይም ግልጽ ባለ አመክንዮ - በጠቀስካቸው አውደ ምንባቦች ካላመንኩ በቀር - ህሊናዬን በእግዚአብሄር ቃል ተገድቦ ካልተገዛ - ማፈግፈግ አልችልም ደግሞም አላፈገፍግም፣ ምክንያቱም ለክርስቲያን በህሊናው ላይ መዋሸት መልካም አይደለምና።

ሉተር ህይወቱን የሚያጣበት ትልቅ አደጋ ውስጥ ነበር። ነገር ግን ንጉሰ ነገስት ቻርለስ አምስተኛን፣ የፖለቲካና የሀይማኖት መሪዎች ተጋባገሮችን ፊት ለፊት በመጋጠም "ይኸው ቆሜአለሁ፣ ሌላ ነገር ማድረግ አልችልም። እግዚአብሄር ይርዳኝ! አሜን።" በማለት በድፍረት ተናገረ ። ንጉሰ ነገስቱም ጭምር "መነኩሴው በጸና ልብና በማይናወጥ ብርታት ይናገራል" ለማለት ተገዶ ነበር።

የማርቲን ሉተር መረጋጋት ቅዱሳት መጻህፍትን የማጥናቱና ወደ እግዚአብሄር የመቅረቡ ውጤት ነበር። ያመነውንና ያመነበትን ምክንያት ያውቅ ነበር። ምንም እንኳን እንደ ማርቲን ሉተር መንፈሳዊ እውቀትና ብርታት በፍጹም ባይኖረንም እግዚአብሄር ሁላችንም መንፈሳዊ መረጋጋት እንዲኖረን ይፈልጋል። የመጀመሪያውም የመጨረሻውም የዚህ መንገድ የእግዚአብሄርን ቃል ወደ ማወቅ ነው። ለዚህ ምትክ የለም።

ማሰብና መተግበር

እዚህጋ ግን አያበቃም። የእግዚአብሔርን ቃል ለኑሮአችን ማዛመድም መማር አለብን። አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች በሰሙት ስብከት ውስጥ በቂ ተዛምዶ እንደሌለ ሲናገሩ ይሰማሉ። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል ከሆነም ደግሞ እሱን በተመለከተ ሰባኪዎቹ የሆነ ነገር ማድረግ አለባቸው። የእግዚአብሄርን ቃል ለጉባኤው ህይወት ማዛመድ ያልቻለ ስብከት ከትክክለኛ ስብከት በጣም ጎድሏል። ነገር ግን ግድ የተሰኙት ሰዎች ለራሳቸው ማሰብን በፍጹም እንዳልተማሩም የሚገልጽ ይሆናል እንዲህ ያለው ክስ። በዚህ ምክንያት የቅዱሳት መጻህፍትን ታላቅ መርሆች በህይወታቸው የተለየ ሁኔታ ማዛመድ አይችሉም፣ ስለዚህም ልክ እንደ ህጻን ልጅ በማንኪያ መመገብ አለባቸው። ለሆነ ችግር መንፈሳዊ አስጎሪን ለማግኘት ብቻ ስብከት ማዳመጥ አደጋ አለው። እኛ ራሳችንን ለየትኛውም ችግር ማዛመድ የምንችለውን ታላላቅ እውነቶች ከነርሱ በመመማር ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስ የአድርጉና የአታድርጉ ረጅም ዝርዝር አይደለም፤ ይልቁን ሁሉንም የህይወት አቅጣጫ የሚነኩ መርሆችን ይዞአል። ለምሳሌ፣ አንድ ክርስቲያን በሳምንት ውስጥ ቴሌቭዥን ለማየት ስንት ሰአት ማጥፋት እንዳለበት ምንም አይናገርም ነገር ግን ስለ ጥበበኛና ተገቢ የጊዜ አጠቃቀም ብዙ ነገር ይናገራል። በምን ያህል ጊዜ አንድ ክርስቲያን መኪናውን መቀየር እንዳለበት ወይም ምን ያህል ሙሉ ልብሶች ወይም ጫማዎች ሊኖሩት እንደሚገባ አይናገርም ስለ ገንዘብ ባለ አደራነታችን ግን ብዙ ይናገራል። ለእያንዳንዱ ቀን ኑሮአችን የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶችና መርሆች ማዛመድ ካልተማርን በቀር መንፈሳዊ መረጋጋትን በፍጹም አናውቅም። እንደ ክርስቲያን መኖር ካለብህ፣ እንደክርስቲያን መማር አለብህ። ከክርስቶ ጋር ብዙ ጊዜ ካላጠፋህ ደግሞ እንደክርስቲያን በፍጹም አታስብም። ያ ማለት በጸሎት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ብዙ ጊዜ ማሳለፍ ማለት ነው።

ውጤቴማ እድገት

ያለ እንቅስቃሴ መረጋጋት ካለህ እንደ መንገድ መብራት የማትነቃነቅ ትሆናለህ ነገር ግን ቀዝቃዛ፣ በጣም በትንሽ ስፍራ ብቻ መብራት እንደሚበራበት ህይወት አልባ የኮንክሪት ምሰሶ። እንቅስቃሴ ያስፈልገናል የምናውቀውና የምንወደው እውነት በጠላት ላይ በውጤታማነት መንቀሳቀስ እንዲችል። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወደ ጦር ሜዳ መገስገስ አለባት። ለመጠቃት ዝም ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ተነሳሽነቱን በመውሰድና መልእክቷም ለዛሬ ህዝብ ጠቃሚ እንዲሆን የምናደርገው እንዴት ነው? እንደዛ እንዲያደርግ አናደርገውም፤ በራሱ ጠቃሚ ነው። ወንጌል በህይወታችን እንዲሰራ ስንፈቅድለት፣ የእግዚአብሄር ሰላም በእኛ ይታያል በጠፋው አለም ላይም ማስረጃ ይሆናል።

ስለዚህ ህይወታችን ስለዚህ የውስጥ ሰላም ማስረጃ መሆን አለበት። የሰላም ወንጌል በእኛ ውስጥ በጌታ ብርቱና የታመንን ሆነን ጠላትን ለመግጠም ወደፊት የሚያመጣን የአእምሮ አመለካከትን ማምጣት አለበት።

ዕብ 13፡20-21ን አንብብ። በእግዚአብሄር ሠራዊት ውስጥ በእግዚአብሄር ሰላም እውቀት ያልታጠቀ ሰነፍና ደካማ ወታደር ነው።

ፊሊ. 4፡6-7ን አንብብ። አይምሮህ በጭንቀት ከተሞላ መዋጋት አትችልም። የእግዚአብሄር የውስጥ ሰላም ከውጫዊ ሀሳብና ጭንቀት ይጠብቃል።

ቆላ 3፡13-17ን አንብብ፡፡ በልብ ውስጥ የእግዚአብሄር ሰላም ሲሰፍን ብቻ ነው ለጦርነት በብቃት የታጠቅን የምንሆነው፡፡

አንድ ሰነፍ፣ ያልተነቃቃ ክርስቲያን መሆን የአዲስ ኪዳን እምነትን መካድ ነው፡፡ እንደ ጳውሎስ ምክር እግሮቻችን ሲጫሙ፣ በፍላጎትና በተሟላ ዝግጁነት ወደስራ መንቀሳቀስ እንችላለን፡፡ መነቃቃት እንዲሁ የቴፕራመንት ጉዳይ ብቻ አይደለም፤ በልብ ውስጥ የወንጌል ስራ ውጤት ነው፡፡ የሰላምን ወንጌል ቀምስን ከሆነ ደግሞም የሚሰጠውን አስገራሚ በረከት አይተን ከሆነ በእግሮቻችን የወንጌል ጫማዎች አድርገን ለመጠቃት አንጠብቅም፣ ወደ ጦር ሜዳ እንበራለን እንጂ፡፡

በ2 ኛው የአለም ጦርነት ፍጻሜ ላይ (1945)፣ በብሪታንያ ውስጥ ሁሉም ሸቀጥ አንሶ ነበር ህዝቡም ምግብ፣ ልብስና የቤት ዕቃ ለማግኘት ራሽን/ኮታ መጠቀም ነበረባቸው፡፡ የስፖርት ጫማዎች መግዛት አይቻልም ነበር ትምህርት ቤቶች ግን ልጆች የሚጠቀሙበት ጥቂት ነበራቸው፡፡ ልጆቹ እነዚህን ልዩ የሆኑ ጫማዎች ለሰውነት እንቅስቃሴ ወይም ለጨዋታዎች እንዲያደርጉ ሲፈቀድላቸው ትልቅ ቀን ነበር፡፡ የትምህርት ቤቱ ጊቢ ያለጥንቃቄ ላይና ታች በሚረግጡ ትናንሽ ወነዶችና ሴቶች ልጆች ይሞላል፡፡

ይህ የእግር ጫማ የሰጣቸው መነሳሳትና ጉጉት የማይታመን ነበር! በተማሳሳይ መንገድ፣ ክርስቲያን በሰላም ወንጌል እግሩ ሲጫማ በአምላኩና በአዳኙ ስም ለመዋጋት ዝግጁና ጉጉ ይሆናል፡፡

ልበሰው

የእግዚአብሄር ሰላም በልባችን ሲገዛ እና መተማመናችን ባለማወላወል በወንጌል እውነት ላይ ሲያርፍ ይህ የእግር ጫማ ተደርጓል፡፡

7. የእምነት ጋሻ

“በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤” (ኤፌ 6፡16)፡፡

የቁጥር 16 መግቢያ ሐረግ፣ “በሁሉም ላይ ጨምራችሁ” ለተጨማሪ ጊዜ የእግዚአብሄር የጦር እቃ ሁሉ እንደሚያስፈልገን ያስታውሰናል፡፡ ቀበቶው፣ የደረት ጥሩርና ጫማ ዋና ናቸው፣ በቂ ግን አይደሉም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሄር ሌላ ሶስት መሳሪያዎችን ይሰጣል፡፡ የመጀመሪያዎቹን 3 መሳሪያዎች “እንድንወስዳቸው” ነው የተነገረን፡፡

> **የመጀመሪያዎቹ ሦስት ክፍሎች ይብዛም ይነስም ዝም ያሉና አዘጋጂ ናቸው፤ ወታደሩ ይለብሳቸዋል ደግሞም ይጠብቃቸዋል፡፡ ወደ ሁለተኛው ቡድን ስትመጣ ግን ወዲያውኑ የእንቅስቃሴ ጥቆማ አለ፡፡ ወታደሩ በብርጌዱ ውስጥ በክፍሉ ቁጭ ብሎ የእረፍት ጊዜ እየወሰደ ሊሆን ይችላል ቢሆንም ግን በእውነት መታጠቂያውን፣ የደረት ጥሩርና ጫማውን አድርጎ ነው ያለው፡፡ ከዚያ በድንገት ጠላት እያጠቃ እንደሆነ ደወል ተደወለ ወዲያውም ጋሻውንና ሰይፉን ይይዝና የራስ ቁሩን አድርጎ ይሮጣል፡፡ በምታርፍበት ሰአት በእጅህ ጋሻ አትይዝም፤ ታስቀምጠዋለህ፤ ሰይፍህንም እንደማ፡፡ ጠላት ግን በተንቀሳቀሰ ሰአት እነዚህን ነገሮች ማንሳት አለብህ ለውጊያው ዝግጁ እንድትሆን፡፡**
>
> *ዲ. ኤም. ሎይድ. ጆንስ*

የሮማን ወታደር ጋሻ በጣም ትልቅ ነበር፡፡ በቅርጽ አራትማዕዘን ነበር ልክ እንደበር፡፡ ልኬቱ 1.3 ሜትር * 0.75 ሜትር ሆኖ ፣ከእንጨት የተሰራ ነበር የላይኛውም ክፍል በጠላት “የሚንበለበሉ ፍላጻዎች” እሳት የማያቃጥለው መከላከያ በሚሆን በቆዳ ወይም በብረት ገበር የተሸፈነ ነው፡፡ በጠላት ላይ ከመወርወራቸው በፊት እንዲነዱ የሚደረጉ በዙሪያ የተጠመጠሙ የሚነዱ የብረት ጫፎች ያሏቸው ስለሆኑ እነዚህ ቀስቶች ገዳዮች ናቸው፡፡ የታለሙት ዘልቀው እንዲገቡ ብቻ ሳይሆን ለማቃጠልና አሰቃቂ ጉዳት ለማድረስም ነበር፡፡ እንዲህ ላሉት ቀስቶች ብቸኛው በቂ የሆነው መከላከያ ጋሻ ነበር፡፡

የሚንበለበሉ ፍላጻዎች

በመንፈሳዊ ውጊያ ጠላታችን ዲያብሎስ ብዙውን ጊዜ በእኛ ላይ የሚንበለበሉ ፍላጻዎችን ይወረውራል፡፡ መጋደላችን ከሰይጣንና ከጨለማ ሀይላት ጋር እንጂ ከደምና ከስጋ ጋር

እንዳልሆነ የቁ 12ን እውነት በፍጹም መዘንጋት የለብንም። ሰይጣንን ወንዶችና ሴቶቸን ይጠቀማል እኛን ለማጥቃት፤ ነገር ግን በጦርነቱ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ የሰዎችን ትችት ወይም የጠላትን ማሳደድ ጭምር ቢሆን ስንቀበል አይደለም። እስከተወሰነ ድረስ እነዚህን ነገሮች መረዳት እንችላለን ደግሞም እንቋቋማቸዋለን። ከባዶቹ ችግሮች በአእምሮአችንና በሃሳባችን ላይ ቀጥተኛ የሆኑት ሰይጣናዊ ጥቃቶች ናቸው። ጳውሎስ እነዚህ ጥቃቶች የሚንበለበሉ ፍላጻዎች ብሎ ሲገልጻቸው፣ ስዕላዊ ቋንቋ እየተጠቀመ አይደለም። በጣም ትክክለኛ አገላለጽ ነው።

> የሚነዱ ቀስቶች መብሳት ብቻ ሳይሆን የበሱት ነገር በእሳት ይያያዛል፣ በእጥፍ ሁኔታ አደገኛ ናቸው። ስለዚህ እዚህጋ እንደሰይጣን የቁጣ ጅማሬ ምልክት ሆነው ያገለግላሉ። የእሳትን ቀስቶች፣ በእምነት ጋሻ ካተጠበቀ በቀር ፈጥኖ በሚጠፋው በአማኙ ነፍስ ላይ ያርከፈክፋል። አንዳንድ ጊዜ በአእምሮ ድርጊት ህግ መጠየቅ የማይችሉ ደግሞም መረሳት የማይችሉ አስፈሪ ፣ ያልተቀደሱ፣ የስድብ፣ የጥርጥር፣ ክፉ ሀሳቦች፣ በአእምሮ ላይ መጉረፋቸው ለእግዚአብሄር ህዝብ የተለመደ ተሞክሮ ነው። ልክ እንደሚቃጠሉት ቀስቶች ይለጠፋሉ፤ ነፍስንም በስቃይ ይሞላሉ። ለእርዳታ ክርስቶስን በመጥራት በእምነት ብቻ ነው መጥፋት የሚችሉት ። ይሁን እንጂ እነዚህ ብቸኞቹ የሚቃጠሉ ወንጭፎች አይነቶች አይደሉም፤ በጣም አስጊዎቹም አይደሉም። የሚስተው ልባችን ሊያጠፋው የማይፈጥነውን፣ ትልቅ ጉዳተትና ጥፋትንም ጭምር እስኪያደርግ እንዲቃጠል ብዙ ጊዜ የሚፈቀድለትን፣ ነበልባል በማምረት ፍላጎትን የሚያነሳሱ፣ ምኞትን የሚያቀጣጥሉ፣ ስግብግብነትን (ለማግኘት መሳሳትን)፣ ትምክህትን፣ አለመርካትን ወይም እኔነትን የሚቀሰቅሱ ሌሎች አሉ። በእነዚህ የክፉው አደገኛ መሳሪያዎች ላይ፣ ብቸኛው መከላከያ እምነት ነው።
>
> *ቻርለስ ሆጅ*

በቅርብ ይዳኑም ለአምሳ አመታት አማኞች ይሁኑም፣ ሁሉም ክርስቲያኖች እነዚህን ጥቃቶች ይለማማዳሉ። የማርቲን ሉተርን መረጋጋትና ጥንካሬ አመላክተን ነበር ቀደም ብለን፣ ከእነዚህ ከሚንበለበሉ ፍላጻዎች ግን እንዳይነኩት የተከተበ አልነበረም። የእርሱ ዝነኛ ታሪክ አለ፤ በክፍ ውስጥ የዲያብሎን መኖር ያወቀበት አንድ ቀን ነበር የቀለም ገንቦን በክፉው ላይ የወረወረበት።

እነዚህ ቀስቶች እኛ ላይ እንደተተኮሱ አስብ፤ ስለዚህ ከእኛ አይደለም መነሻቸው። ይህንን ማስታወስ ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም እነርሱን በመጠቀም አንዱ ዋናው የዲያብሎስ ሃሳብ እኛን ተስፋ ወደመቁረጥ ማምጣት ነው። በዚህ መንገድ ካሰብንና ከተሰማን ክርስቲያኖች መሆን እንደማንችል እንድናምን ይፈልጋል።

እነዚህ ቀስቶች ብዙ መልክ ሊኖራአቸው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ለማንበብ ስንሞክር ይመጣሉ ትኩረታችንም ይጠፋል። ብዙ ጊዜ በጸሎት ጊዜ አእምሮአችን በሁሉም ጉዳዮች ላይ ይቅበዘበዛል፤ ስብከትም ስንሰማ እንዲሁ ሊሆን ይችላል። እነዚህ የሰይጣን ጥቃቶች ናቸው፣ ቀስቶች ወደ አይምሮአችን ይወረወራሉ ከቅዱሳት መጻህፍትና ከጸሎት እንዳናተርፍ። ይሁን እንጂ ከሁሉም የሚከፉት ወደ እኛ የሚመጡት ክፉ ሃሳቦች ናቸው - ማንም ሌላ ሰው ቢያውቃቸው በጣም የምናፍርባቸው ሃሳቦች።

> ዲያብሎስ አንዳንድ በጣም የተከበሩ ቅዱሳንን በአስነዋሪ ሃሳቦች መቷቸዋል - እግዚአብሄርን በመሰድቡ አስነዋሪ ሀሳቦች፣ ስለጌታ ኢየሱስ አስነዋሪ ሃሳቦች። አሰቃቂ፣ ዘግናኝ! ደግሞም . . . ዲያብሎስ እንዲሆን ተስፋ የሚያደርገውና የሚያምነው በጥቃት ላይ ያሉት ቅዱሳን የራሳችን ሀሳብ ነው ብለው እንዲወስዱና ክርስቲያን መሆናቸውን እንዲጠራጠሩ ነው። ወይም ዲያብሎስ ቃላትንና ሐረጎችን፣ ርግማኖችን፣ አስጸያፊ ንግግሮችን በክርስቲያኖች ላይ ይወረውራል። አስተሳሰቡ በእነዚህ የተሞላ ይመስላል። አንዳቸውም ግን ከአማኙ ከራሱ አይነሱም። ሊያናውጠው ከሚሞክር፣ ሊያደናግረው ከሚሞክር፣ ክርስቲያን እንዳልሆነ ሊያሳምነው ከሚሞክር፣ በፍጹም ክርስቲያን እንዳልሆነ ከሚሞክር ከዲያብሎ ነው የሚመጡት።
>
> *ጄ. ሌም. ሎይድ. ጆንስ*

ጋሻ

ለእነዚህ ጥቃቶች ብቸኛው መልስ እምነት ነው። “በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።” (1 ጴጥ 5፡8-9)። የእምነትን ጋሻ እንዴት ነው የምናነሳው? ስለ እግዚአብሄር ጸጋ የምናውቀውንና የምናምነውን በጸጥታ በማዛመድ፣ የጠላትን ቀስቶች ለመመለስ። ሌሎቹን የጦር ዕቃዎች ለተወሰነ አደጋ መጠቀም ነው። በድንገት በጥቃት ውስጥ ነህ። ጸንትህ መቆምና በፍጠነት ምላሽ መስጠት አለብህ (ጫማዎቹ) እውነትን በመጠቀም (ቀበቶ)ና በክርስቶስ ጽድቅ ብቻ በመታመን (የደረት ጥሩር)።

እምነት በግልጽ የሚያካትተው የምናምነውን ነው ነገር ግን ከዛ በላይ ነው። እምነት ሁልጊዜ በስራ ይገለጣል ብቸኛ ስራውም ከራስ ወጥቶ ወደ ልኡል እግዚአብሄር ፍቅርና ጸጋ ማመላከት ነው።

የሰይጣን እቅድ ሁልጊዜ ራሳችንን እንድንመለከት ነው። አንዳንድ ጊዜ የምናየውን ነገር እንወደዋለን። መልካም ክርስቲያኖች እንደሆንን እናስባለን በርግጥ ከብዙዎቹ የተሻልን እንደሆንን፤ በነገራችን ላይ ከገንዘባችን አስራት እናወጣለን የጸሎት ስብሰባ በፍጹም አንተውም . . . ይህ ማለት የትምክህት ቀስት ምልክቱን አገኘ ማለት ነው። በሌላ ጊዜ (ምናልባትም ብዙውን ጊዜ) ተቃራኒው ነው የሚሆነው። ጸሎት አስቸጋሪ የክርስትና ህይወትም ከባድ ትግል ሆኖ እናገኘዋለን ክርስቲያን ነን ወይ ብለን እስከምንጠይቅ ድረስ። የጥርጥርና የተስፋ መቁረጥ ቀስቶች ጎጆ ሰርተዋል ቤትን ። ለእነዚህ ሁለት ችግሮች የእግዚአብሄር መፍትሄ የእምነት ጋሻ ነው።

> እምነት በታላላቅ ሰዎች ብቻ የሚገኝ ትልቅ መስፈርት እንዳልሆነ አስታውስ። በተወሰኑ ጥቂት ሰዎች የሚገኝ በጎ ነገር አይደለም። ጥቁር ነጭ እንደሆነ ወይም በጣም በርትተን ከተመኘን ብቻ የምንመኘው ነገር እንደሚሆን ራሳችንን የምናሳምንበት ችሎታ አይደለም ። እምነት ማለት በቃ አይምሮአችንን ከእግዚአብሄር ተስፋዎች ጋር ማስተካከል ነው። የምድር ሁሉ አምላክ እንደማይዋሽ ፍጹም በሆነ ርግጠኛነት።
>
> *ኤ. ደብሊው. ቶዘር*

እምነት ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሄርና ወደተስፋ ቃሎቹ ነው የሚያሳየን። በሮሜ 4፡18-21 ውስጥ በአብርሃም ህይወት ስላለ እውነተኛ እምነት የጳውሎስ ገለጻን አንብብ። የእግዚአብሄርን የተስፋ ቃል በማመን ለእግዚአብሄር ክብር በመስጠት በእምነቱ በርትቶ ነበር። በሌላ አነጋገር፣ አይኖቹ በራሱ ብርታት ወይም ድካም ላይ አልነበረም የተተከሉት በእግዚአብሄር ላይ እንጂ፡ ጌታ እንዲህ አለው፡ “አብርሃም ሆይ አትፍራ፣ እኔ ጋሻህ ነኝ” (ዘፍ 15፡1)፡ ተስፋ ሰጪውን እንዲያምን አደረገው። እግዚአብሄር ለህዝቡ ሁሉ ተመሳሳይ ተስፋ ይሰጣል።

በመዝ 3 ውስጥ ዳዊት እየተጠቃ እንደነበር እናነባለን። ብዙ ጠላቶች በእርሱ ላይ ተነስተው ነበር። እግዚአብሄርም እንደማይረዳው ይናገሩ ነበር። ዳዊት ግን ከእነርሱ የተሻለ ያውቃል፡ “አ ጌ ሆይ አንተ ግን በዙሪያዬ ጋሻ ነህ” (ቁ 3)። በመዝ 28፡7 ተመሳሳይ አዋጅን ይናገራል - “እግዚአብሔር ኃይሌና ጋሻዬ ነው፤ ልቤ በእርሱ ታመነ እኔም ተረዳሁ፤” እኛም እንዲህ ያለ

መተማመን ሊኖረን ይችላል ምክንያቱም ጌታ “በእርሱ ለሚታመኑት ጋሻ ስለሆነ” (ምሳሌ 30፡5)። የሮማ ወታደር በጦር ሜዳ ውስጥ ከጋሻው በስተጀርባ ይደበቃል፤ እኛም በጌታ ሀይልና ተስፋ ማመን በሆነው ከጋሻችን ጀርባ መደበቅ አለብን።

አእምሮ

እነዚህ የሚንበለበሉ ቀስቶች ከእኛ አይደለም መነሻቸው። ጠላታችን በእኛ ላይ የሚተኩሳቸው ናቸው ዋናው አላማው አይምሮአችን ነው። የምናስብበትን መንገድ ላይ ዲያብሎስ ተጽኖ ካደረገ፣ ድል ያደርጋል። የምናደርገው እያንዳንዱ ነገር በአይምሮአችን ቁጥጥር ስር ነው። ከንፈሮቻችን ከመዋሸታቻው በፊት ሀሳቦቹን አይምሮአችን ወልዷቸዋል።

እዚህጋ መጠንቀቅ አለብን ምክንያቱም አንዳንዴ ሀጢአት በደጅ ወደሆነበት ሁኔታ ራሳችንን ልናገኘው እንችላለን። የሆነ አይነት መጽሐፍ በሴክስና በመጥፎ ቃላት የተሞላ ወይም የሆነ የቴሌቪዝን ሮግራሞችን ካየህ ይህ አስተሳሰብህ ላይ ተጽኖ ያደርጋል። የዚህ ምክንያት የዲያብሎስ የሚነበለበል ፍላጻ የገዛ ራሳችን ፈቃደኛ የሆነ አለመታዘዝ እንጂ፤ መፍትሄውም የእምነት ጋሻ አይደለም ንስሃና ለእግዚአብሄር ፈቃድ መታዘዝ ነው።

በየትኛውም መንገድ ግን አእምሮ ከጥቃት ውስጥ ነው ስለዚህም፣ አዲስ ኪዳን ስለክርስቲያን አእምሮና አስተሳሰብ ብዙ የሚለው ነገር ቢኖር የሚያስገርም አይሆንም።

“የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” ሮሜ (12፡2)

“ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። (ሮሜ 5፡8)

“በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤

ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፤ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።” (ፊሊ. 4፡8-9)

እንደ ክርስቲያን የመኖር ብቸኛ መንገድ እንደክርስቲያን ማሰብ እንደሆነ ተመልክተናል። እንደ ክርስቲያን የማሰብ ብቸኛ መንገድም ደግሞ በጸሎትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ክክርስቶስ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ ነው። አእምሮአችን በክርስቶስ ከተሞላ የሚንበለበሉ ፍላጻዎች ምንም ጉዳት አያመጡብንም።

አንሳ

የእምነትን ጋሻ እናነሳለን፣ የሆነ መንፈሳዊ ስሜትን ለማምጣት በመሞከር ሳይሆን ዲያብሎስ ሲያጠቃ ወደ እግዚአብሄር በመሸሽ ነው። እምነት በቀጥታ ወደ እግዚአብሄር ነው የሚያደርሰው።

እምነት ግን እንክብካቤና መመገብ ይፈልጋል፤ ይህ ደግሞ በአምላካችን ህልውና ብቻ ይከናወናል።

> በክርስቶስ ህልውና ውስጥ ልማዳዊ ህያው እምነትና ለመረዳት ዝግጁነት የክርስቲያን ወታደር በስኬት የመዋጋት ምስጢር ነው። እምነት መጠኖች እንዳሉት በፍጹም መረሳት የለበትም። ሁሉም ሰዎች እኩል አያምኑም አንድም ሰው እንኳን የእምነት መውረድና መውጣት አሉት። በሆነ ጊዜ ከሌላ ጊዜ ይልቅ የበለጠ ከልቡ ያምናል። በእምነቱ መጠን መሠረት ክርስቲያን በጥሩ ወይም በመጥፎ ሁኔታ ይዋጋል ድል ያገኛል ወይም የአልፎ አልፎ ድካምና ሽንፈት ይገጥመዋል፤ ከድል ይጎድላል ወይም ድል ያደርል።የበለጠ እምነት ያለው ምንጊዜም ደስተኛ እና ዘና ያለ ወታደር ይሆናል። እንደ ክርስቶስ ፍቅርና ቀጣይነት ያለው ጥበቃ ማረጋጋጫ የጦርነት ጭንቀቶች በሰው ላይ ቀለል ብሎ እንደሚቀመጥ የሚያደርግ ምንም ነገር የለም። ክርስቶስ ከጎኑ እንደሆነና ድል ርግጠኛ እንደሆነ ወሰጣዊ እርግጠኛነት ያለ የመጠበቅን፣ የውጊያን እና ከሀጢአት ጋር የመታገልን ድካም እንዲሸከም የሚያስችለው ምንም ነገር የለም።

ጄ. ሲ. ራይል

8. የደህንት የራስ ቁር

“የመዳንንም ራስ ቁር ያዙ” (ኤፌ 6፡17)

የራስ ቁር አላማ የወታደሩን ራስ መከላከል እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ውጊያ የአእምሮአችን፣ የማስተዋላችንና የአስተሳሰባችን ጥበቃ አስፈላጊነት ትኩረትን ይስባል ጳውሎስ፡፡ ከጠላት ጥቃት አስተሳሰባችንን ስለመጠበቅ በአጭሩ ተመልክተናል ፡፡ ይህም ደግሞ በፍጹም በብርቱ አጽኖት ሊሰጥበት የማይቻል ነጥብ ነው፡፡ እዚህጋ በክርስቲያን መረዳትና አመለካከት የተወሰነ ሁኔታ ላይ ማተኮር አለብን፡፡

ሁሉንም ትክክለኛ ዶክትሪኖች ልታምን ደግሞም የእምነትን ጋሻ በዘዴ ልታነሳና ከዲያብሎስ የሚንበለበሉ ፍላጻዎች ጋር ዲል በማድረግ በዚህ መንገድ በክርስትና ህይወት በበቂና በሚያረካ ሁኔታ ልትሄድ ትችላለህ፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን ይደክምሀል፣ ይታክትሃል፣ ውጊያውም ተስፋ ሊያስቆርጥህ ይጀምራል፡፡ ይህ ለምኔ ነው ይህን ውጊያ መዋጋት ይገባልን? ክርስትናን በጣም አጥብቄአለሁን? በቤተ ክርስቲያንና በመንፈሳዊ ነገሮች ላይ ብዙ ጊዜ እያሳለፍኩ ነውን? በማለት መጠየቅ ትጀምራለህ፡፡ በርግጥ ሌሎች ፍላጎቶችን መፈለግ ነበረብኝ፡፡ ከክርስትና ጓዜን ጠቅልዬ መሄድ አለብኝ ትላለህ፡፡

በሌላ መንገድ ሊሆንም ይችላል፡፡ ከራስህ ወደ ውጭ ታይና ክርስትና ትንሽ ውጤት ብቻ እንዳመጣ ይሰማሀል፡፡ ምናልባት በአንተ እድሜ ካሉ ጥቂት ክርስቲያኖች ጋር በአንድ ትንሽ ህብረት ውስጥ ነህ፡፡ ወደ አለም ትዕይንት ትመለከትና በሰሜን አየርላንድ ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶች፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በሊባኖስ ውስጥ እርስ በርስ ሲገዳደሉ ዜና ትሰማለህ፡፡ በነዚህ ነገሮች ላይ ስትቆይ፣ ህይማኖት ጊዜ ከማባከንና ከግብዝነት በቀር ምንም እንደሌለው ትደመድማለህ፡፡

ይሄ ምንም አይነት ቅርጽ ይውሰድ፣ ለህይወት ያለህን መረዳትና አመለካከት እያጠቃ ያለው ዲያብሎስ ነው፡፡ ከእነዚህ ጥቃቶች ጋር ዲል ማድረግ ያለብን እንዴት ነው? ከቅዱሳት መጻህፍት ከምናገኛቸው ብዙ ምሳሌዎች መማር አለብን፡፡

ተስፋ የቆረጡ የዕብራውያን ክርስቲያኖች

የዕብራውያን መልእክት የተጻፈው ወደ ክርስትና ለመጡ አይሁድ ነበር። ዳግም የተወለዱ አማኞች ነበሩ ነገር ግን በጣም ከባድ ጊዜን እያሳለፉ ነበር። አይሁድ ወገኖቻቸው እንደ ከዳተኞች ቆጥረዋቸው ደግሞም በመራራ ሁኔታ አሳደዋቸው ነበር። አንዳንዶቹ እስከሞት ተወግረዋል እነርሱም አህዛብ ክርስቲያኖች የማያውቁት መከራ ገጥሞአቸዋል።

> ለሁሉም እስራኤላውያን በተሰጡ በረከቶች ተባርከዋል፤ በመቅደሱ የተዋበና እግዚአብሄር ያዘዛቸው አግልግሎቶች ተቋዳሽ ሆነዋል፤ አሁን ንጹህ እንዳልሆኑና እንደከዳተኞች ተቆጥረዋል። በኢየሱስ ማመናቸውን ካልተው በቀር እና በአንድ ላይ መሰብሰባቸውን ካልተዉ በቀር ወደ ቤተ መቅደስ መግባት አይፈቀድላቸውም ነበር፣ ከመሰዊያው፣ ከመስዋእቱ፣ ከሊቀክህነቱ፣ ከያህዌ ቤት ተወግደዋል።
>
> ውስጠኛው ልባቸውን ያቆሰለውን ሰይፍ ምንም ያህል መረዳት አንችልም። መሲሁን በመከተላቸው ከመሲሁ ሰዎች መከራ መቀበል በርግጥም አስጨናቂ መከራ ነበር፤ ለእስራኤል ክብር ተስፋ እግዚአብሄር ከመረጠው ስፍራ፣ መለኮታዊ ህልውና ከተገለጠበት፣ ምልክቶችና ዜና መዋእሎች፣ የአባቶቻቸው ደስታና ብርታት ከነበሩባቸው ተወግደዋል፡ ከእንግዲህ የቃል ኪዳኑና የቤቱ ልጆች አይደለም፣ ከአህዛብ በከፋ ሁኔታ ከውጨኛው አደባባይ ተባረዋል፣ ከእስራኤል የጋራ ንብረት ተቆርጠዋል።ይህ በርግጥ ቁስልና ረቂቅ ፈተና ነበር።
>
> *አዶልፍ ሳፊር*

የዚህ ውጤት በጣም ተስፋ መቁረጣቸው ነበር። በርግጥ ይህ ይገባው ነበርን? ለቀደሙት በአላት መናፈቅ ጀመሩ፣ በተለይም በእነርሱ በኩል ስለነበረው ሊከክህንነት። የጌታ ኢየሱስን ደግሞ የክበር መምጣት ይጠብቁ ነበር። ይህ ግን የሚፈጸም አልሆነም። ሁሉም ነገር የተበላሸ መሰለ። ምናልባት ክርስትናን በተውና ወደ አይሁድ ማህበር በሄዱ ደህና ይሆኑ ነበር።

ለዚህ አይነቱ አስተሳሰብ የእግዚአብሄር መፍትሄ የደህንነት ቁር ነበር። በሌላ አነጋገር፣ በመልእክቱ ሁሉ የክርስቶስን መብለጥ ያስታውሳቸዋል።

ግራ የተጋባው ዘማሪ

መዝሙር 73 በተመሳሳይ ሁኔታ ያን የእግዚአብሄር ሰው ያሳየናል። የማያምኑትን መመልከትና በእነርሱ መቅናት ስለጀመረ እምነቱ ጠፋ (ቁ 2-3)። ለእነርሱ ሁሉም ነገር ቀላል

ነው (ቁ 4-5)። ወደው ሀጢአት እያደረጉ በእርሱ ይኖራሉ (ቁ 6-12)። ድምዳሜው ለእግዚአብሄር ለመኖር በመሞከር ጊዜውን እያባከነ እንደነበር ነው (ቁ 13-14)።

እዚህም ጋ አመለካከቱን እያጠቃ ዲያብሎስ በስራ ላይ እንደሆነ እንመለከታን። "አውቅም ዘንድ አሰብሁ፥ ይህ ግን በፊቴ ችግር ነበረ።" (ቁ. 16)። የእግዚአብሄርን መንገዶችና አላማዎች ማስተዋል ሲጀምር ብቻ ነበር መልሱ መገኘት የቻለው (ቁ. 17-28)።

ተስፋ የቆረጠ ክርስቲያንም ይሁን ወይም ግራ የተጋባ ዘማሪ ችግሩ ተመሳሳይ ነው።

> አንዳንድ ጊዜ ዲያብሎስ ሁሉን የሚሸፍነውን ዋናውን እውነት በመርሳት በክርስትና ህይወት ዝርዝር ጉዳይ እንድንያዝ ያሳምነናል።እንጨቱን ረስተን ስለዛፉ ግድ እንሰኛለን፤ ታላቁን ዘመቻ ረስትን በትናንሽ ዘዴዎች እንነከራለን ። "አለም ለእኛ በጣም ብዙ ናት።" ማንነታችንን ረስትን ስለቀኑ ሙቀትና ጫና ለማሰብ ጎበዞች ነን፣ ለምን አላማ እንደተወሰንን እንረሳለን። የዚህ ሁሉ ውቴት፣ በርግጥ ወደፊት መሄድ እንደማንችል ሊሰማን ይጀምራል፣ ያ ለእኛ በጣም ብዙ ነው፣ "ትግላችን ሁሉ በከንቱ" ነው፣ መቁሰላችን ሁሉ በከንቱ ነው። ዲያብሎስ በጣም ብርቱ ለእኛ በጣም ረቂቅ እንደሆነ ይሰማናልን፤ እኛን ለማሸነፍ እርግጠኛ ነው።
>
> *ዲ. ኤም ፤ ሎይድ ጆንስ*

የራስ ቁር

ይህንን የተለየ የጥቃት አይነት ደህንነት እንደ ራስ ቁር የሚያገልግለው በምን መንገድ ነው? "የደህንንተት ራሰ ቁር" ማለት ስለደህንነት መገንዘብ ማለት ነውን? ስለዳንን በጣም አስጨናቂ የሆነ ጠላቶችንም ልናገኝ እንችላለን ደግሞም መትረፍ ብቻ ሳይሆን ድል ለማድረግ በመተማመን መጠበቅ እንዳለብን ማሰብ አለብንን? በርግጥ ይህ የሱ ክፍል ነው ግን ከዚያ ያለፈ ነገር አለው። ሙሉ ትርጉሙን በ1 ተሰ 5፡8 ውስጥ እናገኘዋለን - "እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤"

በአዲስ ኪዳን ውስጥ "ተስፋ" የሚለው ቃል ሁልጊዜ ስለወደፊት ያመለክታል ሁልጊዜ ሙሉና ፍጹም ርግጠኛነት ማለት ነው። ስለ ክርስቲያን ተስፋ ምንም ርግጠኛ ያልሆነ ነገር የለም። አሁን የዳንን ስለሆንን ሁልጊዜ እንደምንድን የተረጋገጠ ተስፋ ያለን መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተዋጁት ደግሞ ሲመጣ ደህንነታችን ይበልጥ የክበር መሆኑ ነው። ያኔ

ደህንነታችን የመጨረሻና የተሟላ ይሆናል፤ ከሀጢአት ቅጣትና ዉጤት ነጻ መሆናችን ብቻ ሳይሆን ከእርሱ ሀይልና ተጽኖም ጭምር ነው እንጂ።

ስለዚህ ዲያብሎስ መረዳታችንን ሊያዛባና ውጊያ እንድናቆም ተስፋ ሊያስቆርጠን ሲመጣ የደህንንተ ተስፋን የራስ ቁርን ማድረግ አለብን። ከአሁኑ ጊዜ ችግሮች ይልቅ የወደፊቱን ክብር እናያለን። ሲኒክ "ያ ስትሞት በሰማይ ትንሽ ቁራጭ" እንደሚሆን ያስረዳል። እንደዛ አይደለም። ክርስቲያን በመሆን ውስጥ የአሁን ክብርና ደስታ አለ። ተስፋ መቁረጡ ልክ አይደለም አንዳንዴ የሚሆን እንጂ። ብርቱ የሆነ መከራዎችን ሊያመጣ ይችላል ነገር ግን "ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።" (ሮሜ 8፡18)። ይህ የራስ ቁር፣ የክብር ተሰፋ ነው።

ለዚህ በማቴ 24 ውስጥ የክርስቶስ አስተምህሮ ምሳሌ አለ። "ስለዘመን መጨረሻ" የሚሰጠው መግለጫ ከባድና አስፈሪ ነው (ቁ 6-11)። በሁኔታው ላይ ለማትረፍ ዲያብሎስ ፈጣን ይሆናል ስለዚህም የብዙዎች "ፍቅር ይቀዘቅዛል" (ቁ 12)። ኢየሱስ ግን ""ጸንትን እንድንቆም" ይናገራል (ቁ 13)። በእንዲህ ያለ በእምንታችን መጠቃት ጊዜ ጸንቶ መቆም እንዴት ይቻላል? መልሱ በቁ 30 እና 31 ውስጥ አለ። ፍጹም የሆነው ርግጠኛነት ተስፋው ነው - ደህንነታችን ለእኛ እንደሚመጣ።

በ2 ቆሮ 4 ውስጥ ተመሳሳይ አመለካከት አለ። በቁ 6 ውስጥ በዳንን ጊዜ የሚያስደስት አዋጅ አለን፡ "እግዚአብሄር . . . በልባችን ብርሃን አብርቷል" . . ."። ወዲያው ይህንን ብርሃን በመከተል "በከባድ ችግር ገለጻ ጋር ተጋጥመናል (ቁ 7-10)። የጨለመው ልቡ "በክርስቶ በእግዚአብሄር ክብር እውቀት ለበራው" ሰው ችገሮቹ እነዚህ ናቸው። ሰውየው እንዴት ነው የሚቋቋማቸው? መልሱ በቁ 14 ውስጥ ይገኛል፡ እንደገና እዚህጋ ፍጹም ርግጠኛነት ወይም የከብር ተስፋ እንዳለ እናውቃለን። "ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።" (ቁ 16-18) በማለት ጳውሎስ ይቀጥላል።

ልበሱት

የደህንነት የራስ ቁር የሚለበሰው በዚህ መንገድ ነው፤ በሚመጣው ክብር ላይ አይኖችህን አድርግ፣ በእርሱም ሃሴት አድርግ። ከፊታችን እንዲህ ያለ ደስታ እያለ እንዴት ነው ልባችን ዝሎ ተስፋ የምንቆርጠው?

ስለዚህ የደህንነት የራስ ቁር ትርጉም ይህ ነው። አይምሮህ በጥርጥርና በሀዘን ተሞልቷል። ጠላት ሁሉንም ተወው ይልሃል። አንተም ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ ነገር ግን ድኛለሁ ደግሞም የደህንት ታላቅ ታስፋ አለኝ በማለት ትመልሳለህ። በዚህ ጊዜ ነገሮችን ወደ ስፍራቸው መመለስ እየጀመርክ ነው። አይንህን በማይታየው ነገር ግን በተረጋገጠውና በተባረከው ተስፋ ላይ እያደረግህ ነው።

ለኢየሱስ ተነስ ተነስ

ትግሉ ረጅም አይሆንም

በዚህ ቀን የጦርነት ድምጽ

በሚቀጥለው ቀን የድል አድራጊ መዝሙር።

ለእርሱ ላሸነፈው

የህይወት አክሊል ይሆናል

ከክብር ንጉስ ጋር

ለዘላለም ይነግሳል

ጆርጅ ደፊልድ

9. የመንፈስ ሰይፍ

“የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።” ኤፌ 6፡17)

የጦርዕቃው የመጨረሻ አይነት፣ አጥብቆ ለመናገር በፍጹም የዕቃ ጦሩ ክፍል አይደለም። ሌሎቹ አይነቶች የተወሰነ የአካል ክፍል ለመከላከል የተሰሩ ናቸው፤ ሁሉም መከለከያ ናቸው። ሰይፉ ግን የተወሰነ ክፍል ሳይሆን መላውን አካል ነው የሚከላከለው፤ የሚከላለውም ቁጣውን በማብረድ ሳይሆን ጠላትን መልሶ በመያዝ ነው ። በተጨማሪም፣ መከላከያ ብቻ አይደለም እጅግ በጣም ማጥቂያ መሳሪያ ነው፤ ጠላትን ማጥፋት ይችላል።

ጳውሎስ “የመንፈስ ሰይፍ” ብሎ ይጠራዋል ከዚያም እርሱ ማለት የፈለገውን ማወቃችንን ፍጹም ለማረጋገጥ “የእግዚአብሄር ቃል የሆነው” በማለት ይጨምራል። ሰይጣንን በምንዋጋ ጊዜ ብቸኛ ማጠቂያ የሆነው ይህ ሰይፍ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ነው ደግሞም የተመራ ነው፣ የማያልፈው፣ ትክክል የሆነው የእግዚአብሄር ቃል ነው። በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ የእግዚአብሄር ቃል በጣም ወሳኝ ነው። በገዛ ብርታታችን አንዋጋም ወይም በራሳችን መሳሪያዎች አንዋጋም። የራሳችን ሀሳቦችና አመለካከቶች ጥቅም የለሽ ናቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የእግዚአብሄር ሀይል ክፍል ነው (ቁ 10)። “የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው” (2 ቆሮ 10፡4)።

> (የእግዚአብሄር ቃል) እውነት ብቻ ሳይሆን ሀይልም አለው፣ ነገር ግን እውነተኛ ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ እውነት የሆነ ሀይል። ጌታችን ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ወደረኞቻቸው በሙሉ ሊመልሱት ወይም ሊቃወሙት የማይችሉትን ቃልና ጥበብ ሊሰጣቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ለስህተት፣ ለሀሰት ፍልስፍና፣ ለሞራል የሐሰት መርሆች፣ ለክፉ መሀይምነቶች፣ለዲያብሎስ አስተያቶች፣ በሙሉ ብቸኛው፣ ቀላሉና በቂው መልስ የእግዚአብሄር ቃል ነው። ይሄ የጨለማ ሀይል ሁሉ እንዲረበሽ ያደርጋል። ክርስቲያን በግል ተሞክሮው ይሄ እውነተኛ መሆኑን ያያል። ጥርጥሮቹን ይተዋል፤ ፍርሀቱን ሁሉ ያጠፋል፣ ከሰይጣን ሀይል ነጻ ያወጣዋል። ይሄ የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ተሞክሮም ነው። ቤተ ክርስቲያን በሀጢአትና በስህተት ያላት ድል ሁሉ በእግዚአብሄር ቃል አማካኝነት የመጣ ነው። እሱን እስከተጠቀመች ድረስ ድል መንሳቷን ትቀጥላለች፤ ሌላ ነገር ፣ አመክንዮ፣ ሳይንስ፣ ልማድ/ወግ፣ ወይም የሰዎች ትዛዝ ሊሆን

ይችላል፣ ስትጠቀም የሉን ስልጣን እንዲወስድ ወይም እንዲጋራ ሲፈቀድለት፣ ቤተ ክርስቲያን ወይም ክርስቲያን በጠላት እጅ ነው።

ሲ.ሆጅ

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር እውነት አስተማማኝና ስልጣን የተሞላ እንደሆነ ተመልክተናል (2 ጴጥ 1፡20-21፤ 2 ጢሞ 3፡16)። ከሁሉ የላቀ መሳሪያ ነው፤ ከየትኛውም ሽጉጥ፣ቦምብ ወይም ሮኬት በላይ ሀይለኛ ነው። በመንፈሳዊ ጦርነት ጊዜ የሀይሉ ሚዛን በርግጥ በክርስቲያን በኩል ነው፤ እግዚአብሄር ለእርሱ የሚሰጠው መሳሪያ ጠላት ካለው ምንም ነገር የላቀ ስለሆነ። የመንፈስን ሰይፍ እንዴት መጠቀም እንለበት ካወቀ፣ ክርስቲያን በፍጹም የተሻለ መሳሪያ የያዘ መሆን የለበትም። ነገር ግን ሰይፍ መያዝ አንድ ነገር ነው፤ በርሱ መሰልጠን ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ልክ መፅሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጠ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ውጤታማ በሆነ መንገድ እንድንጠቀምበት የሚረዳን።

መረዳት

መጽሐፍ ቅዱስን ከመጠቀምህ በፊት ልትረዳው ይገባል፤ ከመረዳትህም በፊት፣ ልትረዳው የሚገባ መሆኑን ማመን አለብህ። ካልሆነ ግን እርሱን ለማጥናት ጊዜና ጥረት አትሰጠውም፤ ያለ ጥናትም መረዳት የለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የአእምሮ ስራ ብቻ አይደለም። ልዩ የሆነ ነገር ነው። በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በርካታ መጻህፍት አሉ በፍጹም ልትረዳቸው የማትችላቸው። ያንን ለማድረግ እውቀት ወይም ችሎታ ላይኖህ ይችላል። ክርስቲያን ስለሆንክ ግን መንፈስ ቅደስም ባንተ ስለሚኖር የእግዚአብሄርን ቃል መረዳት ትችላለህ። 1 ቆሮ 2፡6,16ን አንብብ። ክርስቲያን መረዳት ይችላል ምክያቱም "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና።" (ቁ 12)።

እንደማንኛውም ጦርነት ጠላት መሳሪያዎቻችን ሊያጠፋና ሊደመስስ ይፈልጋል። ዲያብሎስ ምን ያህል የመጽሐፍ ቅዱስን እውነትና አስተማማኝነት ላይ ተጽኖ ለማድረግ እጅግ እንደፈለገ ተመልክተናል ነገር ግን እዚያጋ አያበቃም። ክርስቲያኖች በሚገባ የተማሩ ስላልሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስን የበለጡ አስቸጋሪ ትምህርቶች መረዳት እንደሚችሉ ማሰብ እንደሌለባቸው ያደርጋቸዋል። ይሄ ውሸት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተካተቱ በጣም የደክትሪን ትምህርቶች ጥቂቱን የያዘው የሮሜ መልእክት በጣም በተራ ሰዎች ከተመሰረተች፣ ከእነርሱ

ብዙዎቹ ባሪያዎች በሆኑ እዛ ላለች ቤተ ክርስቲያን እንጂ በሮሜ ከዩኒቨርሲቲ ለተመረቁ ሰዎች እንዳልተጻፈ በፍጹም አትርሳ። ጳውሎስ ጽሁፎቹ በጣም አስቸጋሪ እንደሆኑ በፍጹም አላሰበም። በመንፈስ ቅዱስ የበሩ አይምሮዎች ከፈለጉ መረዳት እንደሚች ያውቃል።

መጽሐፍ ቅዱስን ከተራ ሰዎች እንድትከለክል ሰይጣን የሮማን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ተጠቅሟል። አንድ ቅጂ እንዳይኖራቸውም ተከልክለው ነበር። በላቲን ስለነበር ተጽፎ የነበረው ሊያነቡት አይችሉም ነበር። በሰዎች ቋንቋ ተተርጉመው የነበሩ ተፈልገው ተቃጠሉ። እንደዊያም ቲንዴል ያሉ ሰዎች በእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖረን ህይወታቸውን ሰጡ። የፕሮቴስታንት ተሀድሶ ሰዎች በቋንቋቸው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲኖራቸውና የእሱን መለኮታዊ መንገድ እንዲረዱ እግዚአብሄር ተጠቀመበት።

ተሀድሶአውያን መጽሐፍ ቅዱሰን አስተማሩ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን አብርሆት አስፈላጊነት ተገንዝበው ነበር።

> ቅዱሳት መጻህፍትን በራሳችን የተፈጥሮ ስሜትና አመክንዮ መለካት፣ መፍረድና መረዳት የለብንም ነገር ግን በትጋት፣ በጸሎት መንፈስ ማሰላሰልና መመርመር አለብን። የሚያስተምረን ብቸኛ ጌታ መንፈስ ቅዱስ መሆን አለበት ደግሞም በዚህ አስተማሪ ለመማር ወጣቶችና ምሁራን አትፍሩ።
>
> *ማርቲን ሉተር*

> ለገዛ ቃሉ እግዚአብሄር ብቻ ስለሆነ ምስክር ሊሆን የሚችለው፣ በመንፈስ ቅዱስ የውስጥ ምስክርነት እሰኪታተሙ ድረስ እነዚህ ቃላት በሰዎች ልብ ውስጥ ሙሉ ዋጋ አያገኙም።
>
> *ጆን ካልቪን*

የተከፈተ መፅሐፍ ቅዱስ

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ክፈትና ማንበብ ጀምር። እንደዚህ ስታደርግ፣ እያነበብክ ያለኸውን ነገር አስተውል። ልብ ወለድ ፣ ግለታሪክ፣ ጋዜጣ አይደለም፤ የእግዚአብሄር ቃል ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ወደሱ በእውነተኛና በቆራጥ አይምሮ ና። ከመምጣትህም በፊት መረዳት እንዲሰጥህ ጸልይና እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስን ጠይቅ። “ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ።” (መዝ 119፡18)።

መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ መጽሐፍ ነው፤ አንዱ ልዩ ፀባዩም ከመጀመሪያ ማንበብ አለመጀመርህ ነው። ከዘፍጥረት አትጀምር። ከአዲስ ኪዳን የሆነ ነገር መረዳት አለብህ ብሉይ ኪዳን ለአንተ ጠቃሚ መሆኑን ከመረዳትህ በፊት። በወንጌላት ጀምር - ሁሉንም አንብባቸው። (በየትኛውም የክርስቲያን መጽሐፍ ሱቅ ሚገኘውን)፣ *ማርቆስን አንብብ ተማር* የተሰኘውን በጆን ብላንካርድ የተጻፈውን ኖት በመጠቀም በዝግታየማርቆስን ወንጌል አንብብ። ከዚያም ለአጠቀላዩ መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መግቢያ፣ በፒተር ጄፈሪና በኦወን ሚልተን የተጻፈውን *የጽኑ መሠረቶችን* ማብራሪያዎች ተጠቀም። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ያለብህ መቼ ነው? በየለቱ። ስለዚህ ምንም ጥያቄ የለም። ለሁለት አበይት ምክንያቶች በየለቱ መሆን አለበት፡

1) “ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሄር አፍ በሚወጣ ቃል እንጂ” (ማቴ 4፡4)። ታላቁ ጄኔራል ናፖልዮን አንድ ሰራዊት የሚገሰግሰው በሆዱ ነው ብሎ ያምናል። በየለቱ ጥሩ ምግብ ለወታደሮቹ ውጤታማነትና ስኬት አስፈላጊ ነው ማለቱ ነው። እንደ ጌታ ወታደሮች በጦርነቱ እንዲያበረታን በየለቱ መንፈሳዊ ምግብ ያስፈልገናል።
2) የእግዚአብሄር ቃል እንደማያልቅ ጎተራ ነው። አቅርቦቱ በፍጹም ሊያልቅ አይችልም። እርሱን ለመያዝ መጠጋትና አስተምህሮቱን መረዳት ካለብን በየለቱ ልናጠናው ይገባል።

በእግዚአብሔር ቃል የየለት ጊዜህን ለነፍስህ የከበረ አድርግ። በምንም ሁኔታ ቸል አትበለው።

አላማ

ለምን መጽሐፍ ቅዱስን እንደምናነብ ራሳችንን እናስታውስ። በጦርሜዳ ውስጥ ወታደሮች ነን አላማችንም በብቸኛው መሳሪያችን፣ በመንፈስ ሰይፍ አጠቃቀም ራሳችንን ማሰልጠን ነው። የቅዱሳት መጻህፍት እውቀትና መረዳት የተወሰኑ አስፈላጊ ነገሮችን ያደርግልናል።

እንድንድግ ያደርገናል	1 ጴጥ 2፡2
የእግዚብሄርን ማረጋገጫ ያገኛል	2 ጢሞ 2፡15
አስደናቂ ስልጠና ነው	2 ጢሞ 3፡16-17
ሀጢአትን እንድናሸንፍ ይረዳናል	መዝ 119፡ 9-11
የስኬት ብቸኛው መንገድ ነው	ኢያሱ 1፡7-8

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለአንድ ክርስቲያን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ታያለህ። የየለት አምልኮዎችና የየለት ስልጠናዎች አስፈላጊዎች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፣ እርሱን ማጥናት በእርሱ አስተምህሮ ማሰላሰል - እነዚህ የመንፈስን ሰይፍ በውጤታማ መንገድ መጠቀም የሚችል የሰለጠነ ወታደር ብቸኛ መንገዶች ናቸው።

ውድቀት

አንድ ክርስቲያን ለቃሉ በቂ ጊዜና ጥረት ሳይሰጥ፣ ስለዚህም በፍጹም እርሱን ሳይረዳ ሲቀር የሚሆነው ነገር ምንድን ነው?ይህ የምርምር ጥያቄ አይደለም፤ ብዙ ጊዜም ይከሰታል። ይህን ለመመለስ፣ በጳውሎስ የሮማን ወታደር አሳሳል ጋር ተመሳሳይ የሆነ ነገርን እንጠይቅ። አንድ ወታደር ሰይፉን ሳይዝ ወደጦር ሜዳ ቢሄድ ምን ይሆናል? ለመሸነፍ ቀላል ይሆናል። ለጠላት ምንም ማስፈራሪያ አይሰጥም፤ በራሱም በኩል ዕዳ ይሆናል። ጓደኞቹም በእርሱ ላይ ጥገኛ መሆን አይችሉም ደግሞም እርሱን ለማዳን ብዙ ጊዜ ያባክናሉ።

መጽሐፍ ቅዱስን የማንረዳ ከሆነ፣ የተወሰኑ ነገሮች መከተላቸው አይቀሬ ነው። የማናውቀውን ነገር መታዘዝ አንችልም። አለማወቅ ትልቅ የእውነት ጠላት ነው። በክርስትና ህይወት ውስጥ በቀላሉ ብዙ የሀጢአት ስራዎችን ማድረግ ይቻላል ምክንያቱም ስለእነርሱ እግዚአብሄር ምን ማለት እንዳለበት ስለማናውቅ። ይህ መንፈሳዊ እድገትን ወደማጣት ያመጣል። በእምነት ካላደግህና ካልጠነከርህ በጦርሜዳ ውስጥ ትክክለኛ የሀላፊነት ድርሻህን መወጣት አትችልም። በቤተ ክርስቲያን እድገት ውስጥ እዳና ሸክም ትሆናለህ። ዕብ 5፡11-14ን አንብብ።

እንዲህ ከሆነ፣ ውድቀትን ማስወገድ ካለብን፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማወቅና መረዳት አለብን ሁሉንም መረዳት አለብን፤ ግልጽ ክፍሎችን ብቻ ሳይሆን። ቅዱሳት መጻህፍትን በማሰላሰል ትልቅ ዋጋ አለ ነገር ግን የግልጽ ክፍሎችን ዝርዝር መማር ብቻን ልብ በል። በብዙ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ የሚበልጥ ብዙ ነገር እንደሚል በመርሳት የዚህ አደጋ የተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ትምህርትን፣ በተጠናው ጥቅስ መሠረት ብቻ ለማሰብ ማዘንበልህ ነው።

ሁሉንም ቃል ለማወቅ ፍላጎት ይኑርህ። ይህ ጊዜ ይወስዳል ነገር ግን በጣም ከፋይ ነው። በትክክል መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ተራ ሂደት እንዳልሆነ በፍጹም አትርሳ። የእግዚአብሄር ቃል በመንፈሳዊ ሁኔታ መረዳት አለበት። የመንፈስ ሰይፍ ነው መንፈስ ቅዱስም የላቀው የቃሉ መምህር ነው።

ዘዴ የተሞላበት አጠቃቀም

መጽሐፍ ቅዱስን የመረዳት አላማ ፈተና ለማለፍ ወይም ለሰዎች ምን ያህል ጎበዞች እንደሆንን ለማሳየት አይደለም፤ ሰይፉን በሀጢአት ላይ ለመጠቀም ነው። ይህን የምናደርገው እንዴት ነው? ይህን መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ያሳየናል። በርካታ ምሳሌዎች አሉ፤ ዋናው በሉቃስ 4፡1-12 ይገኛል። እዚህጋ ኢየሱስ በዲያብሎስ ሲፈተን እናያለን። እያንዳንዱን ፈተና ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ከዘዳግም በመጥቀስ ሲመልስ ልብ በል (ሉቃስ 4፡4፣8፣12)። ኢየሱስ አይወያይም ወይም አይከራከርም፤ ሰይፉን ይጠቀማል። የእግዚአብሄር ዘላለማዊ ልጅ እንደዚህ ቅዱሳት መጻህፍትን መጠቀም ካስፈለገው፣ እኛማ እንዴት አብልጠን! ፈተናን በተመለከተ የእግዚአብሄር ቃል ዘወትር ታላቅ መከላከያና ማስረጃ ነው።

> የመጽሐፍ ቅዱስን ከፍተኛ ስልጣንና በውስጡ ያሉትን እውቀት ታላቅ ዋጋ ከዚህ አስደናቂ ታሪክ ምንም ካልተማርን ከዚህ ነጠላ እውነት እንማር ። እናንብበው፣ እንመርምረው፣ በትጋት፣ በጽናት፣ ሳንደክም እንጸልይበት። ጽሆፎቹ በትዝታችን እንዲቀሩና በሚያስፈለግን ቀን በቀኝ በእጃችን የተዘጋጁ እንዲሆኑ ከገጾቹ ጋር በሚገባ ለመተዋወቅ እንጣር። በጸሐይ ብርሃን የተጻፉ ለሚመስሉት ለነዚያ በሺህ ለሚቆጠሩ ግልጽ ክፍሎች ከሁሉም ስህተትና ከ የሐሰት ትርጉም ፈቀቅ ማለት እንቻል። መፅሐፍ ቅዱስ በርግጥ ሰይፍ ነው፤ በሚገባ ማወቃችንን ማረጋገጥ አለብን፤ በውጤታማ ሁኔታ እንድንጠቀመው።
>
> *ጄ. ሲ. ራይል*

እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችን ራሳችንን መጠየቅ አለብን፤ ትክክለኛው ነገር ወይም ልክ ያልሆነው ነገር ምንድን ነው? ላድርገው ወይስ አላድርገው? እዛ መሄድ አለብኝ ወይስ የለወበኝም? መልሱ ሁልጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መገኘት አለበት፤ በአድርጉና በአታድርጉ ረጅም ዝርዝር ውስጥ ሳይሆን ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን በሚሸፍኑ መርሆች እንጂ። ሰይፉን መጠቀም ጥቂት ያልተለመዱ ጥቅሶችን የመጥቀስ ጉዳይ አይደለም፤ ቃሉን ማወቅና ለእያንዳንዱ ሁኔታ መጠቀም መቻል ነው። በሉቃስ 4፡ 16 ዲያብሎስ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሳል (መዝ 91፡11፣12)፣ እርሱን የተጠቀመበት መንገድ ግን በአጠቃላይ ስህተት ነው። ኢየሱስ እነዚህ ቃላት ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለተጠቀሱ አልተወሰደም። መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚያውቅ፣ ምን እየሆነ እንዳለ ያውቃል በቁ 12 ም “ እግዚአብሄር አምላክህን አትፈታተነው” በማለት ይመልሳል (ዘዳ 6፡16)። ሞርሞን ወይም የይህዋ ምስክሮች በርህን እንዲያንኳኩ ዲያቢሎስ ሲልካቸው ይህ ነጥብ በጣም አስፈላጊ ነው ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳሉ፣ ወይ ሁልጊዜ

ትርጉሙን ያጣምማሉ ወይም ያለ አውዱ ይጠቅሳሉ፡፡ በመሠረቱም ብዙ የመፅሐፍ ቅዱስን ክፍል ሆነ ብለው ችል ይላሉ፡፡

በርግጥ በፈተና ጊዜ ብቻ አይደለም ሰይፉን መጠቀም ያለብን፡፡ የማጥቂያም የመከላያም መሳሪያ ነው፡፡ ሰይጣንን ማጥቃት ደግሞም ውጊያውን ወደ ጨለማ ምሽጎች መውሰድ አለብን፡፡ ስለዚህ በመመስከርና ወንጌልን በመስበክ ጊዜ የመንፈስ ሰይፍ ወደፊት መሆን አለበት፡፡ በማር 10 ውስጥ ኢየሱስ ከተጠማ ነፍስጋር ዲል ሲያደርግ ሰይፉን ነው የተጠቀመው፡፡ “የዘላለምን ህይወት እንድወርስ ምን ላድረግ?” ለሚለው ጥያቄ ሲመልስ ኢየሱስ ሀጢአት ምን እንደሆነ ለወጣቱ ሰው ለማሳየት አስርቱን ትዕዛዛት ጠቅሷል፡፡ የወንጌል ክፍሎችን ብቻ ሳይሆን ኢየሱስ ህጉን እንደተጠቀመ ልብ በል፡፡ ይህ ሰይፉን በትክክለኛ ሁኔታ መጠቀም ነው - ትክክለኛ ጥቅስ በትክክለኛ ጊዜ፡፡ በሐዋርያት ስራ ውስጥ ሐዋርያት ወንጌልን ሲያዳርሱ ስንመለከት - ሁልጊዜ ሰይፉን ይጠቀሙ ነበር፡፡ በሐዋርያት ስራ ውስጥ የጴጥሮስን ዝነኛ ስብከት አንብብ፡፡ ደግሞም የእርሱ ምን ያህሉ ቀጥታ የመጽሐፍ ቅዱስ ተዛምዶ እንደሆነ ልብ በል፡፡ ጳውሎስም ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል (ሐዋ ስራ 17፡2)፡፡ መመስከር ዝም ብሎ ምስክርነት የመስጠት ጉዳይ አይደለም፤ ለሀጢአተኞች እግዚአብሄር ስለእነርሱ የሚለውን ነገር መንገር ነው፡፡ የመንፈስን ሰይፍ መጠቀም ነው፡፡

የእግዚአብሄር ቃል ለሆነው ለመንፈስ ሰይፍ ምንም ሌላ ምትክ የለም፡፡ ቃሉንና መንፈሱን ለመለየት በፍጹም ሙከራ ማድረግ የለብንም፡፡ መንፈስ ቅዱስ በፍጹም ከቃሉ ተቃራኒ የሆነ ነገር አይናገርም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በፍጹም አልፎ አይሄድም፡፡ ቃሉ ያለ መንፈሱ ትርጉም የለሽ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ይጠቀማል “መንፈስም ህይወትን ይሰጣል”፡፡ ስለዚህ ቃሉን ውደድ፣ ለእርሱ ተጠንቀቅ፣ አንብበው፣ እወቀው፣ ከዚያም ተጠቀመው፡፡ በእርሱ ዲያብሎስን ተቃወም ከአንተም ይሸሻል፡፡

10. እያንዳንዱን የጦር ዕቃ በጸሎት ልበስ

“በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤” (ኤፌ 6፡18)

ጳውሎስ የእግዚአብሄር ዕቃ ጦረ አስተምህሮውን ይደመድማል። የሮማንን ወታደር ንጽጽር በመውሰድ የተለያዩ የጦርዕቃ አይነቶችን አመለከተ ደግሞም ከዲያብሎስ ጋር ሲዋጋ አንድ ክርስቲያን የሚያስፈልገውን ትጥቅ አብራራ ። ይህን በማድረግ፣ ወሳኝ መንፈሳዊ ትምህርቶችን አወጣ። አንዱ የተሟላ የእግዚአብሄር ዕቃ አስፈላጊ ነው የሚል ነው። ሌላው ቸል ተብሎ ግማሹን ብቻ የጦር ዕቃ ለብሶ መሄድ ጥቅም የለውም። ለእኛ የእግዚአብሄር አቅርቦት ሙሉ ነው ደግሞም ሁሉም ያስፈልገናል። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሄር የጦር ዕቃውን ለእኛ ሰጥቶአል እኛ ግን ማድረግ አለብን የሚል ነው። ይህ ራስን መግዛትን እና ጥረትን ይጠይቃል። እሱን ማድነቅ ብቻ አይደለም ያለብን፤ አሁንም አሁንም የጦር ዕቃውን ማውለቅና መወልወል የለብንም፤ ልንለብሰው ይገባል። ከፍ ያለ አገልግሎት ሊሰጥ እንጂ ለጌጥ የሚደረግ አይደለም ።

እያንዳንዱ የጦር ዕቃ ምን ማለት እንደሆነ መርምረናል፣ አምናለሁ አሁን ላይ አስፈላጊነታቸውን ተረድተናል። ስለዚህ በዚህ የጦር ዕቃ ራሳችንን እናለብሳለን። በእያንዳንዱ ቀን በጥንቃቄ የደህንነትን ቁር፣ የጽድቅን ጥሩርና የተቀረውን የእግዚአብሄርን አቅርቦት እንለብሳለን። አሁን ለጦርነቱ ዝግጁ ነን ከዚያም ሳይቆይ የሰይጣን የሚንበለበሉ ፍላጻዎች እና ሌሎች ክፉ ጥቃቶች በመንገዳችን ይወረወራሉ። በእግዚአብሄር የጦር እቃ እንተማመናለን ግን ራሳችንን እንዴት እንደገና ተሸንፈን እናገኘዋለን? ይህ ለምንድን ነው የሚሆነው? የጦርዕቃው ጥቅም አልባ ስለሆነ ነውን? አይደለም፣ ችግሩ ከጦር እቃው አይደለም። ችግሩ የጦር ዕቃውን የምንለብስበት መንገድ ነው። የሽንፈቱ ምክንያት የፀሎት እጥረት ነው። የሚከተለውን ሲጽፍ ቅኔ - ጸሐፊው በፍጹም ልክ ነበር፡

የወንጌልን የጦር እቃ ልበስ

እያንዳንዱን በጸሎት ልበስ።

በእግዚአብሔር የጦር ዕቃ ላይ የጳውሎስ አስተምህሮ በቁ 17 ላይ አላበቃም፤ በጦርነቱ ጸሎት ምን ያህል ወሳኝ ነገር እንደሆነ ለእኛ ማሣየቱን ወዲያው ይቀጥላል። ምንም እንኳን ጸሎት የጦር ዕቃው ክፍል ባይሆንም ለጦር ዕቃው ስኬት የግድ አስፈላጊ ነው።

> ስለዚህ ይህ ማለት በእግዚአብሄር ለእኛ የተሰጠን የጦር ዕቃ ከእግዚአብሄር ጋር አንድነትና ህብረት ካላደረግን በቀር ጥቅም ላይ መዋል አይችልም። እግዚአብሄር ለእኛ የሰጠን የጦርእቃ ዝም ብሎ እንደምህታዊ መታሰብ የለበትም። አደጋው፣ ፈተናው፣ ይህንን የጦር ዕቃ እስከለበስን ድረስ ሌላ ምንም ማድረግ የለብንም የሚለው ስሜት ነው። ሁሉ ደህና ነው፤የጦርዕቃው በራሱ ይከላከልልናል፣ ዝም ብለን እናድርገው። ስለዚህ እርሱን ለብሰን ዘና ማለት እንችላለን መጠንቀቅንም እንተዋለን። ይህ ግን የእውነተኛ አቋም ተቃራኒ ነው ይላል ሐዋርያው፤ በዚያ መንገድ ማሰብ ማለት በቃ ተሸንፈሃል ማለት ነው። የጦር ዕቃው ፣ እና መንፈሳዊውም ተዛምዶ ሁልጊዜ ጠቃሚና ህያው በሆነ መንገድ ልንረዳው ይገባል። ዘወትርና በሁለም ጊዜ ከእግዚአብሄር ጋር ህያው በሆነ ግንኙነት ካልሆንን እና ከእርሱ ብርታትና ሀይልን ካልተቀበልን በቀር እያንዳንዱ መሳሪያ በራሱ በጣም ጥሩ ቢሆንም ያ አይበቃንም፤ አይጠቅመንም።
>
> *ዲ. ኤም. ሎይድ. ጆንስ*

ብርታትና ሀይል

የጦር ዕቃው የሚወክላቸው - የተቆጠረ ጽድቅ፣ የደህንነት ተስፋ፣ ወዘተ - ታላቅና ክቡር ናቸው፣ ነገር ግን እነዚህ ነገሮች በራሳቸው በቂ አይደሉም። የጦር እቃውን ለመልበስ ብርታትና ሀይል ያስፈልገናል ያም ደግሞ ጸሎት ማለት ከሆነው ከእግዚአብሄር ጋር ህብረትና አንድነት በማድረግ ነው የሚገኘው ። ፈረስን መጫን፣ የጦር ዕቃ ልብስ ማልበስና ወደ ጦር ሜዳ መላክ ትችላለህ። የጦር ዕቃው ተሟልቶአል ግን ጥቅም አልባ ነው የሚሆነው። ባዶ ቀፎ ብቻ ነው። እንዲሁ እግዚአብሄር በሰማይ እንዳለ መለኮታዊ የጦር ጌታ ከሰማይ የሚያቀብለን ከመሰለን እኛም የጦር ዕቃውን ከናካቴው ላንለብሰው እንችላለን ። አምላካችን እንደዛ አይነት አይደለም፣ አግለግሎት ብቻ የሚሰጥ እንደመኪና ኪራይም ያለ አይደለም ። እግዚአብሄር የጦር ዕቃውን አያከራይም፤ ያ ለእርሱ ምንም ጥቅም ስለሌለው። በሌላ አባባል የእርሱን ጦርነት ለመዋጋት እርሱ የሚሰጠው መሳሪያ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሄር የራሱ ብርታት እንደሚያስፈልገን ነው ጳውሎስ እየተናገረ ያለው።

ለእያንዳንዱ የጦር ዕቃ እግዚአብሄርን ማመስገን አለብን፡፡ ሁሉም የግድ አስፈላጊ ናቸው፣ ግን ከእነዚህ በላይ የሆነ ነገር ያስፈልገናል፡፡ ጳውሎስ የጸሎትን ርእሰ ጉዳይ ሲያስተዋውቅ፣ በቁ 10 ላይ ያለውን እየደገመ ብቻ ነው፡ “በመጨረሻ” የሚለው ቃል የሚከተለው ነገር ሁሉ የዚያ ገለጻ ብቻ ነው፡፡ ሁሉንም የቃጦር በጸሎት በመልበስ ነው “በጌታና በሀይሉ ችሎት መበርታት” የምንችለው፡፡ ከሰማዩ አባታችን ጋር የግል የቀረበ ግንኙነት ያስፈልገናል፡፡ ለዚህም ደግሞ ጸሎት አስፈላጊ ነው፡፡

በክርስትና ህይወት ሁልጊዜ መንፈሳዊ ሚዛን ያለመጠበቅ አደጋ አለ፡፡ ቅዱሳት መጻህፍትን በሚገባ የሚያውቁ አማኞች አሉ በጦር ሜዳ ግን ጥቅም የለሽ ናቸው፡፡ እውነቱን በገዛ ህይወታቸው በቅድስና ወይም ወንጌልን በመስበክ ለአማኞች ማዛመድ አይችሉም፡፡ እውነቱን ያውቃሉ ነገር ግን ከማወቅ ያለፈ ምንም ህይወት የላቸውም፡፡ ያለ ጥርጥር ይህ ጸሎትን ቸል ከማለት የሚመጣ ነው፡፡ በሌላ በኩል፣ ለሰአታት በጸሎት የሚያሳልፉ አማኞች አሉ፣ የእግዚአብሄርን የተገለጠ እውነት ቸል ስለሚሉ እነዚህም በጦርነት ጊዜ ዋጋ የለሽ ናቸው ፡፡

ብርታትና ሀይል የሚመጣው ሁሉን የጦርዕቃ ከመልበስና ከሁሉን ቻይ ከእግዚአብሄር ጋር በጸሎት ህብረት ከሚያደረግ ህይወት ጋር ሲዋሀድ ነው፡፡

> ጸሎት መጣበቅ ያለበት ክክርስትና የጦርዕቃ ሌሎች ክፍሎች ሁሉ ጋር ነው፣ ቁ 18፡፡ ጸሎትን ከእነዚህ ጸጋዎች ሁሉ ጋር ማገኛኘት አለብን፡፡ እነዚህን መንፈሳዊ ጠላቶቻችንን ለመከላከል፣ የእግዚአብሄር ርዳታና እገዛ በመለመን፣ እንደ ሁኔታው አስፈላጊነት፣ ሁልጊዜ መጸለይ አለብን፡፡
>
> *ማቲው ሄንሪ*

“በመንፈስ ስለ መጸለይ” እና “ስለ ሁሉም አይነት ጸሎቶች” ገለጻ እንደሚገባ ተመላላስ በተሰኘው ተከታታይ ጽሁፍ ሌላ እትም ላይ “ጸሎት” የሚለው ምዕራፍ ውስጥ ማንበቡ የሚረዳ ነው፡፡ እስትንፋስ ለአካላችን እንደሆነው ሁሉ ጸሎትም ለነፍሳችን እንዲሁ ነው፡፡ ሁሉን የጸሎት አይነቶች መጸለይ አለብን፣ በሁሉም ስፍራዎች ከሁሉም በላይ ደግሞ በመንፈስ መጸለይ ያስፈልገናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ላይ መስራት ያስፈልገናል፡፡ ይህ በእኛ ካልተፈጸመ እንዲፈጸም መትጋት አለብን፡፡ ህይወታችንን ማዘዝ አለብን እንዲፈጸም፡፡ የህይወታችን ማዕከል ስለሆነ በባከነ ሰአት እንዳይደረግ ለጸሎት ጊዜ መስጠት አለብን ፡፡ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ ነው፣ ደግሞም ከዚያ የበለጠ አስፈላጊ ነገር የለም፡፡ ከዚህ ጋር ሲወዳደር

ሁሉም ተራ ነው። ከእግዚአብሄር ጋር ህብረትና ቅርበት ከሌለን፣ ምንም የለንም ደግሞም ምንም አይደለንም። ይህ ካለን ግን ብርቱ ነን፤ ከዚያም በላይ የማንረታ ነን።

የእግዚአብሄር የጦርዕቃ ሁሉ አድርግና ጸልይ። ይሄ ጦርነቱን ቀላል አያደርገውም፣ ነገር ግን በሽንፈትና በድል መካከል ያለውን ልዩነት ያጎላዋል።

ስለዚህ በታላቅ ሀይል ጽና፣

በሙሉ ሀይል በርታ

የእግዚአብሄር ሙሉ የጦር ዕቃ

ለውጊያ ሊያስታጥቅህ ያወጣህማል

ሰይፍህ እያበራ እንዲቆይ ለማድረግ

በማያቋርጥ እንክብካቤ ይጠብቅሃል

በመሪህ እይታ ፊት በማገልገል

በጸሎትም በመንቃት።

ከሀይል ወደ ሀይል ሂድ

ታገል፣ ተዋጋ ደግሞም ጸልይ

የጨለማ ሀይላትን ሁሉ ርገጣቸው

የመልካሙን ውጊያ ቀን አሸንፍ

እነዚህን ሁሉ አድርገህ

ያለፉ ትግሎችህንም ሁሉ

በክርስቶስ ብቻ ታሸንፋለህ

በፍጻሜም በድል ትቆማለህ።

ቻርለስ ዌስሊ

11. ድል

“ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።” (1 ቆሮ 15፡57)

የመንፈሳዊ ውጊያ ትልቁ ነገር ድል የተረጋገጠ መሆኑ ነው። ውጊያው በእግዚአብሄርና በሰይጣን መካከል ነው። የተሳተፍነው ክርስቲያኖች ስለሆንን ነው እንጂ የእኛ ውጊያ ስለሆነ አይደለም፤ ውጊያው የእግዚአብሄር ነው። ሰይጣን ብርቱ ፍጡር ነው እግዚአብሄር ግን ሁሉን ቻይና የማይሸነፍ ነው። ለዚህ ነው ድል የተረጋገጠው። የድሉን ምንነት ለመረዳት አንድ ጊዜ ደግመን የውጊያውን ምንነት እንመርምር። ይህን ለማድረግ በዚህና በ1982ቱ በፋልክላንድስ ጦርነት መካከል ንጽጽር እናደርጋን።

በፋልክላንድስ ወደቦች የወንዶች፣ የሴቶችና የልጆች ማህበረሰብ በሳላም ይኖሩ ነበር። በብሪቲሽ ዘውድ ጥበቃና ህግ ስር ነበሩ። በዚህም ደስተኞች ነበሩ። ጠላት ግን ያንን ስፍራ ሲወርር ፣ የውጭ አገዛዝና ስልጣንን በመጫንና ነጻነታቸውን በመውሰድ ሁሉም ነገር ተቀየረ። ስለዚህ ፋልክላንደሮችን በተመለከተ ማድረግ የሚችሉት ምንም ነገር አልነበረም። ለመቋቋም የማይችሉ ደካሞች ነበሩ፤ ብቸኛው ተስፋቸውም ብሪታንያ እነርሱን ለማዳን በበቂ ሁኔታ የምትረዳቸው መሆኑ ነው። ይህንንም ብሪታንያ አደረገች። ድርድርና ውይይት ተስፋ የሌለው መሆኑ ተረጋገጠ ስለዚህም ግብረሀይል ተላከ፤ ጠላት መሸነፍና፣ ትቶ ለመሄድ መገደድ አለበት። ይህንን የማግኘት ዋጋ በህይወትና በመሳሪያ ሲለካ በጣም ከፍ ያለ ነበር። አንዳንዶች ዋጋው በጣም ከፍተኛ እንደሆነና ፎክላንዶችም ለእርሱ እንደማይመጥኑ ይናገሩ ነበር። ዋጋው ግን ተከፍሎ ነበር። ህይወቶች ጠፍተው ድልም ተገኝቶ ነበር፤ ነጻነትም ለእነርሱ ሲመለስ ታላቅ ሀሴት ነበር። ጠላት ግን በመሸነፍና በመዋረድ ፈንታ ለፎክላንደሮቹ ያለውን ፍላጎት አልቀነሰም ነበር ስለዚህም ፍርሀት በድል አድራጊዎቹ ላይ አንጣቦ ነበር። በዚህም ሁሉ ጠርት በበረካታ የማዕድናት ሜዳዎች እና ጫካዎች ከኋላ ቀርቶ ነበር። እነዚህም ለሚመጣው ለረጅም ጊዜ ሊሆን የሚችል የአደጋ ምንጭ ይናሆሉ። ስለድሉ ምንም ጥርጥር የለም ነገር ግን ፍርሀቱና አደጋው ግን አሁንም አሉ።

አለም የእግዚአብሄር ፍጥረት ነው በውበቱም እንዲደሰቱ ወንዶችና ሴቶችን በርሱ ውስጥ አስቀምጧቸዋል። ከእግዚአብሄር ስልጣንና አገዛዝ ስር ነበር። ከዚያም ሰይጣን በታላቅ

የሀጢአት መሳሪያው ወረረው። አዳምና ሄዋን ወዲያው ተሸነፉ፣ ከዚያም ጊዜ ጀምሮ የሰው ዘር በሙሉ ባሪያ ሆነ። ሰይጣን የዚህ አለም ንጉስ ሆኖ ይገዛል። ሰውን በተመለከተ መደረግ የሚችል ምንም ነገር አልነበረም፤ በርግጥ እንደ ፎክላዶች ሳይሆን ሰው በፈቃዱ ነው ምርኮኛ የሆነው። ብቸኛው ተስፋችን እኛን ለማዳን በመምጣት በበቂ ሁኔ ለእኛ ዋጋ መስጠቱ ነው። ይህንን እግዚአብሄር አደረገ። ድርድሮች አልነበሩም። ጠላት ሰይጣን መሸነፍ ሰውም ነጻ መውጣት አለበት። እግዚአብሄር ግን በጦር ፅቃ የሚዋጋ ግብረ ሀይል አልላከም። ይልቁን፣ “ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ” (ገላ 4፡4)። የእግዚአብሄር ወጪ በጣም ከፍተኛ ነበር፤ ጥፋተኛ ሀጢአተኞችን ለመዋጀት ልጁ መሞት ነበረበት።ዋጋው እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ሀጢአተኞችም እንደማይገባቸው በሚገባ መከራከር ይችል ነበር። እንዲህ ሆኖ ግን ጌታ ዋጋውን ከፈለ። ኢየሱ በቀራንዮ ላይ ሞተ ድልም ተከናወነ።

በከበረውም በኢየሱስ ደም ደህንነት ተገዛ ሲድኑም ነፍሳት ሀሴት አደረጉ። ቢሸነፍም ግን ሰይጣን ተስፋ አልቆረጠም የዳኑትን ማስፈራራቱን ቀጠለ። አሮጌው ማንነታችን ስላልሞተና እንደመንፈሳዊ የማዕድን መሬት እንዲሁ ስለሚያደርግ አሁንም ጠላት ተጽኖ ያደርጋል ። ስለድሉ ጥርጥር የለም ማስፋራራቱና አደጋው ግን አሁንም ቀጥሏል።

ከዚህ 3 የተለያ የድል አይነቶች እንዳሉ ማየት እንችላለን።

የደህንነት ድል

ክርስቲያን ከሆንክ ይህ ተከናውኗል። ያለዚህ ድል ስለጦር ሜዳ ምንም አታውቅም። በሀጢአት እስር ቤት የተዘጋብህ ገና የሰይጣን ምርኮኛ ሆነህ ይሆናል ። እግዚአብሄር በፍቅሩና በምህረቱ አንድን ነፍስ ሲያድን የትልቅ ድል ቅጽበት ነው። ይህ በመስቀል ላይ የክርስቶስ ትልቅ ድል ውጤት ነው። የደህንነት ድል በሀጢአት ጥፋትና ኩነኔ ላይ ማሸነፍ ነው። በደህንነት ጊዜ ፍርድ በጽድቅ ተተክቷል። በሌላ አነጋገር ጥፋተኛው ሀጢአተኛ ከእግዚአብሄር ሰላም አግኝቷል። በክርስቶስ ጸድቅ አማካኝነት በእግዚአብሄር ፊት ተቀባይነት አግኝቷል። የእግዚአብሄር ህግ የሀጢአት ደሞዝ፣ ሞት፣ ሙሉ በሙሉ እንዲከፈል ይፈልጋል። የክርስቶስን ጽድቅ ለእኛ በመስጠት ጽድቅ ሙሉ በሙሉ የህጉን ትክክለኛ መስፈርት ያሟላል (ሮሜ 3፡21-26)። እኛን ተክቶና ቅጣታችንን ተሸክሞ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት፣ በእኛ ቦታ ነው የሞተው (2 ቆሮ 5፡18-21)።

ኩነኔ የለም (ሮሜ 8፡1)

የሀጢአት ይቅርታ (ኤፌ 1፡7)

እርቅ (ቆላ 1፡21፣22)

ያ ድል ፍጹም ነው። ምንም ሊቀይረው አይችልም። ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰራልን የስርየት ፍጹም ስራ ስለሆነ ፍጹም ድል ነው። ስለዚህ የሰጠን ደህንነት ከእኛ በፍጹም ሊወሰድ አይችልም (ዮሐ 10፡28፣29)። ስለዚህ ይህ ሀሴት የምናደርግበት ድል ነው። እኛን ስላዳነ እግዚአብሄርን በማመስገን ለክርስቲያን ይህን ድል ማክበር የየለት ልምምድ መሆን አለበት።

የክርስትና ህይወት ድል

በሀጢአት ቅጣትና ፍርድ ላይ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶ ድል ብናገኝም፣ የጠላት ሀይሉና ተጽኖው ግን ከእግዚአብሄር ጋር ያለንን ሰላም ይዋጋል። ደህንነታችን የሚጠፋ አይደለም የእርሱ ደስታ ግን ሊጠፋ ይችላል፣ የደህንነትም ማረጋገጫ እንደዛው ሊጠፋ ይችላል በሀጢአት ሀይል ላይ ያለውን ድል ካላወቅን በቀር። ለዚህ ድል ነው የእግዚአብሄር የጦር ዕቃ ያስፈለገን። የደህንነት ድል የግል እውነታ ስለሆነ በጦርሜዳ ያለንበትን ብቸኛ ምክንያት በፍጹም መርሳት የለብንም ። በትክክል ክርስቲያን እንደሆንን ጦርሜዳው ማስጃ ነው፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ ድልን ሳይሆን ሽንፈትን የምንለማመድ ነው የምንመስለው። ትዕግስት እናጣለን፣ እንቀናለን፣ ትምክህት ይነፋናል፣ ሀጢአት በማንነታችን ላይ ይረማመዳል። በክርስቲያን ህይወት ሽንፈት ትክክለኛ ነገር፣ ድል ደግሞ ያልተገባ ነገር ይመስላል። ይሁን እንጂ ባብዛኛው ይሄ ቢሆንም የሚታየው፣ እውነት ግን አይደለም። ይህ ከሰይጣን ትላልቅ ዘዴዎች አንዱ ነው። ፍጹም አለመሆናችን እውነት ነው በዚህም ህይወት በፍጹም እንደዛ አንሆንም፤ እንደ ክርስቲያን መሆን ያለብንን አንዳችንም አለመሆናችንም እውነት ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሄር ይመስገን አንድ ጊዜ ሆነን የነበርነውንም አለመሆናችንም እውነት ነው። ራስህን መርምር። እንዲህ አይደለምን? ስለ ሀጢአትህ ታውቃለህ (ሰይጣንም ያንን ያያል)፣ ስለ እግዚአብሄር በአንተ ውስጥ የመቀደስ ስራም አታውቅምን? በፊት ስታደርገው እንደነበረው አትኖርም ደግሞም አታደርግም። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ ታነባለህ ደግሞም ትጸልያለህ፤ በፊት ይህንን በፍጹም አታደርግም ነበር። በህይወትህ በሀጢአት ላይ ድል ስለማግኘትህ ማስረጃ የሚሆኑ 101 ትናንሽ ነገሮች የሉምን ? እንዲህ ማለት ያልተለመደ ሊሆን ይችላል ነገር ግን እውነቱ እንደዚህ ነው፣ በህይወታችን ላይ ስለ ሰይጣን የበለጠ ስናውቅ፣ ያነሰ ተጽእኖ ነው ያለው።

ጦርነቱ የሀጢአት ሀይል ማስረጃ ነው፣ ግን አሁንም ከጌታ ጋር የመሆንህ እውነታ በህይወትህ በርካታ አቅጣጫዎች ላይ የድል ማስረጃ ነው። ለገጠሙን ብዙ ሽንፈቶች ሰበበኞችና ግዴለሽ መሆን አንፈልገም ነገር ግን በውስጣችን እየተካሄደ ያለውን ጸጋም መቀነስ አንፈልግም። ፈተናን ባላሸነፍን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት በንስሀ መቃተት አለብን፤ በፈተና ላይ የርሱ ሀይል ድል አድራጊዎች እንድንሆን ሲያስችለን ግን ሀሴት ማድረግና ጌታን ማመስገን መማርም አለብን።

በእግዚአብሄር የጦር ዕቃ ራሳችንን ስናለብስ፣ ጸንተን መቆም ስንችልና በሰይጣን ጥቃቶች ላይ ድል ማድረግ ስንችል፣ በርግጥ ድሉ ጣፋጭ ጣዕም አለው። የትቢት ጣዕም አይደለም የትህትና እንጂ። በራሳችን ብርታት ተስፋ ቢሶች መሆናችንን ስለምናውቅ። ድላችን ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለን ህብረት ብቻ እንደሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ እግዚአብሄር በእርሱ ሀሴት እንድናደርግና ምስጋናና አምልኮአችንን በየለት - ለተባረከው ጌታ ኢየሱስ፣ "ለሀጢአት እጥፍ መዳኒት ለሆነው" ብቻውን "ከርሱ ቅጣትና ሀይል ሊያነጻን" ለሚችል፣ ለርሱ እንደንሰጠው ይፈልጋል።

የመጨረሻው ድል

የመጨረሻው ድል ሙሉ በሙሉ የሀጢአት፣ የክፋትና የአለማዊነት መጥፋት ነው። ይህ ኢየሱስ ወደዚህ አለም በውርደት ሳይሆን በክብር ዳግም ሲመጣ ይሆናል፣ ሰይጣንም ለዘላለም ይጠፋል። ስለዚህ ድል ድንቅና የተሟላ ነገር ለመረዳት የሚከተሉትን ቅዱሳት መጻህፍት አንብብ፡

የመምጣቱን ተስፋ	ዮሐ 14፡1-4
ለአማኞች ይሆናል	1 ተሰ 4፡13-18
ለፍርድ ይሆናል	ማቴ 25፡31-46
አዲስ ሰማያትና አዲስ ምድር	2 ጴጥ 3፡1-13
የክርስቶስ ድል	ራእይ 19
ፍርድ በሰይጣን ላይ	ራዕይ 20

የጦርነቱ አላማ ሰይጣንን ለማሸነፍ፣ በዚህ አለም ያለችግር የእግዚአብሔር ክብር እንዲመለስ፣ እና ልክ ፍጹምነትን ሀጢአት ሳያበላሸው እንደነበረው መላውን ፍጥረት እንደገና ለማቋቋም ነው። በመስቀል ላይ የክርስቶስ ድል ይህንን ለማሳካት ረጅም መንገድ ተጉዟል። ለምሳ ያክል፣ በዘፍ 3 አዳም ሀጢአት ባደረገ ጊዜ የተወሰኑ ባርኮቶችን አጥቷል፤ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውንም ሰላም አጥቶአል እግዚአብሔርንም ፈርቷል (ቁ 10)፤ ወደ እግዚአብሄር መግባትን አጥቶአል ደግሞም ተባሮአል (ቁ 23፣24)። እነዚህ የጠፉ ሁሉም በረከቶች በመስቀል ላይ ክርስቶስ ስላደረገውና በህይወታችን ስላለው የርሱ ድል፣ ይህ አሁን የእኛ ተሞክሮ ነው። አሁንም ግን የሰይጣን ተጽእኖና የሀጢአት ሀይል በአለም ውስጥ በጣም ግልጽ ናቸው። ይሄ እግዚአብሔር እሱን ማሸነፍ ስላልቻለ ወይም መስቀሉ ሙሉ ድል ስላልሆነ አይደለም። ውጊያውን ለመዋጋትና ድል ለማግኘት እግዚአብሄር የመረጠው መንገድ ስለሆነ ነው እንጂ።

ስለፍጻሜው ድል ምንም ጥርጥር የለም። የቀራንው መስቀልና ባዶው መቃብር ያንን አረጋግጠውልናል። ሰይጣን የተሸነፈ ጠላት ነው። “አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን፣ የጻድቃንን መኖሪያ” እግዚአብሄር ወደመኖር ሲያመጣ የፍጻሜው ድል ይከበራል፡ “(2 ጴጥ 3፡13)።

> እግዚአብሄር ሰውን ሲሰራ፣ ከሁሉም አስቀድሞ የሚኖርበትን አለም ሰራ። ሰው መንፈስ እንደተሰራው አልተሰራም፤ ገና ከመጀመሪያው አካል፣ ነፍስና መንፈስ ሆኖ ነበር የተሰራው፣ እግዚአብሄርም በአካላዊ አጽናፈ አለም እንዲኖር ሰራው። ክርክሬ፣ እግዚአብሄር ሰይጣንን ለመጨረሻና ሙሉ በሙሉ ማሸነፍ ካለበት ሁሉንም ነገር ወደ መጀመሪያው መመለስ አለበት። ስለዚህ ሰማይ ማለት አማኞች የሆንን በመጨረሻ ይህንን አሮጌ አካል አስወግደን በመንፈሳዊው ግዛት በንጹህ መንፈሳዊ ሁኔታ እንኖራለን ማለት ከሆነ፣ መዋጀትና ደህንነት ገና አልተሟላም ማለት ነው። የእግዚአብሄር የመዋጀት እቅድ ሰው በአካል የሚኖርበት ምድር እስከሚኖር ድረስ የተሟላ አይደለም። እንደደገና የተገኘ ገነት ከዛ ያነሰ ነገር ሊሆን አይችልም። እግዚአብሄር ይመስገን፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው ነገር ያ ነው። ግልጽ ወዳልሆነ፣ ወደደበዘዘ፣ በትክክል ወዳልተተረጎመ መንፈሳዊ ሁኔታ ወደፊት ማየት የለብንም። እንደዛ አይደለም፣ በአካል ውስጥ መሆን አለብን፣ ጽድቅ በሚኖርበት፣ ከአዲስ ሰማያት በታች በአዲስ ምድርም መሆን አለብን ። ያ፣ እና ከዛ በምንም ያላነሰ፣ የእግዚአብሄርን ክብርና የእርሱን የመጨረሻ ድል በዲያብሎስና የእርሱ በሆኑት ላይ ይመሰርታል።
>
> *ዲ. ኤም. ይድ. ጆንስ*
